# የፌደራል የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠና ማዕከል

## ለረጅም ጊዜ የስራ ላይ ሰልጣኞች የተዘጋጀ የስልጠና ሞጁል

# የውርስ ሕግ

በፌደራል የፍትሕ አካላት ባለሙያወች ስልጠና ማእከል የተዘጋጀ

## ማውጫ

ምዕራፍ አንድ ........ 3
ስለውርስ ህግ በጠቅላላውና የአወራረስ ስርዓት በኢትዮጵያ........ 3
1.1. ስለ ውርስ ህግ በጠቅላላው ........ 3
1.2. የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያ ........ 4
1.3. የተለያየ አይነትና ባሕሪያት ውጤት ያላቸው የውርስ አወራረስ ደንቦች መኖራቸው ያለው ጠንካራና ደካማ ጐን 5
1.4. የሸሪዓና የፍትሐብሔር የውርስ ደንቦች መካከል የሚታየው መሠረታዊ ልዩነትና በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች........ 6
ምዕራፍ ሁለት........ 9
የኢትዮጵያ የውርስ አስተላለፍ ሥርዓት በጠቅላላው፣ ........ 9
ምዕራፍ ሦስት ........ 21
ለመውረስ ስለሚያስፈለግ ችሎታ........ 21
ምዕራፍ አራት ........ 25
ሳይናዘዝ የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት xፈጻጸም........ 25
ምዕራፍ አምስት ........ 33
በሟች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀም ውርስ........ 33
ምዕራፍ ስድስት........ 56
ውርስን ማጣራት እና ውርስን ማስተዳደር ........ 56
ምእራፍ ሰባት ........ 63
ስለውርስ የተደነገጉ የይርጋ ጊዜ ገደቦች ........ 63
መግቢያ ........ 63
ዋቢ መፅሐፍት ........ 78

# ምዕራፍ አንድ

# ስለውርስ ህግ በጠቅላላውና የአወራረስ ስርዓት በኢትዮጵያ

**የስልጠና ምዕራፉ ግብ፡-**

ሰልጣኞች፡-

- የኢትዩጵያ ውርስ ህግን በተመለከተ ለቀጣይ ስልጠና መንደርደሪያ የሆነ አጠቃላይ ግንዛቤ ይጨብጣሉ፡፡
- በኢትዮጵያ በመደበኛውና በሸሪያ ስርአት መካከል ያለውን የአወራረስ ልዩነትና የሚያጋጥሙ ችግሮችን ይለያሉ፣

## 1.1. ስለ ውርስ ህግ በጠቅላላው

በዓለማችን እየተሠራባቸው ያሉ ዘመናዊ የውርስ ህጋጋት በመሠረታዊነት ሶስት አይነት የአወራረስ ሥርዓቶችን የሚዘረዝሩ የውርስ ደንቦችን የያዙ ናቸው፡፡ እነርሡም፣

- የሟች ውርስ ያለኑዛዜ ለሟች የሥጋና የጋብቻ ዘመዶች የሚፈፀሙበትን የአወራረስ ሥርዓት በዝርዝር የሚደነግጉ፣ ደንቦችን የያዙ (Rules of Intestate Succession)
- የሟች ውርስ በሟች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀምበትን ሥርዓት የሚደነግጉ ደንቦች የያዙ (Rules of testate Succession)
- የሟች ውርስ በሟች በክፊል ኑዛዜና በከፊል ያለኑዛዜ የሚፈፀምበትን ደንቦች የያዙ (Rules of partially intestate and partially Testate secession) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ አሁን እየተሠራባቸው ያሉ የውርስ ህጋጋት የሟች የሚንቀሣቀሥ እና የማይንቀሣቀሥ ንብረት ገንዘብና ከሌሎች ሰዎች የሚሰበሰብ ብድር ወይም ተከፋይ ገንዘብ የአክስዮን ድርሻና ሌሎች በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጡ የሟች መብትና ግዴታዎች ለሟች ወራሾች ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ የሚተላለፍበትን የአወራረስ ሥርዓት የሚደነግጉ ናቸው፡፡

## የማሰቢያ ጥያቄዎች፡-

1. የውርስ ህግ አንድ ሰው በህይወት በነበረበት ጊዜ ያለው የንብረት ባለቤት የመሆን መብት በሞት ከተለየም በኋላ ተፈፃሚነት የሚያደርግ ከንብረት ባለቤትነት መብት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ የህግ ክፍል እንደሆነ የሚገልፁ ጸሐፊዎች አሉ፡፡ የውርስ ህግ መሠረታዊ ግብና ዓላማ ምንድን ነው?
2. የኢትዩጵያ የውርስ ስርአት ከየትኛው የሚመደብ ነው?
3. በኢትዩጵያ የውርስ ህግ በውርስ ንብረት ውስጥ የሚካተተውና የማይካተተውን ይለዩ?

### 1.2. <u>የአወራረስ ሥርዓት በኢትዮጵያ</u>

ስለ ኢትዮጵያ የአወራረስ ስርዓትና ህግ ስናነሳ በአሁኑ ጊዜ የሚታየው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ያለውን የአወራረስ ስርዓት ነው፡፡ ህገ መንግስቱ የግል መብቶችን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች በተከራካሪዎቹ ፈቃድ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ ፍርድ ቤት የመዳኘት መብትን በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሀይማኖት እና የባህል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም ዕውቅና ሊሰጡ እንደሚችሉ ከመደንገጉም በላይ ህገመንግስቱ ከመጽደቁ በፊት ዕውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የኃይማኖትና የባህል ፍርድ ቤቶች በህገመንግስቱ መሰረት በአንቀጽ 78 ንዑስ አንቀጽ 5 በግልጽ ደንግጓል፡፡ በዚህ መሰረት፣ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 188/1992 መሠረት ተጠናክሮ ስራውን የቀጠለ ሲሆን ክልሎችን የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን የማጠናከሪያ አዋጆችን በማወጅ ስራቸውን እንዲቀጥሉ አድርገዋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ፀድቆ ሥራ ላይ ከዋለበት ነሐሴ 1 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ባህላዊና ልማዳዊ የአወራረስ ደንቦች፣ ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች ህገ መንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ አግኝተው ከፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች ጐን በጐን እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ስለዚህ አሁን ያለው የአወራረስ ስርዓቶች ስንመለከት ሁለት መሠረታዊ እና ልዩ ባህሪያት ያሉት ነው፡፡

- የመጀመሪያው በእኩል ደረጃ ህገመንግስታዊ ዕውቅናና ጥበቃ በተሰጣቸው፣ 1)ባሕላዊና ልማዳዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች 2)ሀይማኖታዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች እና 3) በፍታብሔር ህጉ

የተመለከቱት የተለያዩ አይነት ባህሪ እና ውጤት ያላቸው የአወራረስ ሥርአቶች በአገሪቱ ውስጥ ተግባራዊ እየሆኑ መሆናቸው ሲሆን፣

- ሁለተኛው በሟች የውርስ አወራረስ ሒደት ሥርዓት ሲፈፀም የሚነሱ ክርክሮች ተፈፃሚነት ያላቸውን የአወራረስ ደንቦች የመምረጥ መብት ሙሉ በሙሉ የተከራካሪዎች መሆኑ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት ከተከራካሪዎቹ አንደኛው በልማዳዊ ወይም ሀይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች መሰረት ለመዳኘት ፈቃደኛ ካልሆነ ጉዳዩ በፍታብሔር ህጉ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚፈፀም መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡- ስለሆነም ዜጐች የፍታብሔር ህጉን የውርስ ደንቦች ተፈፃሚነት የሚያስቀሩት ጉዳዩ በባህላዊ ወይም ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንብ እንዲፈፀም ሙሉ በሙሉ ሲስማሙና ፈቃደኛ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡

## 1.3. የተለያየ አይነትና ባሕሪያት ውጤት ያላቸው የውርስ አወራረስ ደንቦች መኖራቸው ያለው ጠንካራና ደካማ ጐን

ከላይ እንደተገለፀው በአገሪቱ አንድ ወጥ የሆነ የአወራረስ ሥርዓት ኖሮ የማያውቅ ሲሆን አንድና ወጥነት ያለው የአወራረስ ሥርዓት ለመዘርጋት የተደረገው ሙከራም ተግባራዊ ውጤት አላስገኘም፡፡ ይህም በመሆኑና ህገመንግስቱ ባህልን፣ ሃይማኖትን መሰረት ለሚያደርጉ የአወራረስ ደንቦች ዕውቅናና ጥበቃ ሰጥቷል፡፡ ይህም ዜጐች በፈቃዳቸውና በፍላጎታቸው የህብረተሰባቸው ባህላዊ የውርስ ደንቦች ወይም ኃይማኖታዊ የውርስ ድንጋጌዎች መሰረት የሟች ውርስ የሚያስፈፅሙበት እድል የሚሰጥ በመሆኑ፣ ዜጐች የግል ጉዳያቸው በመረጡት መንገድ የመጠየቅና የመዳኘት መብታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይህም ሊመሰገን የሚገባው ጠንካራ ጎን እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ከአንድ በላይ የሆኑ የውርስ አወራረስ ስርዓቶች በአንዲት አገር ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞከር የአንዱ የአወራረስ ሥርዓት ደንቦች ከሌላው የሚለያዩበት ሰፊ ሁኔታ ስለሚኖርና ከሟች ወራሾች መካከል የተወሰኑትን በአንደኛው የአወራረስ ስርዓት ሌሎቹ ደግሞ በሌላ የአወራረስ ሥርዓት መሰረት የሟች ውርስ እንዲፈፀም ለማድረግ የየበኩላቸውን ጥያቄ ስለሚያቀርቡና በሌሎች ምክንያቶች የሚፈጠረው የተለያዩ የውርስ ደንቦችና የአፈፃፀም ግጭት ምክንያት የሚፈጠሩ ችግሮች አሉ፡፡ በኢትዮጵያ ተፈፃሚነት ያላቸው ባህላዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውን የሚያሳይ ወጥ ጥናት ባለመደረጉ በእርግጠኝነት ብዛታቸውን፣ ይዘታቸውንና የአፈፃፀም ሒደታቸውን ከሌሎች ኃይማኖታዊና የፍታብሔር ህግ የውርስ ድንጋጌዎች ጋር በማነፃፀር ለመግለጽ አይቻልም፡፡ ሆኖም የተለያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ጎሳዎችና ማህበረሰቦች የየራሳቸው ባህላዊ የውርስ አወራረስ ደንቦች እንዳላቸውና እነዚህም በይዘትም ሆነ በአፈፃፀም የተለያየ ይዘትና ባህሪ እንዳላቸው በተለያየ ጊዜ ከተደረጉ አጫጭር የዳሰሳ ጥናቶች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ስለሆነም በኢትዮጵያ ተግባራዊ እየሆኑ ባሉ የባህል አወራረስ ደንቦች መካከል ያለው ልዩነትና አንድነት እንደዚሁም እያንዳንዱ ባህላዊ የውርስ አወራረስ ሥርዓት እየተሰራባቸው ካሉት የፍትሐብሔር ህጉ እና የሸሪዓ የውርስ ድንጋጌዎች ያላቸውን አንድነት እና ልዩነት በንጽጽር ለማቅረብ አይቻልም፡፡ በአንጻሩ ጐን በጎን የሚተረጐሚቸው እና የሚያስፈጽሚቸው ፍርድ ቤቶች ተቋቁመው እየተሰራባቸው ባሉት የፍትሐብሔር ሕግ የውርስ ደንቦችና በሸሪዓ የውርስ ደንቦች መካከል ያለውን መሰረታዊ የይዘት ልዩነትም በአፈፃፀም ሒደት እየተከሰቱ ያሉ መሠረታዊ ችግሮች ማየት በአገራችን የተለያዩ ባህላዊ ኃይማኖታዊና የፍትሐብሔር ህግ የተደነገገውን የአወራረስ ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ሒደት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ለመረዳት ጠቀሜታ ስለሚኖረው በአጭሩ ማየት ይጠይቃል፡፡

## 1.4. የሸሪዓና የፍትሐብሔር የውርስ ደንቦች መካከል የሚታየው መሠረታዊ ልዩነትና በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች

**ሀ**) በሸሪዓና በፍትሐብሔር ህጉ መሰረታዊ የፖሊሲ ሐሳብ ልዩነቶች የሸሪዓም ሆነ የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች መሰረታዊ ግብ የሟችን ውርስ ለወራሾቹ ማስተላለፍ ቢሆኑም በይዘታቸው አንድ አንድ መሰረታዊ ልዩነቶች አሏቸው፡፡ ይህም ልዩነት ሁለቱ ህግጋት መካከል የተካተቱ የፖሊሲ ሀሳብ ልዩነት ነፀብራቅ ነው፡፡ ከልዩነቶቹ ጥቂቶቹን ስንመለከት፣

- የፍትሐብሔር ሕጉ የሟች ወራሾች ከሟች በሀይማኖትና በእምነት መለየታቸው የወራሽነት መብታቸውን አያሳጣቸውም፡፡ በሌላ በኩል ሟች ሙስሊም ከሆነ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ያልሆኑ ወራሻቹ በሟች ውርስ እንዳይሳተፉ የሸሪዓ የውርስ ደንቦች ይከለክላሉ፡፡
- የፍትሐብሔር ህጉ የሟች ሴትና ወንድ ወራሾች በጾታቸው ምክንያት የተለያየ ድርሻ እንዲወስዱ አያስገድድም፡፡ በእኩል የዝምድና ደረጃ እስካላቸው ድረስ እኩል ድርሻ ያገኛሉ፡፡ በሸሪዓ የሟች ሴት ልጆች ከሟች ውርስ አንድ ሶስተኛ የሚሰጣቸው ሲሆን ወንዶች ሁለት ሶስተኛ ይወስዳሉ፡፡
- በሸሪዓ ሚስት ባሏን የመውረስ መብት ያላትና ከባሏ ውርስ አንድ ስምንተኛ የማግኘት መብት ያላት ሲሆን በፍትሐብሔር ህግ መሰረት ሚስት ባሏን የመውረስ መብት የላትም፡፡
- የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ህግ ሟች ከወራሾቹ አንዱን በኑዛዜ የመንቀል መብት ያለው መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን በሸሪዓ ሟች ወራሾቹን በኑዛዜ የመንቀል መብት የለውም፡፡

በፍትሐብሔር ህጉ ሟች በኑዛዜ ንብረቱን ለሶስተኛ ወገን የማስተላለፍ መብት ያለው ሲሆን በሸሪዓ አንድ ሰው በኑዛዜ ሊያስተላልፍ የሚችለው የንብረቱን አንድ ሶስተኛ ብቻ ነው፡፡

### ለ) በአፈፃፀም የሚታዩ ችግሮች

በሁለቱ ህጐች መካከል ያሉት እነዚህ እና ሌሎች መሰረታዊ ልዩነቶች ሟች ሙስሊም በሆነ ጊዜና የሟች ወራሾች የሌላ ኃይማኖት ተከታይ ወይም ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ በሆኑ ጊዜ ወይም ሟች በጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታና ነጠላ የኑዛዜ ስጦታ ንብረቱን ባከፋፈለ ጊዜ በሸሪአ ተጠቃሚ የሚሆኑት ወራሾቹ በሸሪዓ መሠረት ውርሱ እንዲፈፀም ሌሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ህጉ መሰረት ታይቶ እንዲወሰን በየበኩላቸው የወራሽነት ማረጋገጫ ለማግኘትና ውርሱን ለመካፈል ክስ የሚያቀርቡበትና የአንድ ሰው ውርስ ጎን በጎን በሁለት ፍርድ ቤቶች የሚታይበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀፅ 5 ይህንን ችግር ዘለቄታ መፍትሔ ለመስጠት ታስቦ የተደነገገ ሲሆን፣ ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ የፌዴራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን ለማጠናከር አዋጅ ቁጥር 188/1992 ታውጇል፡፡ በተለያዩ ክልሎችም የክልል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ማጠናከሪያ አዋጆች ታውጀዋል፡፡ እነዚህ የህግ ማዕቀፎች ከመውጣታቸው በፊት የነበሩ በርካታ ችግሮችን ለመፍታት እንዲረዱ የሚስተባበል ባይሆንም አሁንም ቢሆን፣

- በህግ ማዕቀፎቹ ድንጋጌዎች ግልፅ አለመሆንና በአንድ አንድ ጉዳዮች ክፍተት ያለባቸው በመሆኑ የተነሳና
- መደበኛው ፍርድ ቤት እና የሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ህግን በመተርጎምና በማስፈፀም ሒደት የየራሳቸው ችግር ያለባቸው በመሆኑ

ሁለቱን የውርስ ህግጋት በማስፈፀም በኩል በርካታ ችግሮች እንደሚፈጠሩና ችግሮቹ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አልፈው የህገመንግስት አጣሪ ጉባኤና የፌዴሬሽን ምክር ቤት የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆኑ መሆኑን አንድ አንድ ጉዳዮችን አንስቶ ማየት ይቻላል፡፡

በዚህ በኩል በህግ አተረጓጎምና አፈፃፀም ያሉ ችግሮችን ለመረዳት

- በአንሻ መሐመድና ከድጃ በሽራ
- በወ/ሮ ፈንታየ መሐመድና ወ/ሮ እናትነሽ ከተማ

መካከል የተደረጉ ክርክሮችንና በየደረጃው የተሰጡ ውሳኔዎች መመርመሩ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ በአገራችን እየተሰራባቸው ያሉ በርካታ ባህላዊና ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች ከፍትሐብሔር ህጉ የአወራረስ ደንቦች ጋር ጎን በጎን ሥራ ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚከሰቱትን ችግሮች መሰረታዊ ባህሪ ችግሮቹ የሚፈቱበትን የህግ አግባብ በመረዳት ለተግባራዊ እንቅስቃሴ ዝግጁ ለመሆን ስልጠናዎች በአካባቢያችን ያሉትን ባህላዊ ኃይማኖታዊ የአወራረስ ሥርዓቶች መሰረታዊ ደንቦች እና

የአፈፃፀም ሥርዓት ላይ ስልጣኖቹ በየአካባቢያቸው የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ግኝት ላይ የጋራ ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ የላቀ ጠቀሜታ ስላለው ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. የሟች ውርስን በማስፈፀም በኩል በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ የተቋቋሙ መደበኛ ፍርድ ቤቶችና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች ላይ የተጣለ የህግ ገደብ አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?
2. ባህላዊ የአወራረስ ደንቦች ኃይማኖታዊ የአወራረስ ደንቦች እና የፍትሐብሔር ህጉ የውርስ ደንቦች ጎን በጎን ሥራ ላይ መዋላቸው ምን አይነት ጠቀሜታ እና ጉዳት ይኖራቸዋል ብለው ያስባሉ? ያብራሩ፡፡
3. አንድ ሙስሊም ወንድ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል፡፡ የሟች ሚስት በሸሪዓ መሠረት ሟች ያገባት ህጋዊ ሚስት መሆኗን አጣርቶ ማስረጃ እንዲሰጣት በአካባቢዋ ላለው የናኢባ ፍርድ ማመልከቻ ታቀርባለች፡፡ ይህ ማለት የጋራ ንብረት አከፋፈል በሸሪዓ መጣራት እንዲከናወን በአዋጅ ቁጥር 188/1992 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት ሰጥታለች ማለት ነውን? ለምን?
4. ወ/ሮ ከድጃ ዑመርና አቶ ሰማን አበጋዝ በሸሪዓ ሕግ መሠረት ተጋብተው ሃያ ዓመት ከኖሩ በኂላ ባልየው በዚህ ዓመት በሞት ይለያል፡፡ በዚህ ወቅት ሴትዮዋ በሸሪዓ መሠረት ከሟች ጋር ጋብቻ ፈጽማ የነበረች የሟች ሕጋዊ ሚስት መሆኗን ለማረጋገጥ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርባ ሸሪዓ በሚፈቅደው መሠረት የተገባች የሟች ሚስት መሆኗን የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሸሪዓ ፍርድ ቤት ይሰጣታል፡፡ በሌላ የፌደራልና የክልሉ የቤተሠብ ሕግ ጋብቻ የሚቋረጥበት አንደኛው ምክንያት ከተጋቢዎቹ አንደኛው በሞት ሲለይ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ጋብቻው ሲፈርስ ደግሞ የጋራ ንብረታቸው እኩል ተከፍሎ የሟች ድርሻ ለወራሾቹ የሚስት ድርሻ ደግሞ ለራሷ እንደሚሆን የቤተሠብ ሕጉ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የሸሪዓ ፍርድ ቤት የሟች ሚስት ስለመሆኗ አረጋግጦ የሰጣትን ማስረጃ በማያያዝ የሟች ወራሾች ግማሽ ንብረቷን እንዲያካፍሏት የሥረ ስልጣን ላለው መደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ የሟች ወራሾች ሚስት ስለመሆኗ ማስረጃ እንዲሰጣት ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ያመለከተች ስለሆነ የንብረት ክፍያውም ጉዳይ መታየት ያለበት በመደበኛው ፍርድ ቤት ሣይሆን ጉዳዩን በመጀመሪያ ባየው የሸሪዓ ፍርድ ቤት በኩል መሆን አለበት በማለት ተቃወሙ፡፡ ይህንንም የሚሉት የንብረት ክፍያው በሸሪዓ ሕግና በሸሪዓ ፍርድ ቤቶች በኩል ቢታይ በሸሪዓው ሚስት ባሏን መውረስ ስለምትችል በሸሪዓ ሕግ መሠረት ከንብረቱ የምታገኘው አንድ አራተኛውን እንጅ ግማሹን ባለመሆኑ ነው፡፡

   ሀ. እርሰዎ ጉዳዩን የያዙት ዳኛ ቢሆኑ የንብረት ክፍፍሉን አስመልክቶ ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 34/5/ እና የፌደራል ሸሪዓ ፍርድ ቤቶችን አቋም ለማጠናከር በወጣው አዋጅ 188/1992 አንቀጽ 4

ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘትና በሸሪዓ ሕግ መሠረት ጉዳዩ እእንዲታይ ፈቃድ ሰጥታለች ብለው ጉዳዩን በሸሪዓ ፍርድ ቤት እንድታቀርብ ይወስናሉን? ለምን?

ለ. ወ/ሮ ከድጃ ዑመር የአቶ ዑስማን አበጋዝ ልጅ ብትሆንና የሟች ልጅና ወራሽ መሆኗን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሸሪዓ ፍርድ ቤት እንዲሰጣት አመልክታ የወራሽነት ማስረጃውን ከወሰደች በኋላ የውርስ ንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ በሸሪዓ ፍርድ ቤት ለመዳኘት ፈቃደኛ ባትሆንና የውርስ የንብረት ክፍፍሉ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት እንዲፈፀም ብትጠይቅ ጥያቄዋ ተቀባይነት ማግኘት አለበት ብለው ያስባሉ? ወራሽነትን እንዲያረጋግጥ ለሸሪዓ ፍርድ ቤት ማመልከቻ ማቅረብ የውርስ ንብረት ክፍያ ስርዓቱን የሸሪዓ ፍርድ ቤት አይቶ እንዲወስን ፈቃደኝነትን መግለጽን ያሣያል ብለው ያስባሉ? ለምን ?

5. የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 27783 ሐምሌ 05 ቀን 1999 ዓ/ም የሸሪአ ፍርድ ቤቶችን ስልጣን በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ከዚህ ሞጁል ጋር የተያያዘ ሲሆን ውሳኔው ትክክል ነው ብለው ያምናሉ? ውሳኔውን ከላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች ጋር እንዴት ያገናዝቡታል?

# ምዕራፍ ሁለት

## የኢትዮጵያ የውርስ አስተላለፍ ሥርዓት በጠቅላላው፣

**የስልጠና ምዕራፉ ግብ፡-**

**ሰልጣኞች፡-**

- የፍትሐብሔር ሕጉ የውርስ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ይዘት፣ አተረጓጐምና በአፈጻጸም ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮች ይለያሉ፡፡
- በጠቅላላና በልዩ የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መካከል የትርጉም ልዩነት በሚያጋጥመበት ጊዜ ችግሩ የሚፈታበትን ክህሎት ይለያሉ፡፡

### 2.1. የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አደረጃጀት

በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ በአምስተኛው አንቀጽ የአገሪቱ የውርስ ስርዓት እንዴት እንደሆነ ዝርዝር የሆኑ ደንቦችን የያዙ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ እነዚ!ህ ስለ ውርስ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አቀራረጽ ስንመለከት በአንድ በከ#ል የውርስ ሕግ ጠቅላላ መሪ ደንቦች የሆኑ ጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች /General Provisions/ ያለ#ት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሟች ውርስ በኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ የሚተላለፍበትን መንገድ በዝርዝር የሚያስቀምጡ ስለ ውርስ ንብረት አስተዳደር እና የውርስ ንብረት እንዴት ለወራሾች እንደሚከፋፈል

የሚዘረዝሩ ልዩ የሕግ ድንጋጌዎች /Special Provisions/ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ ውርስ ስለሚከፈትበት ጊዜና ስፍራ ለወራሾች ሊተላለፉ ስለሚችሉ የሟች መብትና ግዴታዎች እና ሟችን ለመውረስ ስለሚያስፈልግ ችሎታ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826-841 የተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸው በግልጽ ተመልክቷል፡፡

እነዚ!ህ ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የሟች ውርስ በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት መሪ ደንቦች በመሆን በእኩልነት ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው፡፡ ጠቅላላ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የኢትዮጵያ ሕግ ስለ ውርስ ያስቀመጠውን አጠቃላይ መርህ የሚያንፀባርቁ እና አንድ ሰው ወራሽ ሆኖ ለመቅረብ ሟሟላት ያለበትን ሁኔታ የሚደነግጉ ናቸው፡፡ በፍትሐብሄር ሕጉ የሟች ውርስ ያለ ኑዛዜ ወይም በኑዛዜ ለወራሾቹ የሚተላለፍበትን መንገድ በዝርዝር የሚወስኑት ደንቦችና ስለ ውርስ አስተዳደር፣ የውርስ አጣሪ የውርስ ንብረት ክፍፍል የተደነገጉት ገዥነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚ!ህ የኢትዮጵያ የውርስ ሥርዓት አስተዳደርን የሚቆጣጠሩ ዝርዝር ደንቦች የያዙ ሲሆን የውርስ ሕጉን አብዛኛውን ክፍል ሸፍነው እናገኛቸዋለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በውርስ ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች እና ዝርዝር ጉዳዮችን በሚወስኑት ልዩ ድንጋጌዎች መካከል የሰፋ ልዩነት እና የመልእክት አለመጣጣም ያጋጥማል፡፡ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥመን የመጀመሪያው ጥረታችን መሆን ያለበት ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች ተቻችለው በስራ ላይ የሚውሉ ከሆነ አቻችለን ሁለቱም ድንጋጌዎች የወጡበትን ግብ እና አላማ እንዲያስፈጽሙ ማድረግ ነው፡፡

ነገር ግን ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች ተቻችለው በአንድ ላይ በስራ ላይ ለማዋል የሚችሉበት ሁኔታ ካጋጠመን በጠቅላላ የሕግ ድንጋጌዎች እና በልዩ የሕግ ድንጋጌዎች መካከል መሠረታዊ ልዩነት ሲኖር ለልዩ የሕግ ድንጋጌዎች ብልጫ እና ተፈጻሚነት መስጠት አለበት የሚለውን የሕግ አተረጓጎም መርህ መከተል አለብን፡፡ ስለዚህ ለልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ብልጫ በመስጠት ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ከሕግ መተርጎም ተግባር ውስጥ የመጀመሪያው ነው፡፡ በመሆኑም በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 826 - 841 የተደነገጉት ድንጋጌዎች የውርስ ሕግ ጠቅላላ መሪ ደንቦች መሆናቸውን እና ሌሎች ድንጋጌዎች ዝርዝር ጉዳዮችን የሚያብራሩ ልዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በሁለቱ መካከል መሠረታዊ ልዩነት ሲያጋጥመን የሕግ አተረጋጓም መርሆችን በመጠቀም ለተያዘው ጭብጥ እልባት መስጠት እንደሚገባ መዘንጋት የለበትም፡፡

## 2.2. <u>የውርስ መከፈትና በውርስ ስለሚተላለፉ መብትና ግዴታዎች</u>

### 2.2.1. <u>ውርስ የሚከፈትበት ጊዜና ሥፍራ</u>

በብዙ አገሮች ሕግጋት አንድ ሰው በሕግ ጥበቃ ያገኙ መብትና ግዴታዎች ሊኖረው የሚችለው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የፍትሐብሐ@ር ህግ ቁጥር 1" ሰው ከተወለደበት ቀን አንስቶ እስከሞተበት ቀን ድረስ የሕግ መብት አለው'' በማለት በግልጽ ደንግጓል፡፡

በጽንሰ ኃሣብ ደረጃ የሟች ውርስ ተከፈተ የምንለው ሟች በሞት ሲለይ በሕይወት ዘመኑ ሲኖር በነበረው መብቱ ተጠቅሞ ያፈራው ንብረት ባለቤት በማጣቱና ለሟች ግዴታም ተጠያቂ የሚሆን ባለመኖሩ የአንዲት አገር ሕግ የሟችን መብትና ግዴታ ለሌሎች ሰዎች /ወራሾች/ ለማስተላለፍ ስለ ሟች ውርስ አስተዳደር ትኩረት ሰጥቶ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የምናመለክትበት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕግ በዘ!ህ ላይ ያለውን አቋም ስንመለከት አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ በሞተበት ጊዜ ዋና መኖሪያ ሥፍራ በሆነበት ቦታ የሟች ውርስ ይከፈታል'' በማለት የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 826/1/ ይደነግጋል፡፡ ከዘ!ህ የሕግ ድንጋጌ የምንረዳው የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ስለ ሟች ንብረትና የውርስ አስተዳደር ትኩረት መስጠትና ጥበቃ ማድረግ የሚጀምረው ሟቹ ከሞተበት ሠዓት ደቂቃና ሠኮንድ ጀምሮ ምንም አይነት የጊዜ ክፍተት ሣይተው መሆኑን ነው፡፡

ሟች ህይወቱ ማለፉ ከተረጋገጠበት ቅጽበት ጀምሮ የሟች ውርስ ይከፈታል፡፡ የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ በሕግ መወሰኑና ግልጽ በሆነ ድንጋጌ ማስቀመጡ፣ ራሱን የቻለ ጥቅም አለው፡፡ የመጀመሪያው ሟችን የሚወርሰው ሰው ሟች ከሞተ በኍላ በስንት ጊዜ በህይወት የኖረ ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ በሌላ አነጋገር የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ ለማረጋገጥ መርዳቱ ነው፡፡ ሟችን ለመውረስ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር አስፈላጊ መሆኑ በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 830 ተደንግጓል፡፡ የሟች ውርስ የሚከፈተው ሟች በሞተበት ቅጽበት በመሆኑ ሟች ከሞተ በኍላ በአንድ ወይም በሁለት ሠከንድ ዘግይቶ የሞተ ሰው ሟችን ወርሶ እንደሞተ ይቆጠራል፡፡ ስለዚ!ህ የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ ትኩረት ሰጥቶ የሕጉ ድንጋጌ በግልፅ ማመልከቱ$ የወራሽነት ችሎታን እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ የተደነገጉትን የሕግ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም እና ለመተርጎም ጉልህ ጠቀሜታ አለው፡፡

ሌላው በጥንቃቄ መታየት ያለበት ነጥብ፣ የሟች ውርስ መከፈት የሚለውን ጽንሰሀሳብ የሟች ወራሾች ነን የሚሉ ሰዎች የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 996-1002 በተደነገጉት ድንጋጌዎች መሰረት ፍርድ ቤት ቀርበው ከሚያቀርቡት አቤቱታ እና ከሚያስከፍቱት የስረ ፋይል ጋር አንድ አለመሆኑን ነው፡፡ የሟች ወርስ መከፈት የሚለው ጽንሰሀሳብ ሟች በህይወት እያለ የነበረው የፍትሀብሄር መብትና ግዴታ የተቋረጠና የሟች ንብረት በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 942 በተደነገገው መሰረት ‹እንደአንድ ልዩ ንብረት ተቆጥሮ› ህግ ጥበቃ ማድረግ መጀመሩን የሚያመለክትና ይህም የሟች ህይወት ካለፈበት ቅጽበት ጀምሮ የሚከናወን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

የሟች የሕግ ወይም የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ በማስረጃ ከተጣራ በኑላ ይህንኑ የሚያረጋግጥ የፍርድ ቤት ውሣኔ ወይም ትእዛዝ ይሰጠኝ በማለት የሟች ወራሾች ነን የሚሉ ሰዎች የሚያቀርቡት ጥያቄ ውርሱ ከተከፈተ በኑላ የሕጉ የይርጋ የጊዜ ገደብ እስከሚገድበው ድረስ የሚቀርብ የወራሽነት መብት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠኝ ጥያቄ ነው፡፡ ይህም ከሟች ውርስ በወራሽነት ተካፋይ ለመሆን የሚያስችላቸው ማስረጃ እንዲሰጣቸው የሚያቀርቡት ጥያቄ በመሆኑ ከሟች ውርስ መከፈት የተለየ ጽንሰ ሀሣብ ነው፡፡ በመሆኑም የሟች ውርስ የሚከፈትበት ጊዜ ሟች ከዚህ ዓለም በሞት የተለየበት ቅጽበት እንጅ ወራሾቹ የሟች ወራሽ መሆናችንን የሚያስረዳ ማስረጃ ይሰጠን በማለት ፍርድ ቤት ቀርበው መዝገብ ያስከፈቱበት ጊዜ እንዳልሆነ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

በሌላ በኩል ስለ ሕግ እውቀት የሌላቸው ሰዎች የሟች ውርስ ተከፈተ የሚሉት የሟች አርባ ቀን ካለፈ በኑላ የሟች ቤተሰቦች ዘመዶችና በሕይወት ዘመኑ ያፈራቸው ወዳጆቹ ተሰብስበው የሟችን የኑዛዜ እና የሕግ ወራሾች እንደዚሁም ከሟች የተገኘውን ንብረት ለሌሎች ሰዎች በአደራ ወይም በትውስት የሰጣቸው እቃዎች ወይም ገንዘብ በብድር ለሌላ ሰው የሰጠውን ገንዘብና ሟች ያለበትን የሌሎች ሰዎች እዳ ለማጣራት ምክክር እና ምርመራ የሚያደርጉበትን ጊዜ ነው፡፡ ይህ ስርዓት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 እስከ 961 በተደነገጉት የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሚያደርግ የውርስ ማጣራት ስርዓት እንጅ የሟች ውርስ መከፈት የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ጋር አንድ አለመሆኑን መጠቆም ጠቃሚ ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕጉ የሟች ውርስ የሚከፈተው በሟች ዋና የመኖሪያ ስፍራ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ የአንድ ሰው የመኖሪያ ቦታ እና መደበኛ ቦታ በተመለከተ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 174 እና 191 የተደነገገ ሲሆን ሰልጣኞች ከዚህ በፊት ስለ ሰዎች ሕግ በተማራችሁበት ጊዜ በቂ ግንዛቤ አግኝታችኃል የሚል ግምት ስላለ የሟች ዋና መኖሪያ ቦታ የሚባለው የትኛው ነው የሚለውን ነጥብ በዝርዝር ማየቱ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሟች ህይወት ካለፈበት ቅጽበት ምንም የጊዜ ክፍተት ሣይተው በሟች ዋና መኖሪያ ስፍራ ውርሱ እንደሚከፈት ይደነግጋል፡፡ የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ጊዜ ማወቅ ስለ ወራሽነት ችሎታ እና ሌሎቹን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ለመረዳት እና ለመተርጐም እንደዚሁም በአግባቡ በተግባር ላይ ለማዋል ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ መረሣት የሌለበት ነጥብ ነው፡፡ እዚህ ላይ በትኩረት መታየት ያለበት የሟች ውርስ የሚከፈትበትን ስፍራ በሕግ መወሰኑ የማችን ውርስ አፈጻጸም ስርዓት አስመልክቶ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት ትልቅ ጠቀሜታ እንዳለውና የሟች ውርስ የሚከፈትበት ስፍራ በውርሱ ምክንያት የሚነሱ ክርክሮችን ለማየት የግዛት ክልል ስልጣን ያለውን ፍርድ ቤት ለመለየት አስፈላጊ እንደሆነ በእኛም አገር የዚህን ነጥብ አስፈላጊነት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 23 ድንጋጌዎች በአብነት ለማየት ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ የሟች

ውርስ መከፈት ጉዳይ የሚደነግግ ግልጽ የሕግ ድንጋጌ ማስቀመጡ ተገቢ ሲሆን የሕጉን ድንጋጌ መንፈስና ይዘት የወጣበትን ዓላማ ተረድቶ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡

2.2.2 <u>ከሟች ለወራሾቹ ሊተላለፉ የሚችሉና ሊተላለፉ የማይችሉ መብትና ግዴታዎች</u>

በመጀመሪያው ምእራፍ እንደተመለከተው የውርስ ሕግ ዋናው አላማና ግብ የሟች መብትና ግዴታዎች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፍበትን ስርዓት መልክ ማስያዝ ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሟች የነበረው መብት እና ግዴታ በሙሉ ወደ ወራሾቹ ይተላለፋል ማለት አይደለም፡፡ በፍትሐብሔር ሕጋችን ለሟች ወራሾች የሚተላለፉት የሟች መብቶችና ግዴታዎች በሟች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የማይቀሩት ብቻ መሆናቸው በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ይህንንም ፅንሰ ኃሣብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 826 ንዑስ አንቀፅ 2 ’’ በሟች መሞት ምክንያት ተቋርጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አንቀጽ ደንቦች መሠረት በውርስ ውስጥ የሚገኙት የሟች መብቶችና ግዴታዎች ለወራሾቹ እና የኑዛዜ ባለስጦታዎች ይተላለፋሉ’’ በማለት በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

ከዚህ የሕግ ድንጋጌ የምንረዳው በሟች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የሚቀሩ መብቶችና ግዴታዎች ወደ ወራሾቹ ሊተላለፉ እንደማይችሉ ነው፡፡ እነዚህ በሟች መሞት ምክንያት ተቋርጠው የሚቀሩ መብትና ግዴታዎች ምንድን ናቸውሕ የሚለውን ጥያቄ ስንጠይቅ ሟች በግሉ ብቻ ሊጠይቃቸው እና ሊጠቀምባቸው የሚችሉ መብቶች /Personal rights/ እና ሟች በግሉ ሊፈጽማቸው የሚገቡ ግዴታዎች /Personal obligations/ ናቸው፡፡ የሟች ግላዊ መብቶችና ግዴታዎች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለምሣሌ ሟች በሙያው በመንግስት መስሪያ ቤት ወይም በአንድ የግል ድርጅት ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ ቢሆን የሟቹ የመሥራት መብት ወራሾቹ ከእሱ ጋር ተመሣሣይ በሆነ ሙያ የሰለጠኑ ቢሆኑም እንኳን ለወራሾቹ በውርስ የሚተላለፍ አይደለም፡፡ እንደዚሁም ሟች ከልጆቹ ወይም ከዘመዶቹ የነበረው ቀለብ የመጠየቅ መብት ሟች ሲሞት የሚቋረጥና ለወራሾቹ ሊተላለፍ የማይችል መብት ነው፡፡ በሌላ በኩል ሟች በግል ችሎታው ለመፈፀም የገባቸው ግዴታዎች፣ ወራሾቹ በዚያ ሙያ ከእሱ የበለጠ ችሎታ እና ትምህርት ቢኖራቸውም እንኳን ሟች በግሉ ለመፈፀም የገባውን ግዴታ እነርሱ ተክተው እንዲፈጽሙ አያስገድዳቸውም፡፡ ይህም አንድ የህክምና ዶክተር ወይም ጠበቃ በሙያው ለመፈፀም የገባውን ግዴታ እሱ ሲሞት ወራሾቹ ዳክተሮች ወይም ጠበቃ ቢሆኑም እንኳን ሟች በገባው የውል ግዴታ እነርሱ ወርሰውና ተተክተው እንዲፈጽሙ መጠየቅና ማስገደድ አይችልም፡፡ ስለዚህ ከሟች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፉ መብትና ግዴታዎችን ለመለየት መብትና ግዴታዎቹ በሟች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ጥያቄ በማንሣት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሟች በውል ወይም በሕግ መሠረት ያገኘው የይዞታ መብት በውሉ ወይም በሕግ በተገለፀው የጊዜ ገደብ እስከሚደርስ ድረስ በአንድ ንብረት

የመጠቀም መብት ሙሉ ወይም ሌጣ የንብረት ባለቤትነት፣የአክሲዮን፣ የንግድ መደብር እና የሌሎች የንግድ ማህበር ድርሻዎች ሟች ከሌሎች ሰዎች ሊጠይቀው የሚችል የገንዘብ እዳና በውል መሠረት የሚፈፀም ግዴታ እንደዚሁም ሌሎች አበዳሪዎች ከእሱ የሚጠይቁት የገንዘብ እዳና በሟች መሞት ምክንያት የማይቋረጥ የውል ግዴታ ለሟች ወራሾች የሚተላለፉ የሟች መብትና ግዴታዎች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሟች ወራሾች የውርስ ንብረት ክፍል ናቸው በማለት የሟች ወራሾች ጥያቄ ማንሣት የማይችሉባቸውን የካሣና የጡረታ ገንዘብ ክፍያዎች እንደዚሁም በሞት ጊዜ ሊከፈል ስለተገባ የህይወት ኢንሹራንስ ክፍያ ገንዘብ በምን መልኩ ለሟች ወራሾች እና የሟች ወራሽ ላልሆነ ሰዎች ሊተላለፉ እንደሚችሉ ገዥነት ያላቸውን ደንቦች ደንግጓል፡፡ እነርሱንም ከዚህ በመቀጠል በዝርዝር እንመለከታቸዋለን፡፡

2.2.3. <u>ስለሟች የውርስ ንብረት የተደነገጉ፣ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

*ሀ.* <u>የጡረታና ካሣ ክፍያ</u>

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 828 ድንጋጌ ስንመለከት ’’በሞት ምክንያት ለሟቹ ዘመዶች ወይም ባል ወይም ሚስት የሚሰጡ ጡረታዎች ወይም ካሣዎች የውርሱ ሀብት ክፍል አይሆኑም’’ ይህን የሕግ ድንጋጌ መንግሥት የሟች ንብረት ክፍል እንዳይሆኑ በፖሊሲ ደረጃ ውሣኔ ከሰጠባቸው አንደኛው የጡረታና የካሣ ክፍያ መሆኑን የሚያሣይ ሲሆን የሕጉን ድንጋጌ ይዘት በዝርዝር ስንመለከተው የሕጉ ተፈጻሚነት ሦስት ነገሮችን ሊዳስስ እንደሚችል ያስገነዝበናል፡፡

የመጀመሪያው ለሟቹ ዘመዶች ወይም ባል ወይም ሚስት የሚሰጡ ጡረታዎች የውርስ ሀብት ክፍል አይሆኑም በማለት የፍትሐብሔር ሕጉ ይደነግጋል፡፡ ይህ የሕግ ድንጋጌ በመንግስት የማህበራዊ ጠዋስትና እና ድጐማ ፖሊሲ መሠረት የአገሪቱ ሕግ ስለሚፈቅድላቸው ለተጧሪዎች የሚከፈልን የጡረታ አበል የሟች ወራሾች እንደ ውርሱ ንብረት ክፍል በመቁጠር ለእነርሱ እንዲሰጣቸው መጠየቅ እንደማይችሉ በግልጽ ገደብ ያደረገ ድንጋጌ ነው፡፡

ሟች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ለጡረታ አበል ክፍያ የሚያበቃ ግልጋሎት ሰጥቶ በሞት ቢለይ አካለ መጠን ላላደረሱ ልጆቹ ለሚስቱና ለወላጆቹ የሚከፈለውን የጡረታ አበል የሟች ወራሾች መካፈል ይገባናል የሚል ክርክር እንዳያቀርቡ የሕጉ ድንጋጌ በማናቸውም መልክ የሚከፈል የጡረታ ክፍያ የውርስ ንብረት ክፍል አለመሆኑን በመደንገግ ወራሾች የጡረታው ክፍያ ለእኛ ይገባል የሚል ጥያቄ እንዳያቀርቡ ግልጽ የሆነ ክልከላ አድርጓል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ሟች በመሞቱ ምክንያት የሚከፈሉ የካሣ ክፍያዎችም እንደዚሁ የውርስ ንብረት ክፍል እንዳልሆኑ ተደንግጓል፡፡ ሟች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የሚተዳደር ድርጅት

ሠራተኛ ቢሆንና በስራው ላይ እያለ ሟች ለሚደርስበት የሞት አደጋ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅና በድርጅቱ የህብረት ስምምነት መሠረት ለሟች ዘመዶች ሐቤተሰቦችሐ የሚከፈል የካሣ ክፍያ ቢኖር ይህ የካሣ ክፍያ የውርስ ሀብት ክፍል አይሆንምዕዕ እንደዚሁም ሟች በአደጋ ምክንያት በሞት በመለየቱ ከውል ውጭ ስለሚመጣ ሀላፊነት በሕጉ በተደነገገው መሠረት ለደረሰው አደጋ ሀላፊ የሆነ ሰው ሟች በመሞቱ ምክንያት ለተጎጅው ባል ወይም ሚስት እንደዚሁም ለልጆቹና ለወላጆቹ በመተዳደሪያ እረገድ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሣ የመክፈል ሀላፊነት ያለበት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2095ሐ1ሐ ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት የሟች ባል ወይም ሚስት፣ ልጆቹና ወላጆቹ በየራሣቸው ስም የአደጋው ሀላፊ ከሆነው ሰው የተቀበሉት የካሣ ገንዘብ ወራሾቹ ለእኛ ሊሰጠን ይገባል የሚል ጥያቄ ማንሣት እንደማይችሉ የሕጉ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡

ስናጠቃልለው የጡረታና የካሣ ክፍያዎች በሟቹ መሞት ምክንያት የሚከፈሉ ቢሆኑም የውርስ ንብረት ክፍል ባለመሆናቸው ወራሾች የይገባናል ጥያቄ ሊያቀርቡባቸው የማይችሉ መሆናቸው በሕጉ ድንጋጌ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ የህጉ ድንጋጌ መንፈስና ሕግ አውጭ ሊደርስበት ያሰበውን ግብ በሟች መሞት ምክንያት ለባል፣ ለሚስት ፣ ለልጆቹና ለወላጆቹ የሚከፈል የጡረታ እና የካሣ ክፍያ ሟችን ከመውረስ መብት ጋር የተያያዘ ሣይሆን የራሱ የሆነ የፖሊሲ ውሣኔና የራሱ የሆነ ምክንያት ያለው በመሆኑ በሌሎች ሕጐች አፈጻጸሙ ስለሚሸፈን የሟች ወራሾች የወራሽ መብት ስላላቸው ብቻ የጡረታና የካሣ ክፍያ የይገባናል ጥያቄ ሊያቀርቡበት የማይችሉ መሆኑን በመገንዘብ በአተገባበሩ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

ለ. <u>በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ</u>

በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት አንድ ሰው ከኢንሹራንስ ከፋይ ድርጅት ጋር እሱ ሲሞት ለተጠቃሚው እንደሚከፈልለት በመስማማት የሕይወት ኢንሹራንስ ውል መግባት ይችላል፡፡ ይኸ አይነት የኢንሹራንስ ውል በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 692/2 በግልጽ የተቀመጠ ነው፡፡ ሟች የኢንሹራንስ ውሉን በሚዋዋልበት ወቅት በኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ የሚሆነውን ሰው በስም ለይቶ ወይም የኢንሹራንስ ውሉን ለወራሾቹ ጥቅም የገባ መሆኑን በግልጽ አስፍሮ ወይም የኢንሹራንሱን ተጠቃሚ ሣይገልጽ እና ኢንሹራንሱን ውል ለማን ጥቅም ሲል እንደገባ ምንም ፍንጭ ሣይተው የህይወት ኢንሹራንስ ውል የሚዋዋልበት ሁኔታ አለ፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረገው የህይወት የኢንሹራንስ ውል ላይ ወራሾቹ ምን መብት አላቸውሐ የሟች ወራሾች መብት አለን ብለው ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉት መቼ ነውሐ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827 መልስ ለመስጠት የሞከረ ቢሆንም ጉዳዩ አከራካሪና አወዛጋቢ መሆኑን ሙሉ በሙሉ አላስቀረውም፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827(1)፣

ሟቹ ተጠቃሚውን ያልወሰነ እንደሆነ ወይም ኢንሹራንሱ ለሟቹ ወራሾች ጥቅም የተደረገ እንደሆነ ሟቹ በፈረመው ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል አፈጻጸም የሚከፈሉ ገንዘቦች የውርስ ንብረት ክፍል ይሆናሉ’’

በማለት የሚደነግግ ሲሆን፣ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ ከተመለከተው ውጭ በኢንሹራንስ ውሉ የተገለፀ ተቃራኒ ነገር ካለ ግን በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ የውርስ ንብረት ክፍል እንደማይሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/2/ ተቃራኒ ሁኔታ ሲኖር የውርሱ ኃብት ክፍል አይሆኑም በማለት ደንግጓል፡፡ ይህ የሕግ ድንጋጌ ሟች ሲሞት ስለ ሕይወት ኢንሹራንስ ውል በገባው ግዴታ መሠረት የኢንሹራንስ ድርጅቱ የሚከፍለው ገንዘብ ለሟች ወራሾች ሊሰጥና የውርሱ ንብረት ክፍል ሊሆን የሚችለው ከሁለቱ አንደኛው መሠረታዊ ሁኔታ ሲሟላ ነው፡፡

የመጀመሪያው ሟች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን የተዋዋለው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን በውሉ ላይ በግልጽ ሀሣቡን አስፍሮ እንደሆነ ነው፡፡ ሟች በስም ሣይዘረዝር የኢንሹራንሱን ውል የገባው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን ጠቅለል ባለ አነጋገር ሀሣቡን ከገለፀ ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ ለተለየ ተጠቃሚ ጥቅም ማድረግ እንደሚቻል በንግድ ሕግ ቁጥር 702/1/ የተደነገገ በመሆኑና ሟች ወራሾቹን የኢንሹራንስ ልዩ ተጠቃሚዎች መሆናቸውን በመግለጽ የኢንሹራንስ ውል ከገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/1 በሚደነግገው መሠረት የሟች ውርስ ከተከፈተ በኍላ የሟች ወራሽ መሆናቸውን በአጥጋቢ ማስረጃ አረጋግጠው የቀረቡ የሟች ወራሾች በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ እንደ አንድ የውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ ይከፋፈላል፡፡

ሁለተኛው በፍትሐብሔር ሕጉ የህይወት ኢንሹራንስ ውል ክፍያ የሟች ውርስ ንብረት ክፍል ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሟች የኢንሹራንስ ውሉን የተዋዋለው ለማን ጥቅም እንደሆነ ያልገለፀ እንደሆነና የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ፍንጭ ያልሰጠ እንደሆነ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ገንዘብ የውርሱ ንብረት ክፍል እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ ደንግጓል፡፡ የፍትሐብሕር ሕጉ ሟች የኢንሹራንስ ውሉን የገባው ለወራሾቹ ጥቅም መሆኑን ባይገልጽ እና ለሌላ ተጠቃሚ መሆኑን ሣያመለክት በክፍት ቢተወው ምን ይደረጋል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የተወሰደው አቋም በኢንሹራንስ ውሉ ላይ ተጠቃሚው ካልተገለፀ ወይም ካልተመለከተ በውሉ መሠረት የሚከፈለውን ክፍያ እንደ ውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ ለወራሾች ማከፋፈል ይገባል የሚል ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ የተደነገገው እንዳለ ሆኖ በዚሁ ጭብጥ ላይ የንግድ ሕጉ የወሰደው አቋም ከፍትሐብሔር ሕጉ የተለየ መሆኑን ከንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት እንችላለን፡፡ የንግድ ሕግ

ቁጥር 701 ድንጋጌዎች ስንመለከት፣ በመርህ ደረጃ ለሞት የሚደረግ ኢንሹራንስ ለአንድ የተለየ ተጠቃሚ ሊደረግ እንደሚችል የንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ የደነገገ ሲሆን፣ የንግድ ሕጉ ቁጥር 701/2/ በበኩሉ፣

‹ስማቸው በውሉ ላይ ተለይቶ ባይጠቀስም፣

ሀ/ ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ከተፈፀመ በኑላም ቢሆን እንኳን ውል የፈፀመው ባል ወይም ሚስት፣

ለ/ የኢንሹራንሱ ውል ሲፈፀም የተወለዱት የኢንሹራንስ ውል ፈራሚ ሰው ልጆች ተለይተው የታወቁ ተጠቃሚዎች ተብለው ይጠራሉ’’

በማለት ይደነግጋሉ፡፡

ይህ የንግድ ሕግ ድንጋጌ ከፍትሐብሕር ሕግ ቁጥር 827/1/ ጋር መሠረታዊ ልዩነት ያለው ሲሆን ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች በአፈጻጸምም ወቅት ሆነ በይዘታቸው እርስ በርሣቸው የሚቃረኑ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842 መሠረት የሟች ልጆች የሟች የመጀመሪያ ወራሾች ሲሆኑ ከውርሱ የሚደርሣቸው ድርሻም እኩል ነው፡፡ የንግድ ሕጉ ከሟች ልጆች መካከል የኢንሹራንስ ውሉ ሲፈፀም የተወለዱትን ብቻ የኢንሹራንሱ ውል ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ሲደነግግ የፍትሐብሔር ሕጉ የሟች ወራሾች በኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚው ካልተገለፀ በኢንሹራንስ ውል መሠረት በሚከፈል ገንዘብ ላይ የወራሽነት መብታቸው እስከፈቀደ ድረስ ድርሻ እንዳላቸው ይደነግጋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕጉ የሟች ወራሾች የሟች ልጆች ብቻ ሣይሆኑ ተወላጆቹ ወይም እነሱ ከሌሉ ወላጆቹ ወይም የእነርሱ ተተኪዎች እንደሚሆኑ ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ይኖሩታል፡፡ በሌላ በኩል በፍትሐብሔር ሕጋችን ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን የመውረስ መብት የላቸዉም፡፡ ይህም በመሆኑ

- በመጀመሪያ ደረጃ የኢንሹራንሱ ውል ሲፈጸም በተወለዱ እና ከዚያ በኑላ በተወለዱ የሟች ልጆች መካከል፣
- በሁለተኛ ደረጃ በሟች ሚስት ወይም ባል፣ በሟች ልጆች መካከል፣
- በሶስተኛ ደረጃ በሟች ሚስት ወይም ባልና በሟች ወራሾች መካከል፣

የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ መጠነ ሰፊ ክርክር መነሣቱ የማይቀር ነው፡፡ እነዚህም የሚከራከሩት በየበኩላቸው ክራክራቸውን የሚደግፈውን የፍትሐብሔር ወይም የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ነው፡፡

ለምሣሌ አምሣሉ የተባለ ሰው የህይወት ኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ ማን እንደሆነ ሣይገልጽ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት ጋር ብር 20000/ሃያ ሽህ ብር/ እሱ ሲሞት የሚከፈል የመድን ውል ተዋውሏል፡፡ እሱም አዜብ የተባለች ሚስት አለችው፡፡ ውሉን ከመዋዋሉ በፊት ቢኒያም አምሣሉ የተባለ ልጅ ወልዷል፡፡ ውሉን ከተዋዋለ ከሶስት ወር በኋላ ደግሞ ጽጌ አምሣሉ የተባለች ልጅ ወልዷል፡፡ አምሣሉ ከሞተ በኋላ ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት ሊከፈለው የሚችለውን ገንዘብ አስመልክቶ የፍትሐብሔር እና የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች እየተጠቀሱ መጠነ ሰፊ ክርክር ሊያነሱ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ ቢኒያም አምሣሉና ፅጌ አምሣሉ በወኪላቸው አማካኝነት፣ አባታችን የኢንሹራንስ ውል ሲገባ ተጠቃሚዎችን ያልገለፀ ስለሆነ፣ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት መከፈል ያለበት ብር 20000 በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ በሚደነግገው መሠረት የአባታችን የውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነ፣ በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ደግሞ ሚስት ባሏን ባል ሚስቱን እንዲወርሱ ስለማይፈቅድ፣ የኢንሹራንስ ገንዘቡ የሟች አባታችን ወራሽ ለሆነው ለእኛ ለልጆቹ ይገባል ብለው ቢጠይቁ የሟች ሚስት ወሮ አዜብ በበኩላቸው በንግድ ሕግ ቁጥር 701/1/ መሠረት በኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚው ባይገለፅም እና ጋብቻው የተደረገው የኢንሹራንስ ውል ከተፈረመ በኳላ ቢሆንም እንኳን፣ ሚስት የኢንሹራንሱ ገንዘብ ተጠቃሚ መሆን እንደሚችሉ ስለሚደነግግ፣ ሟቹ ባሌን መውረስ በሕግ ባይፈቀድልኝም፣ እሱ የገባው ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ ከመሆን ልታገድ አይገባኝም በማለት ትከራከራለች፡፡በሁለተኛ ደረጃ ወ/ሮ አዜብና ቢኒያም አምሣሉ፣ ፅጌ የኢንሹራንስ ውሉ ከተፈረመ በኋላ የተወለደች ስለሆነ፣ በንግድ ሕጉ ቁጥር 701 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚ መሆን አትችልም የሚል ክርክር ቢያነሱ ፅጌ አምሣሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ ድንጋጌ በመጥቀስ፣ በኢንሹራንስ ውሉ መሠረት የሚከፈለው ክፍያ የሟች ውርስ ንብረት ክፍል ስለሆነና እኔ የሟች ወራሽ ስለሆንኩ ድርሻየ ይገባኛል በማለት ትከራከራለች፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ ደጋፊ የሆኑት የንግድ ሕግ ድንጋጌ ወይም የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ እየተጠቀሰ ክርክሩ ሊቀጥል ይችላል፡፡ በሌላ ሁኔታ ሟች አምሣሉ ጽጌንና ቢኒያምን ባይወልድና ወራሾቹ እናት እና አባቶቹ ቢሆኑ በአዜብ እና በአምሣሉ እናትና አባቶች መካከል የፍትሐብሕር ሕጉ እና የንግድ ሕጉ ድንጋጌ በዋቢነት እየተጠቀሱ ክርክሩ እንደሚቀጥል መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ እና በንግድ ሕግ ቁጥር 702/2/ መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በትርጉም ለመፍታት የተለያዩ ሀሣቦች ሲቀርቡ ይስተዋላሉ፡፡ በተለይ ሁለቱም ሕጎች ማለትም የፍትሐብሔር ሕጉም ሆነ የንግድ ሕጉ ከመስከረም 1 ቀን 1953 ጀምሮ ሥራ ላይ እንዲውሉ የታወጁ መሆናቸው ሲታይ በአተረጓጐም ረገድ ያለውን ችግር ያባብሰዋል፡፡ ይህም በመሆኑ የንግድ ሕጉ ስለ ሕይወት ኢንሹራንስ ውል ክፍያና ስለ ህይወት ኢንሹራንስ ውል ተጠቃሚ የሚደነግግ በመሆኑ ከጠቅላላው የውርስ ሕግ ድንጋጌ ማለትም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ የበለጠ ተፈጻሚነት ሊሰጠው የሚገባው ለንግድ ሕግ ቁጥር 701/2/ ነው የሚል ነው፡፡

ከላይ የቀረበውን ሀሣብ የማይቀበሉ ወገኖች በበኩላቸው የሟችን የውርስ ሁኔታና የውርስ ንብረት ክፍል የሚወስኑት ድንጋጌዎች በፍትሐብሔር ሕጉ እንጅ በንግድ ሕጉ ተካትተው አይገኙም፡፡ ስለዚህ የውርስን ጉደይ ስንመለከት ብልጫ ሊሰጠው የሚገባው የፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ እንጅ የንግድ ሕጉ ድንጋጌ አይደለም የሚል ነው፡፡

ሁለቱ የሕግ ድንጋጌዎች አቻችለን በስራ ላይ ማዋል እንችላለን፡፡ የሟች ወራሾች በፍትሐብሔር ሕጉ የተሰጣቸው መብት ሣይጣስ የሟች ሚስት ወይም ባል በንግድ ሕጉ የተሰጣቸው መብት ሣይጣስ የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘቡን በተመለከተ ብቻ ሚስት ወይም ባል ከሟች ወራሾች ጋር የጋራ ተጠቃሚ ማድረግ እየቻልን አንደኛውን ጠቅሞ ሌላውን በሚጐዳ ሁኔታ ሕጉን መተርጐም የለብንም የሚል አቋም የሚያራምዱ ያሉ ሲሆን አከፋፈሉን በተመለከተም የተለያየ ሀሣብ ይሰነዘራል፡፡ ለምሣሌ ሚስት ወይም ባል ግማሹን መውሰድ አለባቸው የሚል ያለ ሲሆን በሌላ በኩል በህይወት ኢንሹራንስ ውል መሠረት የተከፈለውን ገንዘብ ለመካፈል ባል ወይም ሚስት እንደ ሟች አንድ ወራሽ ተቆጥረው ከወራሾቹ ጋር እኩል መካፈል አለባቸው የሚል ሀሣብ አለ፡፡

ሟች የህይወት ኢንሹራንስ ውሉን ሲዋዋል ተጠቃሚውን ባልገለፀበት ጊዜ ከላይ የተነሣው የሕግ አተረጓጐምና የአፈጻጸም ችግር አለ፡፡ የሕግ አውጭ ሀሣብ ምን እንደሆነ ለመረዳት ሕጉ ከመውጣቱ በፊት ሕግ አውጭው በዚህ ጉዳይ ያደረገውን ውይይት ይዘት ጭምር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የጽሁፍ አቅራቢ ይህንን እድል አላገኘም፡፡ ስናጠቃልለው በሞት ጊዜ የሚከፈል የህይወት ኢንሹራንስ ገንዘብ ተጠቃሚው በግልጽ በተጠቀሰበት ጊዜ ማለትም ለሌላ ሰው ክፍያ ተብሎ ውሉ ከተገባ የሟች የውርስ ንብረት ክፍል አይሆንም፡፡ ይህንንም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 827/1/ እና የንግድ ቁጥር 701/1/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ የኢንሹራንስ ውሉ ለሟች ወራሾች ጥቅም የተደረገ መሆኑ በግልጽ በኢንሹራንስ ውሉ በተገለፀ ጊዜ ምንም ክርክር ሣይቀርብበት እንደ ሟች የውርስ ንብረት ክፍል ተቆጥሮ የሟች ወራሾች ገንዘቡን እንዲከፋፈሉት ይደረጋል፡፡ የኢንሹራንስ ውሉ ተጠቃሚው በግልጽ ያልታወቀ ሲሆን እና ለወራሾቹ ጥቅም የተደረገ መሆኑን የማይገልጽ ሲሆን ከላይ ባየነው መሠረት በንግድ ሕጉ እና በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌ መካከል የሚታየው ልዩነት አወዛጋቢና ለትርጉምም በር የሚከፍት ነው፡፡

# የመወያያ ጥያቄዎች

1. አሁን በስራ ላይ ያለውን የውርስ ሕግ አንቀጽ 827/1/ እና በንግድ ሕግ ቁጥር 702/2/ መካከል ያለውን ልዩነት ለመፍታት ዕርስዎ የትኛውን አተረጓጐም መርህ ይከተላሉ? ለምን? ተጠቃሚው በግልፅ ባልተገለፀ ጊዜ፣ በሞት ጊዜ የሚከፈል የኢንሹራንስ ውል ክፍያ የውርስ ንብረት ክፍል ማድረጉ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?
2. የአንዳንድ አገሮች የውርስ ህጎች ከሟች ወደ ወራሾች የተላለፉትን መብቶችና ግዴታዎች በጥቅሉ ሣይሆን በዝርዝር ያስቀምጣሉ። የእኛ ደግሞ <u>በሟች መሞት የማይቋረጡ መብትና ግዴታዎች </u>የሚል መስፈርት ብቻ ያስቀምጣል። ይኸ አቀራረፅ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?
3. በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 41 መሠረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብት የመንግስትና የህዝብ ነው። ሆኖም አርሶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች እና በግብርና መስክ የተሠማሩ ኢንቨስተሮች በህጋዊ መንግድ በያዙት መሬት ላይ ያላቸውን የመጠቀምና የይዞታ መብት፣ ቋሚ ተክሎችና ሌሎች ንብረቶች ለወራሾቻቸው የማስተላለፍ መብታቸው የፌዴራል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 80/1989 እና ይህንን መሠረት በማድረግ በክልሎች ምክር ቤት በወጡ ክልላዊ የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጆች የተሰጠው ዋስትና እና ጥበቃና የተጣለባቸውን ገደቦች በዝርዝር ያብራሩ። ይህንንም ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826/2/ ድንጋጌ አንፃር ይተንትኑ።
4. ባለሀብቶች በፌዴራል መንግስት የከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና የፌዴራል መንግስት የኢንቨስትመንት አዋጅን እንደገና ለመደንገግ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 280/1996 በአዋጅ ቁጥር 375/1996 እንደተሻሻለ መሠረት ያገኙትን የከተማ ቦታ ለወራሾቻቸው የማስተላለፍ መብታቸው በአዋጆቹና አዋጆቹን ለማስፈፀም የክልል መንግስታት ባወጧቸው ደንቦች የተሰጣቸው ዋስትና ጥበቃና የተጣለባቸው ገደቦች መኖራቸውን በዝርዝር ያብራሩ። ይህንንም ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 826/2/ ድንጋጌ አንፃር ያለውን እንድምታ ይተንትኑ።
5. የፌዴራል መንግስት የኢትዮጵያ ተወላጅ የሆኑ የውጭ ዜጎችን በትውልድ አገራቸው የተለያዩ መብቶች ተጠቃሚ ለማድረግ ያወጣው አዋጅ ቁጥር 270/1994 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣው ደንብ ቁጥር 101/1996 በውርስ ህጉ መሠረታዊ መርሆችና ድንጋጌዎች ላይ በግልፅ ውይም በተዘዋዋሪ ያደረገው ማሻሻያ አለ ብለው ያስባሉ? ለምን?

# ምዕራፍ ሦስት

# ለመውረስ ስለሚያስፈለግ ችሎታ

የዚህ ምዕራፍ ግብ፣

- ለመውረስ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች
- ለወራሽነት የማይገባ ነው ስለሚባሉ ምክንያቶች ግንዛቤ ማስጨበጥ ነው፡፡

## 3.1. ጠቅላላ

ሟችን ለመውረስ የሚቀርብ ሰው ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው የሚለውን ጭብጥ አንስተን ትንታኔ ከመስጠታችን በፊት የሟች ውርስ በኢትዮጵያ ሕግ በምን ሁኔታ ይፈጸማል የሚለውን ነጥብ በቅድሚያ ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡ የሟች ውርስ በኑዛዜው መሠረት እንደሚፈፀም እና ሟች ኑዛዜ ያልተወ እንደሆነ ውርሱ ያለ ኑዛዜ ለሕግ ወራሾቹ እንደሚተላለፍ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል ሟች በከፊል ንብረቱን በኑዛዜ ያወረሰ እንደሆነ በኑዛዜው ያላደላደላቸው ንብረቶች በመሉ ለሕግ ወራሾች ይተላለፋሉ፡፡ በአጠቃላይ የሟች ውርስ ያለኑዛዜ ወይም በኑዛዜ፣ በከፊል ያሉ ኑዛዜና በከፊል በኑዛዜ ሊፈጸም እንደሚችል፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 829 መሠረታዊ መርሆችን ደንግጓል፡፡

የሟች ወራሽ በመሆን ሊቀርቡ የሚችሉት የተፈጥሮ ሰው የሆነ አንድ ግለሰብ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች እና በኑዛዜ ተጠቃሚነት ሊቀርቡ የሚችሉ ድርጅቶችና ማህበራት ጠቅለል ባለ አነጋገር ሕጋዊ ሕልውና ያላቸው የሕግ ሰዎች /Legal persons / ናቸው፡፡ የተፈጥሮ ሰዎች ሟችን በሚወርሱበት ሥዓት ውርሱ ተፈጥሮአዊ የሆነ ውርስ Natural sucession እየተባለ እንደሚጠራ የብላክስ ሎው መዝገብ ቃላት ያመለክታል፡፡ የመውረስ ችሎታ /Capacity to succeed/ስንል፣ ሟችን በኑዛዜ ወይም ያለ ኑዛዜ ለመውረስ የሚቀርቡ የተፈጥሮ እና የሕግ ሰዎች /Legal persons/ በቅድሚያ ማሟላት የሚገባቸውን ሁኔታዎች በአጭሩ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ጽንሰ ሀሣብ ነው፡፡ በሟች ውርስ ለመካፈል ወራሽ የሚሆኑ ሰዎች አሟልተው መገኘት ያላበቸው ቅድመ ሁኔታ ምንድን ነው?

ወራሾች የተፈጥሮ ሰዎች በሆኑ ጊዜ ሟችን በኑዛዜም ሆነ ያለኑዛዜ ወራሽ ለመሆን ሁለት መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች እንደ መሠረታዊ መርህ ተቀምጠዋል፡፡ እነርሱም ሟች ውርስ ሲከፈት በሕይወት ያለ

መሆንና ሟችን ለመውረስ የማይገባ አለመሆን ነው። ወራሾቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች በሆኑ ጊዜ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 835 የተመለከተውን አሟልተው መገኘት አለባቸው።

ከላይ እንደተገለፀው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 የእኛን አገር የውርስ ፖሊሲ የሚያንፀባርቅ ሕግ በመደንገግ በተግባር ላይ አውሏል። አንዳንድ አገሮች የወራሾችን ዜግነት ሀይማኖት እና የትውልድ ሁኔታ ሳይቀር ለመውረስ መሠረታዊ ቅድመ ሁኔታዎች በማድረግ ሕጋቸውን ቀርፀዋል። አብዛኛዎቹ አገሮች ደገሞ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር እና በሟች ላይ ሆን ብሎ የግድያ ወንጀል አለመፈፀምን ለመውረስ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች መሆናቸውን ያሰምሩበታል።

ዜግነትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ሕግ በወራሽነት መብት ላይ የሚያስከትለው ልዩነት እንደሌለ ደንግጓል። ይህ ማለት ግን በንብረት ክፍያ ወቅት የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች በተመለከተ ከውጭ አገር ዜጐች ይልቅ ኢትዬጵያዊ ለሆኑ ወራሾች በቅድሚያ እንዲሰጡ በሕግ አልተደነገገም ማለት አይደለም። እንደሚታወቀው የውጭ አገር ሰው በመንግስት ልዩ ትእዛዝ መሠረት ካልሆነ በቀር በኢትዮጵያ የማይንቀሣቀስ ባለሀብት ሊሆን አይችልም። ይህም በፍሐሕሐቁ 390 ተደንግጓል። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1089 ከወራሾቹ መካከል አንዳንዶቹ የኢትዮጵያ ዜግነት አንዳንዶቹ ደገሞ የውጭ አገር ዜግነት ያላቸው የሆኑ እንደሆነ በኢትዮጵያ ያሉት የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች የሚቻል ቢሆን ኢትዮጵያዊ ለሆኑ ወራሾች ቅድሚያ ይሰጣሉ በማለት የደነገገው ከዚህ መሠረታዊ ፖሊሲ በመነሣት ነው።

ሆኖም የማይቻል በሚሆንበት ጊዜ የውጭ አገር ዜጐች ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሣቀስ ንብረት በወራሽነት ሊረከቡ እንደሚችሉ የሕጉ ድንጋጌ ያሣያል። የውጭ አገር ዜጐች በልዩ የኑዛዜ ስጦታ ወይም በውርስ ክፍያ ወቅት የማይንቀሣቀስ ንብረት ቢደርሣቸው ምን ይደረጋል የሚለውን ጥያቄ ስናነሣ ማንኛውም የውጭ አገር ዜጋ ያለ መንግስት ልዩ ትእዛዝ በቅን ልቦና የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብት ሆኖ ከተገኘ አግባብ ያላቸው ባለስልጣኖች በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያዊ ርስቱን እንዲያስተላለፍ ሊያስገድዱት የሚችሉበት ሁኔታ ያለ መሆኑ የፍሐብሐሕ. ቁ 391 ይደነግጋል።

ሆኖም ይኸ ድንጋጌ አገሪቱ ካወጣቻቸው የኢንቨስትመንት ህጐችና በትውልድ ኢትዮጵያ ስለሆነ ሌላ አገር ዜግነት ስላላቸው ኢትዮጵያ ተወላጆች አስመልክቶ ከወጣ አዋጅ ቁጥር 270/94 እና አዋጁን ለማስፈፀም ከወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 101/1996 ጋር በማገናዘብ ስራ ላይ ማዋል ይገባል። ከላይ ከተገለፁት የህግ ድንጋጌዎችና በኢንቨስትመንት ህጉ መብት የሌለው አንድ የውጭ ዜጋ በውርስ ያገኘውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሰው በሽያጭ ወይም በሌላ ሁኔታ እንዲያስተላልፍ ባለስልጣናት ሊጠይቁት ይችላሉ። ይህ የኢትዮጵያ ሕግ የውጭ አገር ሰው ኢትዮጵያ ውስጥ የማይንቀሣቀስ ንብረት

ባለሀብት እንዳይሆኑ ለመገደብ በፊት የወጣው ፖሊሲ አካል እንጅ የውጭ ዜጋ የወራሽነት መብት ለመገደብ የወጣ የሕግ ድንጋጌ አለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የውጭ አገር ዜጎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸውን የወራሽነት መብት ስንመለከተው ኢትዮጵያ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሳታስቀምጥ የውጭ ዜጎች በሕግ ወይም በኑዛዜ ወራሽነት እንዲካፈሉ በሯን በሰፊው የከፈተች አገር ሆና እናገኛታለን፡፡ አንዲት አገር የዜጎቿን መብትና የእራሷን ጥቅም የምታስከብረው እያንዳንዱ አገር ለሚወስደው እርምጃ ተመጣጣኝ ምላሽ በመስጠት እንደሆነ ከዓለም አቀፍ ሕግ እና አለም አቀፍ የግንኙነት መርሆች መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 3.2. ለወራሽነት ያልተገባ አለመሆን

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ መሠረት ሟች ሲሞት በህይወት የነበረ ሰው ሁል ጊዜ ሟችን ለመውረስ ችሎታ አለው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው፡፡ ሟች ሲሞት በህይወት የነበረ ሰው ሟችን ለመውረስ ማሟላት የሚገባው ሌላ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታ አለ፡፡ ይኸውም ሟችን ለመውረስ ያልተገባ አለመሆን ነው፡፡

ያለኑዛዜ ወይም በኑዛዜ ከሟች ውርስ ለመካፈል የሚመጡ ሰዎች ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙትና በሕጉ በግልጽ የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ያልፈፀሙ መሆናቸውን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሆኑ ተደንግጓል፡፡ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች እና ድርጊቶች በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች በዝርዝር እና በግልጽ ተመልክተዋል፡፡ ከእነዚህ ህጉ በግልጽ ካስቀመጣቸው ውጭ ያሉ ድርጊቶችን እና ምክንያቶችን በመጥቀስ ዳኞች አንድን ሰው ሟችን ለመውረስ ያልተገባህ ነህ በማለት ውሣኔ ሊሰጡ እንደማይችሉ፣ ይህንን በሚመለከት የተደነገጉት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች አመልካች የሕግ ድንጋጌዎች ሣይሆኑ አሣሪ እና አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን መገንዘብና ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሌላው በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ለወራሽነት ያልተገባ መሆን /unworthy of succeding the deceased/ እና ከውርስ መነቀል /Disherison/ የተለያየ የሕግ ጽንሰ ሀሣቦች መሆናቸውን ነው፡፡

ለወራሽነት ያልተገባ መሆን አንድ ሰው በሕግ እንዳያደርገው የተከለከለውን ድርጊት ፈጽሞ በመገኘቱ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ከሟች ውርስ እንዳይካፈል የወራሽነት መብቱን የሚያሣጣበት የሕግ መርህ ነው፡፡ ከውርስ መነቀል ግን በውርስ ሕግ ሟችን ለመውረስ ሙሉ ችሎታ ያለው ሰው ሟች ከውርሱ እንደማይካፈል በማሰብ ባደረገው የኑዛዜ ቃል መሠረት  ለሟች የኑዛዜ ቃል ዋጋ በመስጠትና በማስፈፀም ወራሽ የሆነው ሰው ከሟች ውርስ ውጭ እንዲሆን የማደረግበትን ሁኔታ የማያመለክት የሕግ ጽንሰ ሀሣብ ነው፡፡

ስለዚህ ሟችን ለመውረስ ያልተገባ መሆን ከውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የሚመነጭና ለአፈጻጸም መሠረቱ የሕጉ ድንጋጌ ሲሆን የውርስ መነቀል ምንጩ ሟች ያደረገው የኑዛዜ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱ የተለያዩ የሕግ ጽንሰ ሀሣቦች መሆናቸውን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ አንድ ሰው ከሟች ኑዛዜ ከውርስ የሚነቀልበትን ዝርዝር ሁኔታ በኑዛዜ ስለሚደረግ ውርስ የሚለውን ክፍል በምናይበት ጊዜ በሰፊው የምንመለከተው ይሆናል፡፡ በፍትሐብሔር ሕጋችን ሟችን ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ ምክንያቶች በሁለት ክፍሎች የተመደቡ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው ለመውረስ ያልተገባ ነው የሚያሰኙ የወንጀል ድርጊቶችን ፈጽሞ በፍርድ ጥፋተኛ መባልና መቅጣት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሕጉ በግልጽ የተመለከቱትን ሌሎች ተግባሮች መፈፀም ናቸው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ለመውረስ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ጉዳዬች ምንድን ናቸው?
2. ለወራሽነት ያልተገባ መሆን እና በውርስ መነቀል በሚሉት ፅንሰ ኃሣቦች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
3. የውጭ ዜግነት ያላቸው ሰዎች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በኢትዮጵያዊ ውርስ ተካፋይ እንደሆኑ መጋበዙ፣ ተገቢ ነው ብለው ያስባሉ?
4. በውርስ መከፈትና በውርስ ማጣራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?
5. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 ርእስና በይዘቱ አለመጣጣም አለበት ብለው ያስባሉ?
6. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 838 የፍትሐብሔሩን ጉዳይ በወንጀል ችሎት በሚሰጠው የቅጣት ውሣኔ ላይ ጥገኛ እንዳይሆን ማድረጉ ምን አይነት ጉዳት ያስከትላል ብለው ያስባሉ?
7. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 840/ለ/ ድንጋጌ የአማርኛው የእንግሊዘኛው ቅጅ የትኛው በተሻለ ሁኔታ ህግ አውጭው ሊደርስበት ያሰበውን ግብና አላማ ይገልፃሉ ብለው ያስባሉ? ለምን?
8. ሟች በተዘዋዋሪ መንገድ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 841 መሰረት ይቅርታ አድርጓል ለማለት ምን ምን ሁኔታዎች መሟላት አለባቸው?
9. የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 22305 ሚያዚያ 9 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከዚህ ሞጁል ጋር የተያያዘ ሲሆን ውሳኔው ትክክል ነው ብለው ያስባሉ? ለምን?

# ምዕራፍ አራት

# ሳይናዘዝ የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት አፈጻጸም

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ፡-

በሕይወት ዘመኑ ኑዛዜ ሳይተው የሞተ ሰው የውርስ ሥርዓት አስተዳደር እንዴት መሆን እንዳለበት በፍትሐብሔር ሕጉ የተደነገጉትን መሠረታዊ መርሆች ማሳየት፣

በዚህ ረገድ ፍርድ ቤት የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ሊፈቱ የሚችሉበትን መንገድ ማሳየት

## 4.1. ጠቅላላ መግቢያ

በጠቅላላው ስለ ውርስ ስናወራ ሟች ከሞተ በኋላ የውርስ ሥርዓት የሚፈፀመው ቢያንስ በሦሥት ዓይነት መንገድ ሊሆን እንደሚችል በፍትሐብሔር ሕጉ ተደንግጓል፡፡ ይኸውም ሟች በሕይወት ዘመኑ ስለ ውርስ ሥርዓትና ስለ ወራሾቹ የተወው ኑዛዜ ካለ፣ በሟች ኑዛዜ መሠረት / Testate Succession/ ፣ ሟች በሕይወት ዘመኑ በሞት በተለየበት ጊዜ ውርሱ ምን መሆን እንዳለበት የተወው ኑዛዜ ከሌለ ያለኑዛዜ በሚፈፀም የውርስ ሥርዓት / Intestate Succession/ ፣ ሟች በከፊል ኑዛዜ ከተወና ከፊል ንብረቱ እንዴት መከፋፈል እንዳለበት የተወው ኑዛዜ ከሌለ፣ ውርስ በከፊል በኑዛዜና በከፊል ያለ ኑዛዜ ሊፈፀም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ 829 ተደንግጓል፡፡

በመሠረታዊ መርህነት የኢትዮጵያ ሕግ፣ ሟች በሕይወት ዘመኑ የተወው ኑዛዜ ካለ የሟች የውርስ ሥርዓት በሟች የኑዛዜ ቃል መሠረት መፈፀም እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን ሟች በኑዛዜ ያላደላደላቸው ንብረቶች በሙሉ ለሥጋ ዘመዶቹ በውርስ ሕግ መሠረት ሊተላለፍ እንደሚችሉ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች ንብረቱን በሙሉ በኑዛዜ አደላድሎ ከሞተና ያለኑዛዜ የሚተላለፍ ምንም ዓይነት ንብረት ከሌለው

በውርስ ሕግ መሠረት ያለኑዛዜ ውርስ ለመፈፀም አይችልም፡፡ ሟች ስለ ውርስ ሥርዓት አፈጻጸምና ስለ ወራሾቹ የተወው በሕግ ውጤት ያለው ኑዛዜ በሌለበት ሁኔታ ውርሱ ያለኑዛዜ ይፈፀማል፡፡ ውርሱ ያለኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት እንዴት እንደሚፈፀምና እነማን የቀዳሚ ወራሽነት መብት እንዳላቸው፣ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ይወስናሉ፡፡

ከዚህ አንጻር ሲታይ የአንድ ሰው ውርስ ያለኑዛዜ በሚፈፀምበት ወቅት፣ ሦሥት ዓይነት የአወራረስ ሥርዓቶች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ፣ ስለውርስ ስርዓት የተጻፉ ፅሁፎች ያሣያሉ፡፡ የመጀመሪያው የተለመደ ተፈጥሮዓዊ አወራረስ / Natural Succession/ የሚለው ነው፡፡ የተፈጥሮ አወራረስ ሥርዓት የምንለው ውርሱ የሚፈፀመው በሁለት የተፈጥሮ ሰዎች መካከል የሆነ እንደሆነ ነው፡፡ ይኸም ማለት የሟች ወራሾች የሥጋ ዘመዶቹ የሆኑ የተፈጥሮ ሰዎች የሆኑ እንደሆነ ውርሱ የተለመደ ወይም Natural Succession፣ ይባላል፡፡ የፍትሐብሔር ሕጋችን በአብዛኛው ያለ ኑዛዜ የሚደረግ ውርስ፣ የተለምዶ የውርስ ሥርዓትን / Natural Succession/ እንዲከተል የሚያደርጉ በርካታ የሕግ ድንጋጌዎችን ይዞ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህ የሕግ ድንጋጌዎችም የሟችን ቀጥታ ወራሾች ወይም በሟች ውርስ በተተኪነት ሊካፈሉ የሚችሉትን እነማን እንደሆኑ በሰፊው በመዘርዘር፣ የሟች የውርስ ሥርዓት ተፈጥሯዊ የሆነው የሥጋ ዝምድና መሠረት በማድረግ እንዲከናወን ሰፊ በር የሚከፍት ነው፡፡

ሁለተኛው የአወራረስ ሥርዓት ያልተለመደ አወራረስ ወይም Irregural Succession የሚባለው ነው፡፡ ያልተለመደ የውርስ ሥርዓት የምንለው ሟች በሕይወት ዘመኑ የተወው፣ ኑዛዜ ከሌለና በውርስ ሕግ መሠረት ወራሽ ሊሆን የሚችል የሥጋ ዘመድ ከሌለው፣ የሟች ወራሽ የአገሪቱ መንግሥት ወይም፣ በሕግ በግልፅ የተጠቀሰ የበጐ አድራጐት ድርጅት እንደሆን፣ የአንዲት አገር ሕግ የሚፈቅድ ሲሆንና ውርሱም በዚሁ መሠረት የሚፈፀም ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡የእኛ ሕግ ኑዛዜ ሣይፈጽም የሞተ ሰው በዘመዶቹ እንዲወረስ ሰፊ እድል የሚሰጥ ቢሆንም፣ ሟች በውርስ ሕግ መሠረት ሊወርሰው የሚችለው ዘመድ ከሌለው የሟች ሐብት በወራሽነት ለመንግሥት ሊተላለፍ እንደሚገባው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 852 በግልፅ ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም ሟች በሕይወት ዘመኑ ኑዛዜ ካልተወና፣ በውርስ ሕግ መሠረት ለመውረስ የሚችል ዘመድ የሌለው እንደሆነ መንግሥት የሟች ወራሽ ሆኖ እንደሚቀርብና የሟችን ንብረት እንደሚረከብ፣ በዚህ ዓይነት መንገድ የአንድ ሰው የውርስ ሥርዓት ሲፈፀም ያልተለመደ የአወራረስ ሥርዓት ወይም Irregular Succession በሚባል እንደሚጠራ፣ ግንዛቤ መያዝ አለበት፡፡

ሶሥተኛው የውርስ ሥርዓት ክፍት የውርስ ሁኔታ ወይም vacant Succesion የሚባለው ነው፡፡ የአንድ ሰው ውርስ ክፍት ( Vacant ) ነው የሚባለው ሟች ኑዛዜ ካልተወና፣ በውርስ ሕግ መሠረት ወራሽ ሊሆን የሚችል ዘመድ ከሌለው እንደዚሁም፣ የአገሪቱ የውርስ ሕግ ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ ንብረቱ

ለማን መተላለፍ እንደሚገባው ሣይደነገግ ክፍት አድርጐ የተወው እንደሆነ ነው፡፡ በእኛ አገር ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ መንግሥት በወራሽነት፣ እንደሚቀርብ ግልፅ የሕግ ድንጋጌ በመኖሩ የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ወይም (Vacant Succession) የሚሆንበት አጋጣሚ የለም፡፡ ሆኖም የአንዲት አገር ሕግ ሟች ወራሽ ዘመድ በሌለው ጊዜ የሟች ንብረት ለማን መተላለፍ እንደሚገባው የሚደነገግ ካልሆነ የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ይሆናል ንብረቱም ለብክነት የሚዳረግ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የውርስ ሕግ በሚረቀቅበትም ጊዜ ሆነ ሕጉ በሚሻሻልበት ወቅት የሟች ውርስ ወራሽ አልባ ሆኖ እንዳይቀር ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ የሥጋ ዝምድናን /ትውልድን/ መሠረት አድርጐ የሚፈፀመው የሟች ውርስ ሥርዓት በሥዕላዊ

<table>
<tr><td colspan="4">የእናት መስመር</td><td colspan="4">የአባት መስመር</td></tr>
<tr><td>ወንድ ቅ.አያት እና ተተኪዎ ቻቸው</td><td>ሴት ቅ.አያት እና ተተኪዎ ቻቸው</td><td>ወንድ ቅ.አያት እና ተተኪዎ ቻቸው</td><td>ሴት ቅ.አያት እና ተተኪዎ ቻቸው</td><td>ወንድ ቅ.አያት እናተተኪዎ ቻቸው</td><td>ሴት ቅ.አያት እናተተኪዎ ቻቸው</td><td>ወንድቅ. አያት እና ተተኪዎ ቻቸው</td><td>ሴት ቅ.አያት እናተተኪ ዎ ቻቸው</td></tr>
<tr><td colspan="2">የሟች ወንድ አያት እና ተተኪዎቻቸው</td><td colspan="2">የሟች ሴት አያት እናተተኪዎቻቸው</td><td colspan="2">የሟች ወንድ አያት እናተተኪዎቻቸው</td><td colspan="2">የሟች ሴት አያት እናተተኪዎቻቸው</td></tr>
<tr><td colspan="4">አባት እና ተተኪዎቻቸው</td><td colspan="4">እናትና ተተኪዎቻቸው</td></tr>
<tr><td colspan="8">ሟች</td></tr>
<tr><td colspan="4">የሟች ልጆች እና ሌሎች ተወላጆች</td><td colspan="4">1ኛ ደረጃ ወራሾች</td></tr>
</table>

መግለጫ መልክ ተሰርቶ ሲታይ የሚከተለው መልክ ይኖረዋል፡፡

## 4.2. ተተኪ ወራሽ

የተተኪነት ወራሽ ስለመሆን በተመለከተ ለሰዎች አሁንም የመከራከሪያ ነጥብ እንደሆነ የደቡብ ጐንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 04033 ታህሣሥ 27 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የክርክሩ መነሻ መምህር ሞገስ አለነ በጠበቃ እያታገዙ ያቀረቡት ማመልከቻ ሲሆን ይዘቱም ወላጅ እናቴ ወ/ሮ እማዋይ አለመኔ 1966 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ተለይታለች፡፡ የእናቴ እናት የሆነችው ወ/ሮ ሁሉአገር ውብቴ ደግሞ በ1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት

ተለይተዋል፡፡ አያቴ ወ/ሮ ሁሉአገር ውብቴ በወረታ ከተማ የሠራችው መኖሪያ ቤት ያላት ሲሆን ቤቱን የእናቴ እህት የሆነችው ወ/ሮ አሰፉ አዳነ ከባለቤታቸው ከዶክተር ሞገስ አለነ ጋር በመሆን በውርስ የወሰዱት ስለሆነ እኔ አያቴን በእናቴ በወ/ሮ እማዋይ አለምኔ ምትክ በመሆን ወራሽ ስለሆንኩኝ የቤቱ ግምት ግማሹ ይገባኛል በማለት ክስ ያቀረባል፡፡ በዚህ ጉዳይ አንደኛ ተከሣሽ የሆነውንና የወ/ሮ አሰፉ አዳነ ባለቤት የሆኑት ዶ/ር ሞገስ ጥሩነህ በጠበቃቸው አማካኝነት ባቀረቡት መልስ ሟችን ለመውረስ በመጀመሪያ የሟች ውርስ ሲከፈል በሕይወት መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ የእሱ እናት ወ/ሮ ሁለአገር ውብቴ ከመሞታቸው ከሃያ ሶስት አመት በፊት ቀድማ የሞተች ስለሆነ የከሣሽ እናት ሟች ወ/ሮ ሁሉአገርን ወርሣ አልሞተችም፡፡ በመሆኑም የከሣሽ እናት የፍትሃብሐር ሕግ ቁጥር 830 በሚደነግገው መሠረት ወ/ሮ እማዋይ ከወሮ ሁሉአገር በፊት ስለሞተችና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 832 መሠረት ወራሽነቷን አረጋግጣ ሰላልሞተች ከሣሽ ወራሽ መሆን አይችሉም በማለት የተከራከረ ሲሆን ፣ ሁለተኛዋ ተከሣሽና የከሣሽ አክስት የሆነችው ወ/ሮ አሠፉ አዳነ ከሣሹ ከሟች አያቱ ውርስ የእናቱን ድርሻ ሊወስድ ይገባዋል በማለት ክሱን አምና ተከራክራለች፡፡

ፍርድ ቤቱም ከሣሽ በወ/ሮ ሁሉአገር ውብቴ ውርስ ጉዳይ ክስ ለመመስረት የሚያስችለው መብት አለው ወይስ የለውም የሚለውን ጭብጥ ካወጣ በኋላ በሰጠው ውሣኔ፣ በክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው የከሣሽ አያት ወ/ሮ ሁሉአገር ውብቴ መሆናቸው አልተካደም፡፡ የከሣሽ እናት ደግሞ ወ/ሮ እማዋይ አለምኔ መሆናቸው የከሣሽ አያት ብቸኛ ወራሾች ደግሞ የከሣሽ እናትና ሁለተኛ ተከሣሽ መሆናቸው በግራ ቀኙ የተካዱ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ከዚህ በመነሳት የከሣሽን መብት ስንመለከት ከሣሽ ያቀረበው ጥያቄ የምትክ ወራሽነት ነው፡፡ አንደኛ ተከሣሽ አጥብቆ ያነሣው የመከራከሪያ ነጥብ ይህንኑ አግባብ አይደለም የሚል ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/3/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው ከሟች ልጆች የሚወርሰው ንብረት ባለ ጊዜና እሱ አስቀድሞ የሞተ እንደሆነ በእሱ እግር ተተክተው ተወላጆች መውረስ እንዲችሉ የተደነገገ ነው፡፡ አንደኛ ተከሣሽ እዚህ ላይ ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብ የከሣሽ እና ከከሣሽ አያት ቀድማ የሞተች ስለሆነ አልወረሰችም፡፡ ምክንያቱም ለመውረስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 መሠረት መጀመሪያ ሟች ሲሞት በህይወት መኖር አለበት፡፡ እናቱ ሣትወርስ ከሞተች ደግሞ ተከሣሽ እናቱ የሌላትን መብት ስለማይወርስ ክስ የማቅረብ ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ ነው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 ላይ አንድ ሰው ለመውረስ ተወራሹ ሲሞት በህይወት መገኘት አለበት፡፡ ወደ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/3/ ስንመጣ ደግሞ አንድ የሟች ልጅ ሟችን ተክቶ መውረስ እንደሚችል ደንግጓል፡፡ እንደዚህ የሉ እርስ በርሣቸው የሚቃረኑ የሚመስሉ ትርጉም በምናስታርቅበት ጊዜ ደግሞ ሁለቱን ድንጋጌዎች ስራ ላይ እንዲውሉ እንደሆነ አድርጎ መተርጐም ያስፈልጋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830 መሠረት ተወራሹ ሲሞት ወራሽ በህይወት ከሌለ መውረስ አይችልም ካልን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/3/ ስራ የሌለው አንቀጽ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 842/3/ መተርጐም የሚገባው በአንደኛው ተከሣሽ

አተረጓጐም ሳይሆን መጀመሪያ ሣይወርሱ የሞቱና እርሱ ደግሞ ወራሽ ልጆች ትተው ላለፉ ተወራሾች ነው፡፡ በዚህ አተረጓጐም መሠረት ከሣሽ እህቱን ተክቶ የአያቱን ንብረት የመውረስ መብት ስላለው ክስ ማቅረብ ይችላል፡፡ ሁለተኛዋ ተከሣሽና የሟች ወሐሮ ሁለአገር ልጅ ይህንን አልካደችም ስለሆነም አንደኛው ተከሣሽ በዚህ ረገድ ያቀረበው መከራከሪያ ነጥብ የህግ ድጋፍ የለውም፣ በማለት ሌሎች ነጥቦችንም አንስቶ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

እዚህ ላይ የሚታየው ማችን ለመውረስ በህይወት መኖር አስፈላጊ ሲሆን ወደታች የሚቆጠር ተወላጆች ያሏቸው ሰዎች ሟች ሲሞት በህይወት ባይኖሩም ተወላጆቻቸው እነርሱን በመተካት በሟች ውርስ የሚካፈሉበት የውርስ ስርዓት በአገራችን ሕግ የተፈቀደ ነው፡፡ ምክንያቱም አሁን ያለን የውርስ ስርዓት ሟች ኑዛዜ ከሌለው ውርሱ የእሱ የቅርብ የስጋ ዘመድ የሆነው እንዲያገኝ የሚፈቅድ ነው፡፡ ስለዚህ የሟች ውርስ ሲከፈት በህይወት መኖር ሟችን ለመውረስ አስፈላጊ መሆን በመርህ ደረጃ ቢቀመጥም በህይወት ቢኖር ኖሮ በሟች ውርስ የመካፈል እድል የነበረው ሰው ተወላጆች እሱን ተክተው በሟች ውርስ የሚካፈሉበት የውርስ  ስርዓት በልዩ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ይህንን መገንዘብና ሁሉንም የሕግ ድንጋጌዎች ተግባር ላይ ማዋል ልንከተለው የሚገባን የሕግ አተረጓጐም ዘዴ ነው፡፡

ከሟች ጋር የስጋ ዝምድና ሣይኖራቸው ወይም በጉድፈቻ ውል መሠረት ሕግ የሚያስቀምጠው አግባብ ሣይተሣሠሩ የስጋ ዝምድናንና ወራሽነትን አስመልክቶ በሚነሱ ክርክሮች ላይ የበለጠ ግንዛቤዎችን ለማዳበር ይረዳ ዘንድ የሚከተለውን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 152/87 የካቲት 10 ቀን 1991 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ ማየቱ ጠቃሚነት ይኖረዋል፡፡ ክርክሩ የተነሣው ይግባኝ ባይ ወሐሮ ጤና ገሠሠ እና መልስ ሰጭዎች ወሐሮ ውጭት ገሠሠ አና ሙሉየ ገሠሠ መካከል ነው፡፡ ይግባኙ የቀረበው የሰሜን ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መጋቢት 29 ቀን 1987 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነው፡፡  የክርክሩ መነሻ የሟች የእማሆይ ስመኝሽ ወርቄ ወራሽነት ጥያቄ ነው፡፡ የአሁን ይግባኝ ባይ በጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 47181 እናቴ እማሆይ ስመኝሽ ወርቄ ነሐሴ 28 ቀን 1979ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየች ስለሆነ ወራሽነቴ ይረጋገጥልኝ በማለት አቤቱታ አቅርባ የወረዳው ፍሐቤት ተቃዋሚ እንዳለ እንዲቀርብ ጥሪ አድርጐ ተቃዋሚ ባለመቅረቡ አራት ምስክሮች አቅርባ አሰምታለች፡፡  የቀረቡት አራት ምስክሮች እማሆይ ስመኝሽ ወርቄ የጤና ገሠሠ እናት ናት በማለት ስለመሰከሩ ፍርድ ቤቱ ጤና ገሠሠ የሟች ስመኝሽ ወርቄ ወራሽ ናት በማለት ሕዳር 24 ቀን 1981 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው ሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቄ ያሣደገችው መሆኑን ገልፀው ነሐሴ 1 ቀን 1975 ዓ.ም ባደረገችው ግልጽ ኑዛዜ ከባሏ ከአቶ ካሣ ገሠሠ ጋር ያፈራችውን የጋራ ንብረት የእሷ ድርሻ እና የግል ንብረቷ ጠቅላላ ወራሽ እንድንሆን የሾመችን ስለሆነ የሟች የኑዛዜ ወራሾች መሆናችን ይረጋገጥልን በማለት

በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 321/84 አመልክተዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝ እማሆይ ስመኝ ወርቁ በአምስት ምስክሮች ፊት ነሐሴ 1 ቀን 1975 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ አቅርበዋል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ በጋዜጣ ጥሪ አድርጓል በዚህ መሠረት የአሁን ይግባኝ ባይ በተቃዋሚነት ቀርባ የሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ወራሽ እኔ መሆኔ በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 47/81 በዚሁ ወረዳ ፍርድ ቤት ሕዳር 24 ቀን 1981 የተረጋገጠ በመሆኑ በሀሰት በተዘጋጀ ኑዛዜ ወራሽነታችን ይታወቅልን በማለት መዝገብ ማስከፈታቸው ተገቢ ስላልሆነ ይሻርልን በማለት ተቃውሞዋን አቅርባለች፡፡ መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው ተቃዋሚዋ ከእማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ጋር ምንም አይነት የደም ትስስር ሳይኖራት በሀሰት የሟች ልጅ ነኝ ብላ በማስመስከሯ ወራሽነቷን ማረጋገጧ አውቀናል፡፡ በመሆኑም እኛም ለመቃወም የሚያስችላት መብት የሌላት ከመሆኑም በላይ በሀሰት ምስክርነት የወሰደችውን የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ልትመልስ ይገባታል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳ ፍርድ ቤት መልስ ሰጭዎችን ይግባኝ ባይ ወራሽ ነኝ በማለት ስታመለክት የኑዛዜ ጽሑፍ ይዘው ቀርበው ስላልተቃወሙ ከዚህ በኋላ የሟች ወራሽ ነን ብለው መጠየቃቸው ተገቢ ስላልሆነ ጥያቄአቸውን አልተቀበልኩትም በማለት አሰናብቷቸዋል፡፡

መልስ ሰጭዎች በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ መልስ ሰጭዎች የሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው፣ ይግባኝ ባይንም ቀደም ሲል የተሰጣትን የወራሽነት ማስረጃ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1 በሚደነግገው መሠረት በሶስት ዓመት ውስጥ ቀርበው ስላልተቃወሙ ለይግባኝ ባይዋ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ እንደፀና ይቆያል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኙ የቀረበው ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ሟች እማሆይ ስመኝሽ ወርቁ ለመልስ ሰጭዎች ያደረጉት ኑዛዜ በውል አዋዋይ መስሪያ ቤት ፊት ስላልተፈፀመ የወራሽነት ጥያቄው የይርጋ ጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ የቀረበ በመሆኑና መልስ ሰጭዎች የሕግ ምስክሮች አቅርበው ስለአስመሰከሩ አላግባብ የወራሽነት ማስረጃው በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጣቸው ስለሆነ እንዲሻርልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው ይግባኝ ባይ የእማሆይ ስመኝ ወርቁ ልጅ አይደለችም የሀሰት ምስክርነት አቅርባ የወራሽነት ማስረጃ መውሰዷ ሣያንሣት እኛን ለመቃወም የሚያስችላት ሕጋዊ መብት የላትም፡፡ የይግባኝ ባይ ወላጅ እናት እማሆይ አዋጉ ተዋበ በሕይወት ይኖራሉ እኛ የሟች የኑዛዜ ወራሾች ነን፡፡ ስለዚህ የይግባኝ ባይን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይግባኝ ባይ መልስ አቅርባለች ይዘቱ ከይግባኙ ቅሬታው ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ አልገለበጥነውም፡፡ በስርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ከላይ የተለገፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል መዝገቡን እንደመረመርነው

/1/ ይግባኝ ባይ የመልስ ሰጭወችን የኑዛዜ ወራሽነት ለመቃወም የማያስችላት ሕጋዊ መብት አላት ወይስ የላትም?

/2/ መልስ ሰጭዎች የሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው መባሉ ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች ማየቱ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ ይግባኝ ባይ በዚህ መዝገብ ሁለት የወረዳ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማስረጃነት አያይዛለች፡፡ የመጀመሪያው የወረዳው ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 253/75 በአቶ ገሠሠ ካሣ ውርስ ግንቦት 2 ቀን 1975 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ ይህ ውሣኔ እማሆይ ስመኝ ወርቁ የሟች ገሠሠ ካሣ ሚስት መሆናቸውን ይግባኝ ባይዋ ደግሞ አቶ ገሠሠ ካሣ እማሆይ ስመኝ ወርቁ ሣይሆን ከሌላ ሴት ይግባኝ ባይዋ ጤና ገሠሠ የተወለደች ልጃቸው መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በዚህ ውሣኔ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ ባይ የሟች እማሆይ ስመኝ ወርቁ የስጋ ልጅ አይደለችም፡፡

ሁለተኛው ይኸው የጐንደር ወረዳ ፍርድ ቤት በስራ ፋይል መዝገብ ቁጥር 47/81 የአራት ምስክሮችን ቃል ከሰማ በኑላ ይግባኝ ባይዋ ጤና ገሠሠ የእማሆይ ስመኝ ወርቁ ልጅና ወራሽ ናት በማለት የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡ይህ ውሣኔ የተሰጠው በሁለት የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግና ይግባኝ ባይ 1975 ዓ.ም በወረዳው ፍርድ ቤት የአባቷን ወራሽነት ለማረጋገጥ ያቀረበችውን ማስረጃ ባለመገናዘብ ነው፡፡ በአጠቃላይ የይግባኝ ባይ ወላጅ እናት እማሆይ ስመኝ ወርቁ እንደሆኑ ከመሞታቸው በፊት 1975ዓ.ም ይግባኝ ባይ እና ሟች ስመኝ ወርቁ በአንድ ላይ ባስከፈቱት መዝገብ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ ከሟች እማሆይ ስመኝ ወርቁን ያለኑዛዜ የምትወርስበት የስጋ ዝምድናና የደም ትስስር የላትም ይግባኝ ባይ የሟች ልጅ ሣትሆን ልጅ ነኝ በማለት በወራሽነት መቅረቧ ተገቢ ባለመሆኑ የመልስ ሰጭዎችን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም ክርክር የምታቀርብበት ሕጋዊ ምክንያት የላትም፡፡

በመሆኑም መልስ ሰጭዎች የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን በመቃወም ይግባኝ ስላላቀረቡ ወይም የይግባኝ ባይ ይግባኝ እንደደረሣቸው የሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መስቀለኛ ይግባኝ ባለመቅረባቸው ይግባኝ ባይ የሟች እማሆይ ስመኝ ወርቁ ወራሽናት በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማሸር ወይም ለማሻሻል የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ስለማይፈቅዱ እንዳለ የተውነው ሲሆን ይግባኝ ባይዋ ሟችን ለመውረስ የሚያስችላት ሕጋዊ ሁኔታ ሳይኖር የሟችን የኑዛዜ ወራሾች ተቃዋሚ ሆኖ መቅረቧና በይግባኝ መከራከሯ ተገቢ ሆና አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ መልስ ሰጭዎች የሟች እማሆይ ስመኝ ወርቁ ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሟች በግልጽ ያደረገችው ኑዛዜ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ የኑዛዜው ጽሁፍ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተመለከቱትን ፎርማሊቲዎች የሚያሟላና የሟች ትክክለኛ ቃል መሆኑን የማያሣይ በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት መልስ ሰጭዎች የሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው በማለት

የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ከዚህ በማስከተል የሚነሣው ጥያቄ ይግባኝ ባይ የሟች ልጅ ነኝ በማለት የተሰጣትን የወራሽነት የምስክርነት ወረቀት መልስ ሰጭዎች ባለመቃወማቸው ይግባኝ ባይ የሟች የሕግ ወራሽ ሆናለች፡፡ በሌላ በኩል መልስ ሰጭዎች የሟች የኑዛዜ ወራሾች ናቸው ተብሏል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭዎች በሟች ውርስ ላይ ያላቸው መብት እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡

ይህንን ነጥብ አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ ስንመለከተው የሟች ውርስ በከፊል በኑዛዜና በከፊል ያለኑዛዜ ሊፈፀም እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 829/2/ ያመለክታል፡፡ በዚህ የሕግ ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ ባይ የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ ስትሆን መልስ ሰጭዎች ደግሞ የኑዛዜ ወራሾች ናቸው፡፡ ሟች መልስ ሰጭዎችን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የሾማቸው በመሆኑ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ተቀባይ ያገኘ ሰው ያለኑዛዜ ወራሽ እንደሆነ እንደሚቆጠር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 915/1የተደነገገ በመሆኑ ከላይ በጠቀስናቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የሟች እማሆይ ስመኝ ወርቁ ንብረት፣ ይግባኝ ባይዋ ወ/ሮ ጤና ገሠሠ አንደኛ መልስ ሰጭ ወ/ሮ ሙጭት ገሠሠ ሁለተኛ መልስ ሰጭ ተማሪ ሙሉየ ገሠሠ በወራሽነታቸው ቀርበው እኩል መካፈል ይገባቸዋል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት አጽንተነዋል በማለት ወስኗል፡፡

ከውሣኔው እንደምንረዳው ከሟች ጋር ምንም አይነት የስጋ ዝምድና ወይም የጉድፈቻ ውል መሠረት ግንኙነት የሌላቸው ሰዎች የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ በማለት በሚቀርቡበት ሁኔታ መኖሩን ሲሆን በሌላ በኩል አንድ ተከራካሪን አስመልክቶ ጉዳዩን በስር ያየው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት ይግባኝ ወይም መስቀለኛ ይግባኝ ካልቀረበበት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ ስህተት ቢኖርበትም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በራሱ አነሣሽነት የማይሽረው መሆኑን ነው፡፡ በአጠቃላይ የሟች ውርስ አስመልክቶ ከሚነሡት በርካታ አለመግባባቶች የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሽ ነኝ በሚሉ ነጥቦች ዙሪያ የሚደረግ በመሆኑ የሕጉን ድንጋጌዎች ዓላማና ይዘት በአግባቡ መረዳትና ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡

## <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በዋና ወራሽነት እና በተተኪ ወራሽነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? ሟችን በተተኪነት ለመውረስ የማይቻልባቸው ምክንያቶች ምንድን ናቸው?

2. የደቡብ ጐንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መነሻ አድርገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 830፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 833 እና የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 842/2፣ 844/2፣848/2፣ እንደዚሁም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 853/1 መካከል መሠረታዊ የሆነ ቅራኔ አለው ብለው ያስባሉ? ለምን?
3. የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1088 ድንጋጌዎች መካከል ያለው ተዛማጅና ልዩነት ምንድን ነው?
4. ከበደ ከአባቱ አንድ ሚሊየን ብር የሚወጣ ቤት በቁም ስጦታ አግኝቷል፡፡ ከበደ በድንገተኛ አደጋ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፣ መኣዛ የተባለች ልጅ ነበረችው፡፡ መዓዛ በአስር ዓመቷ ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ በአንደኛ ደረጃ ወራሽነት የሚጣራ ልጅ ወይም ሌሎች ተወላጆች አልነበራትም፡፡ የመዓዛ ወላጅ እናት ሒሩት የመዓዛ ወራሽ መሆኗን አረጋግጣ ቤቱን ለመረከብ ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ የከበደ እህቶች ኬዳኔና ቤቴልሔም ቤቱን ከአባት ወገን በስጦታ የተገኘ ስለሆነ ለመዓዛ አናት ሒሩት ሊሰጥ አይገባም በማለት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 ጠቅሰው ተቃውሞ አቀረቡ፡፡ እርስዎ ዳኛ ቢሆኑ ምን ይወስናሉ? የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 849 ከፍትሐብሐር ህግ ቁጥር 844/3 በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 846/2 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 851 ድንጋጌ ጋር እንዴት በመጣጣም ይተረጎማል?
5. የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 30574 የሰጠውን ወሳኔ አንብባችሁ ተወያዩበት፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# በሟች ኑዛዜ መሠረት የሚፈፀም ውርስ

**የስልጠናው ግብ፡-**

ሰልጣኞች፡-

በኑዛዜ አተረጓገምና አፈፃፀም ዙሪያ በፍርድ ቤት የሚያጋጥሙ ችግሮችና መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን ይለያሉ፡፡

## 5.1 ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የስረ ነገር ሁኔታዎች

በውርስ ሕጋችን ውስጥ ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥረ ነገር ሁኔታዎች /Essential Conditions of Will/ በሚለው ርእስ ስር የተደነገጉት ድንጋጌዎች አንድ ኑዛዜ ኑዛዜ ነው ተብሎ በሕግ ፊት ውጤት ለመስጠት ምን ምን የሥረ ነገር ሁኔታዎችን ማሟላት እንዳለበት የሚደነግጉ ናቸው፡፡ ለኑዛዜ ዋጋ

መኖር አስፈላጊ የሆኑ የሥረ ነገር ሁኔታዎች ተብለው በሕጉ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች በሁለት ከፍሎ ማየትና መተንተን ይቻላል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ኑዛዜውን ሁለንተናዊ ወይም ተፈጥሯዊ አስፈላጊ ነገር /inherent or intrinisic elements of will/ የሚባሉትን የሚደነግጉ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ የኑዛዜውን ይዘት ላይ የሚያተኩሩና ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ መሆን ወይም አለመሆኑን የሚቆጣጠሩ ናቸው፡፡ የኑዛዜ ሁለንተናዊ ወይም ተፈጥሯዊ ነገር /inherent Elements of will/ የሚባለው ተናዛዡ ኑዛዜውን በሚፈጽምበት ሰዓት የነበረው የአእምሮ ሁኔታ ወይም ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ የነበረው መሆኑ/ animus testandi/ የምንለው ነው፡፡ ሆኖም አከራካሪው ጉዳይ የሚነሣው ኑዛዜ አድራጊው ከሞተ በኋላ ስለሆነ ኑዛዜ አድራጊው በሙሉ ሀሣብና ፍላጐት ኑዛዜውን ያደረገ ስለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ መሆን ይቻላል የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህንንም ለመረዳት የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት የሚገቡት፣

- ተናዛዡ ራሱ በሙሉ ሀሣብ ኑዛዜ የፈጸመ መሆኑ፣
- የተናዛዡ ኑዛዜ የመፈጸም ችሎታ፣
- ኑዛዜው በመገደድ ወይም በስህተት ወይም በመንፈስ መጫን ያልተደረገ መሆኑ፣
- ኑዛዜው ሕጋዊ መሆኑ ናቸው፡፡

## 5.2 <u>በሕጉ የተቀመጠውን ፎርም አሟልቶ መገኘት</u>

ሁለተኛው ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አስፈላጊ የሆነው ሁኔታ፣ ኑዛዜው በሕጉ የተደነገገውን ፎርም አሟልቶ የመገኘቱ ሁኔታ ነው፡፡ የብዙ አገሮች የውርስ ሕግ ኑዛዜ በምን ፎርም ሊፈፀም እንደሚገባ የሚደነግጉ የሕግ ድንጋጌዎች ይዘው እናገኛለን፡፡ ምክንያቱም ኑዛዜው በሚፈፀምበት ጊዜ ተናዛዡ ኑዛዜ ለማድረግ የነበረውን ሀሣብ በቀላሉ ማረጋገጥ የማይቻልና ሚችንም አንድን ተግባር የፈፀመው ኑዛዜ ለማድረግ አስቦ መሆን አለመሆኑን ጠይቆ ለመረዳት የሚቻልበት አጋጣሚ ስለሌለ ሕግ አውጭው አንድ ተግባር ኑዛዜ መሆኑንና ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው የሚፈልግ ኑዛዜ አድራጊ ኑዛዜውን በምን አይነት መንገድ ማከናወን እንደሚገባው ስለ ኑዛዜ ፎርም በሚደነግጉ ድንጋጌዎች ይወስናል፡፡

የኑዛዜ ፎርም ለኑዛዜ ዋጋ መኖር አንደኛው አስፈላጊ ነገር ሲሆን ይኸም extrinisic or formal element of the will በማለት ይጠቀሣል፡፡ የኑዛዜ ፎርም ከተናዛዡ ውጭ በሆነ በሌላ ሀይል እንዳይዘጋጅ ሕግ አውጭው ኑዛዜው በምን መልክ መዘጋጀት እንዳለበት በህግ የሚደነግግ ነው፡፡ ሌላው ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነገር በውርስ ሕግ ውስጥ ስለ ኑዛዜ ፎርም የሚደነግጉት የሕግ ድንጋጌዎች እጅግ በጣም ጥብቅና የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይኸም ማለት ኑዛዜው በሕጉ የተመለከተውን ፎርም አሟልቶ ካልተገኘ በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም የኑዛዜ ፎርማቶችን የማሟላቱ ጉዳይ ኑዛዜ አድራጊው ሲፈልግ የሚከተላቸው ሣይፈልግ ደግሞ የሚተዋቸው አይደሉም፡፡ አንድ ሰው

የሚፈጽመው ኑዛዜ በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ በሕጉ የተቀመጡትን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ኑዛዜውን መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ኑዛዜ በሶስት ዓይነት ፎርም ሊፈፀም እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ይኸውም፣

- በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ /public will/
- በተናዛዡ ጽሑፍ የሚደረግ ኑዛዜ /Holographic will/
- በቃል የሚደረግ ኑዛዜ /oral will/ ናቸው፡፡

ሀ/ <u>በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ</u>

በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ /public will/ ስሙ ራሱ እንደሚያመለክተው አንድ ሰው ኑዛዜውን ሲፈጽም ሌሎች ሰዎች /እማኞች ባሉበት የተደረገ በዚህም ምክንያት ለአካባቢው ሕብረተሰብ ግልጽ የሆነ /will be made in the presence of the public/ ማለት ነው፡፡ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሚከተሉትን ሁኔታዎች አሟልቶ መገኘት አለበት፡፡

ተናዛዡ እየተናገረ ተናዛዥ የሚናገረውን ማናቸውንም ቃል ሣይቀንስ ወይም ሣይለውጥ ሌላ ሰው የጻፈው ወይም ተናዛዡ ራሱ የጻፈው መሆን አለበት፡፡

ኑዛዜው በተናዛዡና በአራት ምስክሮች ፊት መነበብና ኑዛዜው የተደረገው አራት ምስክሮች ባሉበትና በመጨረሻም በተናዛዡና በምስክሮቹ ፊት የተነበበ መሆኑን መግለጽ አለበት፡፡

ኑዛዜው የተጻፈበትን ቀን ማመልከትና ተናዛዡና ምስክሮቹ ወደያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረግ እንደሚገባቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 ይደነግጋል፡፡

በግልጽ የተደረገው ኑዛዜ የሚፈፀመው አንድ ዳኛ ወይም ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ ከሆነ ለኑዛዜው ዋጋ ማግኘት የሁለት ምስክሮች መገኘትና የኑዛዜውን ጽሑፍ ተነብቦላቸው መፈረማቸው በቂ እንደሆነ የሕጉ ድንጋጌዎች የሚያመለክቱ ሲሆን በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ምስክር የሚሆኑ ሰዎች አካለ መጠን ያደረሱ በፍርድ ወይም በሕግ ያልተከለከሉ ምስክሮቹ ኑዛዜው የተጻፈበትን ቋንቋ ለማወቅና የተጻፈውንም ለመስማት ወይም ለማንበብ ችሎታ ያላቸው መሆን እንዳለባቸውና እነዚህ ሁኔታዎች ሣይሟሉ ኑዛዜው ተፈጽሞ ቢገኝ ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 883 ይደነግጋል፡፡ በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜን አስመልክቶ በሕጉ የተቀመጡት የአፈጻጸም ስርዓቶች

ብናያቸው እጅግ በጣም ጥብቅ ናቸው። መስፈርቶቹም ኑዛዜውን ይዘት ተናዛዡና ምስክሮቹ እንዲያውቁት የሚያደርግና ለተናዛዡም ሆነ ምስክሮቹን የኑዛዜውን ይዘት እንዳያውቁ የሚያደርግ ቢሆን ለምሣሌ ኑዛዜው ለምስክሮቹ ካልተነበበላቸው ወይም ኑዛዜው ተናዛዡም ሆነ ምስክሮቹ በማያውቁት ቋንቋ የተጻፈ ከሆነ ፈራሽ እንደሚሆን የሚደነግጉ ናቸው።

እዚህ ላይ ኑዛዜው በሌላ ቋንቋ ተጽፎ ለተናዛዡና ለምስክሮቹ በአስተርጓሚ እየተተረጐመ ቢፈፀም ውጤቱ ምን ይሆናል የሚለው ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። የኑዛዜው ፎርም በሕግ መደንገግ የሚያስፈልገው ኑዛዜው የተናዛዡን ፍላጐትና ሀሣብ አሟልቶ መገኘቱን ለማረጋገጥ ነው። ስለዚህ በአስተርጓሚ የሚደረግ ኑዛዜ ተናዛዡ ከሚያስበውና ከሚፈልገው ውጭ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ ሰፊ በር የሚከፍት በመሆኑ ተፈጽሞ ቢገኝ ፈራሽ እንደሚሆን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 883 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል። ምክንያቱም ሕጉ ምስክሮቹ በመጀመሪያ ኑዛዜው የተጻፈበትን ቋንቋ ማወቅ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በሁለተኛ ደረጃ የተጻፈው ሲነበብላቸው ለመስማት ወይም የጽሑፉን ይዘት አንበው ለመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል። ይህንን መስፈርት በግልጽ በሚደገግ ኑዛዜ የሚች ቃል በሚናገረው ቋንቋ ቃል በቃል መጻፍ እንዳለበት ከሚደነግገው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማጣመር ስናየው ሚች በአማርኛ እየተናገረ በእንግሊዝኛ ተተርጉሞ ተጽፎ ተናዛዡና ምስክሮቹ ቢፈረሙበት ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ይቻላል።

ለማንኛውም በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ዙሪያ የሚቀርቡ ክርክሮች በርካታ ናቸው ለምሣሌ ሶስት ምስክሮች ፊት የተደረገ ኑዛዜ ውጤት ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም? ከአራቱ ምስክሮች አንደኛው አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም በሕግ የተከለከለ ቢሆን ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚሉትና ሌሎች በርካታ ጥያቄዎች ይነሣሉ። አንድ ነገር በእርግጠኝነት ለመናገር የሚቻለው የእኛ አገር የውርስ ሕግ ብቻ ሣይሆን የብዙ አገሮች የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች የኑዛዜ ፎርሞች ጥብቅና አስገዳጅ እንዲሆኑ የሚያደርጉት ሚች ኑዛዜ የማድረግ ሀሣብ ኖሮትና የሚፈጽመውን ኑዛዜ ይዘት ተረድቶና አውቆት መሆኑ ለማረጋገጥ ጥብቅ የኑዛዜ አፈጻጸም ስርዓት አስቀምጦ ፎርማሊቲዎቹ መሟላታቸው ከመቆጣጠር ውጭ ሌላ መንገድ ስለሌላቸው ነው። ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያ ሕግም በሕጉ ከተቀመጠው አንዱ ካልተሟላ ኑዛዜው ፈራሽ እንደሚሆን ማስቀመጡ ተገቢነት ያለው ነው።

ለ/ <u>በተናዛዡ ጽሁፍ የሚደረግ ኑዛዜ</u>

በእኛ የውርስ ሕግ አንድ ሰው በራሱ የእጅ ጽሑፍ ኑዛዜ እንዲፈጽም ይፈቅዳል። ተናዛዡ በራሱ እጅ ጽሑፍ ያደረገው ኑዛዜ ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው፣

- ተናዛዡ ኑዛዜው ሙሉ በሙሉ በራሱ የእጅ ጽሁፍ የጻፈው እንደሆነ፣
- ተናዛዡ የጻፈው ጽሑፍ ኑዛዜ መሆኑን በግልጽ ያመለከተ እንደሆነ፣
- ኑዛዜው ከአንድ ገጽ በላይ ከሆነ ተናዛዡ እያንዳንዱ ገጽ ላይ ከፈረመበትና ቀን የጻፈበት እንደሆነ

መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 884 ይደነግጋል፡፡
ከዚህ በተጨማሪ ተናዛዡ ያደረገውን ኑዛዜ ራሱ በመኪና ጽፎት እንደሆነና በእያንዳንዱ ቅጠል ራሱ በመኪና የጻፈው መሆኑን በእጅ ጽሑፍ ካመለከተ ውጤት እንደሚኖረውና ይህንን ካላደረገ ግን ፈራሽ እንደሚሆን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 885 ይደነግጋል፡፡

እንደዚሁም በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የሆነው ኑዛዜ ተናዛዡ ያልተማረ ማህይም በመሆኑ ወይም ኑዛዜውን የተጻፈበትን ቋንቋ ካላወቀው ወይም ፍቻቸውን በማያውቃቸው ፊደሎች ጽፎ ቢገኝ ፈራሽ እነደሚሆንና ኑዛዜው የተደረገበትን ቀን ወርና ዓመት ምህረት ማመልከት እንደማገባው ይደነግጋል፡፡

ሐ/ <u>በቃል የሚደረግ ኑዛዜ</u>

አንድ ሰው የሞቱ መቃረብ ተሰምቶት የመጨረሻ ፈቃድ ቃሎቹን በሁለት ምስክሮች ፊት ሊሰጥ እንደሚችልና ይኸም የቃል ኑዛዜ በመባል እንደሚታወቅ የቃል ኑዛዜ በሕግ ውጤት እንዲኖረው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ማሟላት እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 892 ይደነግጋል፡፡

ኑዛዜው ያደረገው የመሞቻ ጊዜው መቃረቡን ተሰምቶት መሆን ይገባዋል፡፡ ይኸ ማለት ምንም አይነት የሕመም ስሜት ወይም አደጋ ሣይገጥመው ሟች እኔ ስሞት እከሌ ይህንን ይወስዳል በማለት የሚያወራው ወሬ ሁሉ የቃል ኑዛዜ ነው ተብሎ እንደማይወሰድ፣ የመሞቻ ጊዜው መቃረቡ ተሰምቶት፣ የሚለው የሕጉ ድንጋጌ ሀረግ፣ ያመለክታል፡፡

ኑዛዜውን ያደረገው ቢያንስ ሁለት ምስክሮች ባሉበት መሆን አለበት እንደዚሁም ምስክሮቹ አካለ መጠን ያደረሱ በፍርድ ወይም በሕግ ያልተከለከሉ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቃል ኑዛዜ ሊደረግባቸው የሚችሉት ጉዳዮች ምን እንደሆኑ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 893 ይደነግጋል፡፡

ከዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ነገር ሟች በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ወይም በራሱ እጅ ጽሑፍ ባደረገው ኑዛዜ በርካታ ጉዳዮች አንዲፈፀሙለት መመሪያ ሊሰጥ ይችላል፣ ይኸም ማለት ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ መሾም ከፍተኛ የዋጋ ግምት ያለውን ንብረቱን በልዩ የኑዛዜ ስጦታ መስጠት፣ ከወራሾቹ አንዱን

ወይም ሁሉንም ከውርስ መንቀል እና ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ ኑዛዜ መተው ይችላል፡፡ በቃል ኑዛዜ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ጉዳዮች ግን በሕግ ገደብ ተደርጐበታል፡፡

ሟች በሚያደርገው የቃል ኑዛዜ ስለ ቀብሩ ሥነ ሥርዓት መመሪያ መስጠት የእያንዳንዱ የስጦታ ዋጋ ከብር 500 ለመብለጥ ሣይችል ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ማድረግ አካለ መጠን ላላደረሰ« ልጆች ሞግዚት ወይም አስተዳዳሪ መሾም እንደሚችል የሕጉ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሟች በቃል ኑዛዜ ከነዚህ ውጭ የሆነ ነገር ቢናገር ለምሣሌ ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ ቢሾም ወይም ከወራሾቹ አንዱ ከውርስ እንዲነቀል ቢናዘዝ ውጤት እንደማይኖረው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 894/1/ የሚደነግግ ሲሆን ሟች በቃል ኑዛዜ ግምቱ 500 ብር በላይ የሆነ ስጦታ ቢሰጥ ከዚህ በላይ ያለው ነገር እንደሚቀንስ በፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 894/2/ ተደንግጓል፡፡ በአጠቃላይ በቃል የሚደረግ ኑዛዜ ሟች ሁለት ምስክሮቹ ባለበት ከሞተ በኑላ ስለሚፈፀሙ ነገሮች የሰጠውን ቃል የሚመለከቱ በመሆናቸው ከሟች ቃል ሊረሣ ወይም ሊጨመርበት የሚችሉበት አጋጣሚ ሰፊ በመሆኑ ሕጉ በቃል ኑዛዜ ሊካተቱ ስለሚገባቸው ጉዳዮች ገደብ በመጣል በዚህ በኩል ሊመጣ የሚችለውን ችግር ለመቀነስ ጥንቃቄ አድርጓል፡፡

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ከሶስቱ በአንደኛ ፎርም የሚጠይቀውን ሁኔታ ሣያሟላ የተፈፀመ ኑዛዜ እውቅና የማይሰጥና ኑዛዜውም ዋጋ እንደማይኖረው በኑዛዜ ፎርም ጥብቅና አስገዳጅ መሆኑን ፎርሙን አለማሟላት ኑዛዜውን ፈራሽ ሊያደርገው እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ስለ ኑዛዜ የተደነገጉት የውርስ ሕግ የሕግ ድንጋጌዎች በፍርድ ቤቶች የሚሰጣቸውን ትርጓሜ ፍርድ ቤቶች ከሰጧቸው ውሣኔ አንጻር መመልከቱ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ ከበርካታ ውርስ ውሳኔዎች መረዳት የሚቻለው ኑዛዜን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች አብዛኛዎቹ፣

- ኑዛዜው የሟች አይደለም፣
- ኑዛዜው ላይ ያለው ጽሑፍ ወይም ፊርማ የሟች አይደለም፣

የሚሉ የክህደት ክርክሮች ከሟች የስጋ ወራሾች በኩል እንደሚቀርቡና ፍርድ ቤቶችም የእጅ ጽሑፍ ወይም ፊርማው የሟች መሆኑን ለማረጋገጥ ለፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ክፍል በመላክ ይኸ የማይቻል ከሆነ ደግሞ ኑዛዜው ሲደረግ ምስክር የሆኑ ሰዎችን ቃል በመስማት ውሣኔ እንደሚሰጡ በርካታ አብነቶችን በማንሣት ለማየት ይቻላል፡፡

ይኸም ኑዛዜው የሟች አይደለም ወይም ኑዛዜው ጽሑፍ ወይም ፊርማ የሟች አይደለም የሚል ክርክር በሚቀርብ ጊዜ ኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች መሆኑን ለማረጋገጥ ምን አይነት ማስረጃ ነው መቅረብ ያለበት የሚለውን ነጥብ ለመገንዘብ የሚረዳ ይሆናል፡፡ ይህንን አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1207/88 ጥቅምት 6 ቀን 1993 ዓ.ም በይግባኝ ባይ በወ/ሮ

ደመቀች ልባሴ እና በመልስ ሰጭዎች በእነ ሻንበል ባሻ ተዘራሽ ሙሉነህ መካከል የነበረውን የይግባኝ ክርክር አይቶ የሰጠው ውሣኔ በአጭሩ ማየቱ ይጠቅማል፡፡

የክርክሩ መነሻ የሆነው የሟች ሙሉነህ ተክለወልድ ሚስት ነኝ የምትለው ይግባኝ ባይ ወ/ሮ ደመቀች ሰኔ 2 ቀን 1980 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ባለቤቱ ኑዛዜ የተወልኝ ስለሆነ የኑዛዜ ወራሽ መሆኔ ይጽናልኝ በማለት ጉዳዩን በመጀመሪያ ለሚያየው ፍርድ ቤት ያቀረበችው ማመልከቻ ሲሆን፣ መልስ ሰጭዎች በተቃዋሚነት ቀርበው አባታችን 1976 ዓ.ም ጀምሮ ማየት ስለማይችል ኑዛዜ ይጸናልኝ በማለት ያቀረበችው ሰነድ የሀሰት ሰነድ ነው፣ በኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የአባታችን ስላልሆነ ይመረመርልን በማለት ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ ያየው የአራዳ አውራጃ ፍርድ ቤት ኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማ የሟች ፊርማ ስለመሆኑ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲቀርብ ለፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ክፍል ታዞ፣ የፖሊስ ቴክኒክ ምርመራ ክፍልም ኑዛዜው ላይ ያለው ፊርማም ሆነ ለማመሣከሪያ የተላከው ፊርማ የተበላሸ ስለሆነ ፊርማው የእገሌ ነው ብለው ለመለየትና ለማረጋገጥ አልቻልንም በማለት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

የአውራጃው ፍርድ ቤት ወ/ሮ ደመቀች የሟች ሚስት ስለመሆኗና ሟች ኑዛዜ ያደረገላት ስለመሆኑ አራት ምስክሮችን ከሰማ በኋላ የሟች ሚስት መሆኗን በኑዛዜ ካረጋገጠ በኋላ ኑዛዜውን በተመለከተ ሟች የፈረመበት ስለመሆኑ ግልጽ ሆኖ በቴክኒክ ምርመራ ያልቀረበ ስለሆነ ወ/ሮ ደመቀች የሟች የኑዛዜ ወራሽ አይደለችም በማለት ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ በዚህ ውሣኔ ይግባኝ ብላ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን ብታቀርብም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 872 እና 938/1/ የሚቃረን በመሆኑ ይግባኙን አልተቀበልነውም በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት በውሣኔው ከሰጠው የተለየ የሕግ ምክንያት በመጥቀስ የይግባኝ ባይን ይግባኝ ውድቅ አድርጎታል፡፡

ይግባኝ ባይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ባለመቀበል ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርባለች፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተለያየ ምክንያት በመስጠት የአውራጃው እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሣኔ የሚከተለውን ትችት በመስጠት ሽሮታል፡፡

‹ከመዝገቡ ለመረዳት እንደቻልነው የፖሊስ የቴክኒክ የምርመራ ውጤት ፊርማው የሟቹ ነው አይደለም ለማለት አንችልም ከማለት ውጭ በግልጽ ያስቀመጠው ነገር የለም፡፡ ይህም በመሆኑ ሟች ኑዛዜው ላይ

ሲፈረሙ የነበሩና በኑዛዜው ላይ በምስክርነት የተጠቀሱት ምስክሮች ቀርበው በኑዛዜው ላይ ሟች መፈረማቸውን አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ፊርማው የሟች ለመሆኑ በቴክኒክ ምርመራ ለማረጋገጥ ባይቻልም፣ በኑዛዜው ወቅት ነበርን የሚሉ ምስክሮች የሰጡት ቃል ሲመዘን ዋጋ ያለው ሆኖ በመገኘቱና ማስተባበያ ማስረጃም ያልቀረበበት ስለሆነ ኑዛዜው የሟች ኑዛዜ ነው ለማለት ተችሏል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት የይግባኝ ባይ የኑዛዜ የጽደቅልኝ ጥያቄ ኑዛዜው ሕገ ወጥ ነው በማለት ውድቅ ማድረጉ አግባቡ ስላልሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 348(1) መሠረት ሽረነዋል› በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አስተያየት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተገቢነት ያለው ነው፡፡ ኑዛዜን አስመልክቶ የሚነሱ ክርክሮች ሟች ከሞተ በኋላ የሚቀርቡ በመሆናቸው የሟች የስጋ ዘመዶችና የሕግ ወራሾች የተለያየ ምክንያት እየፈጠሩ የሟችን ኑዛዜ በመቃወም ሙሉ ውርሱን ለመውሰድ ይጥራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሟች የማመሣከሪያ ፊርማዎች እንዳይገኙ ለማድረግ ሰነዶችን ሆነ ብለው በመቅደድ በማቃጠልና በማበላሸት ለቴክኒክ ምርመራ አስፈላጊ የሆነውን የማመሣከሪያ ፊርማ የሚያጠፉበት ወይም የሚያበላሹበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ እንደዚሁ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም በኑዛዜው ለይ ስማቸውና ፊርማቸው በምስክርነት የተገለጹት ሰዎች ሟች በኑዛዜ ሰነዱ ላይ ፊርማ የፈረመ ስለመሆኑ በአጥጋቢ ሁኔታ ካስረዱ የሟችን ኑዛዜ ውድቅ ማድረግ ሟቹ ከሞተ በኋላ ንብረቱን ለማስተላለፍ አስቦ የፈፀመውን ተግባር ያለ ምክንያት ህጋዊ ውጤት እንዳያገኝ ማድረግና የሟች የሕግ ወራሾች የሟችን የኑዛዜ ጽሑፍና ፊርማ ወይም ለማመሣከሪያ የሚሆኑ ሰነዶችን ሆነ ብለው እያጠፉ እና እያበላሹ የሕግ ወጥ ተግባራቸው ፍሬ እንዲሰበስቡ መፍቃድ ጭምር ሆኗል፡፡ በመሆኑም ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማስረጃውን የመዘነበትና የተቀበለበት አግባብ የሟችን ኑዛዜ እና ፍቃድ ከማስፈፀም አንጻር ፍርዱ ብዙ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

ሌላው በኑዛዜ ዙሪያ የሚደረጉ ክርክሮች የኑዛዜ ፎርሞችን መነሻ ያደረጉ ናቸው፡፡ ከዚህ በፊት እንዳየነው ሟች ኑዛዜው በሕግ ፊት ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ በሕጉ መሟላት አለባቸው የተባሉ ፎርሞችን በሚሟላት ኑዛዜውን ማድረግ አለበት፡፡ እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ሟች በሕጉ ከተገለፀው ፎርም አንዷን እንኳን መስፈርት ባያሟላ ምን ይሆናል የሚለው ነጥብ ነው፡፡

በዚህ ዙሪያ የሚነሱ ክርክሮችንና የሚሰጡ ውሣኔዎችን ለመረዳት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 1152 ሚያዝያ 19 ቀን 1993 ዓ.ም በይግባኝ ባዩ በአቶ ገብረየስ አርፍቶ እና በመልስ ሰጭ አፀደ ተፈራ መካከል የቀረበውን ክርክር ሰምቶ የሰጠውን ውሣኔ ማየቱ ለግንዛቤ ይረዳል፡፡

ክርክሩ የተነሣው ይግባኝ ባይ ሟች እናቴ ወ/ሮ ለተየሰ መካሻ መሆኔ ይረጋገጥ በማለት በወቀቱ ለነበረው ለአውራጃው ፍርድ ቤት በማመልከቱ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተቃዋሚ ስላልቀረበ ምስክሮችን ሰምቶ ኑዛዜውን አጽድቋል፡፡ በዚህ በኋላ መልስ ሰጭ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 መሠረት ውሣኔው ላይ ሟች የተናዘዘችበት ንብረት የሟች ሣይሆን የእኔ አባት ቤት ስለሆነ ውሣኔው ይሠረዝልኝ በማለት ውሣኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት በማመልከቷ የአውራጃው ፍርድ ቤት ሟች የተናዘዘችበት ቤት የተቃዋሚዋ (መልስ ሰጭ) አባት ቤት ስለሆነ መጀመሪያ የሰጠሁትን ውሣኔ ሽሬዋለሁ በማለት ወስኗል፡፡ የአሁን ይግባኝ ባይ የአውራጃው ፍርድ ቤት ጉዳዮን በድጋሚ አይቶ በሰጠው ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ የፊተኛው ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የቀረበው ኑዛዜ በሟች የእጅ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ ሣይሆን በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ነው፡፡ ሆኖም ኑዛዜው የተደረገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881/2/ በሚደነግገው መሠረት በአራት ምስክሮች ፊት ሣይሆን በሶስት ምስክሮች ፊት ስለሆነ በሕጉ የተቀመጠውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት የአውራጃው ፍርድ ቤት የሰጠውን ምክንያት ለውጦ ኑዛዜው አይፀናም የሚለውን የስር ፍርድ ቤት ወሣኔ አጽንቶታል፡፡

ይግባኝ ባዩ በከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የይግባኝ ባይንና የመልስ ሰጭን ክርክር ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሣኔ ይህ ፍርድ ቤት መዝገቡን ከሕጉ ጋር መርምሯል፡፡ ይህንን ጉዳይ ለመወሰን መልስ ማግኘት የሚገባው ጭብጥ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881/1/ መሠረት ፈራሽ ነው መባል ይገባዋል ወይስ አይገባውም የሚለው ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881/1/ እና 2 እንደተመለከተው ተናዛዥ  እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው በተናዛዥና በአራት መስክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸው ስርዓት /ፎርማሊቲ/ መፈፀምንና የተፈፀመበትን ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ ነው፡፡ ወደዚህ ጉዳይ ስንመለስ ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 የተመለከተውን ፎርም አላሟላም፡፡ ኑዛዜው የተደረገው በአራት ምስክሮች ፊት ነው የሚል ክርክር በይግባኝ ባይ በኩል አልቀረበም፡፡፡ በኑዛዜው ላይ በምስክረነት የተጠቀሱት ሶስት ሰዎች ናቸው፡፡ ሰለዚህ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት ነው የሚል ክርክር በይግባኝ ባይ በኩል አልቀረበም፡፡ በኑዛዜው ላይ የምስክርነት የተጠቀሱት ሶስት ሰዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ኑዛዜው በአራት ምስክሮች ፊት አለመደረጉ አላከራከረም፡፡ ይህ ማለት ኑዛዜው የተደረገው በአራት ምስክሮች ፊት ሣይሆን በሶስት ምስክሮች ፊት ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ የተጠቀሰው ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881/2/ መሠረት ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑ የሚነቀፍ ስላለሆነ ይግባኝ የቀረበበት ውሣኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 881/1/ መሠረት ፀንቷል በማለት ወስኗል፡፡

እዚህ ላይ የአንድ ምስክር ኑዛዜው ሲደረግ አለመኖር የኑዛዜውን ፈራሽነት ማስከተሉ ምን ያህል ሚዛናዊና ፍትሐዊ ነው የሚለውን ክርክር የሚያነሡ ሰዎች አሉ፡፡ ሆኖም ዳኞች በሕጉ በግልጽ የተቀመጠውን

ድንጋጌ ሥራ ላይ የማዋል ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ዳኞች ሕግ የሚተረጉሙት የሕጉ ድንጋጌ ግልጽ ካልሆነ ወይም ክፍተት ያለበት ሲሆን እንጅ በሕግ የተገለፀውን ሁኔታ በርትዕና ሚዛናዊነት ሰበብ ሊጋፉት አይገባም፡፡ በአጭሩ ዳኞች ሕግ ሊተረጉሙ እንጅ በሕግ መተርጎም ሰበብ ሕግ እንዲያወጡና ሕግ አውጭው በግልጽ ያስቀመጠውን የሕግ ድንጋጌ እንዲሽሩ አይፈቅድላቸውም፡፡ በሌላ በኩል የኑዛዜ ፎርሞች አለመሟላት ጥብቅ የሆነ አፍራሽ ውጤት እንደሚያስከትሉ በሕጉ በግልጽ ተቀምጧል፡፡

ስለዚህ ሟች ኑዛዜው ዋጋ እንዲኖረው ከፈለገ በሕጉ የተቀመጠውን ጥብቅ ስርዓት አሟልቶ ኑዛዜውን መተው አለበት፡፡ በመሆኑም የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 881/1/ አለመሟላት ምክንያት በማድረግ በከፍተኛው ና በጠቅላይ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ የኑዛዜ ፎርም የሚደነግጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅና ጥብቅ መሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ የተሰጡ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ሌላውን በትኩረት መታየት ያለበት የኑዛዜ ፎርም አለመሟላት አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 292 የካቲት 16 ቀን 1993 ዓ.ም ይግባኝ ባይ በአቶ አፍወርቅ ደምሴና መልስ ሰጭ በወ/ት እጅግአየሁ ደምሴ መካከል የሰጠውን ውሣኔ ማየቱ የኑዛዜ ፎርም መሟላት ጉዳይ ኑዛዜውን በሕግ ፊት ዋጋ እንዲኖረው ለማድረግ አስፈላጊና አስገዳጅ እንደሆነ ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ ተከራካሪዎቹ የሚከራከሩት በሁለት መሠረታዊ ጉዳዮች ነው፡፡ የመጀመሪያው በውርስ ንብረት ክፍፍል ሲሆን ሁለተኛው አቶ አፈወረቅ ደምሴ ሟች እናቴ ወ/ሮ ዘነበች ቦጋለ ቤቱንና የቤቱን እቃ እኔ እንድጠቀምበት በግልጽ ኑዛዜ አውርሣኛለች በማለት ያቀረበው ክርክርና ማስረጃ ነው፡፡

ጉዳዮን በመጀመሪያ ያየው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭ የሟችን ንብረት እኩል እንዲካፈል ሲወስን፣ ይግባኝ ባይ የሟች የኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ በማለት ያቀረበውን ክርክር ውድቅ አድርጎበታል፡፡ ይግባኝ ባይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሟች ለእኔ ኑዛዜ የተውልኝ ስለመሆኑ የሰነድ ማስረጃውን ሣይመረምርና ምስክሮችን ሣይሰማ መወሰኑ ተገቢ አይደለም በሚልና በንብረት ክፍፍሉ በተሰጠው ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኙን በጠቅላይ ፍርድ ቤት በማቅረቡ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ኑዛዜውን በተመለከተ የይግባኝ ባዩን ሁለት ምስክሮች በማስቀረብ ሰምቷል፡፡ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ምስክሮችን ሲሰማ ከምስክሮቹ አንደኛው አቶ ታደሠ በርቄ የተባለው ሟች ኑዛዜ ስታደረግ በቦታው የነበረው መሆኑን ገልጾ ነገር ግን በኑዛዜው ላይ እንዳልፈረመና በእሱ ስም ፊት ለፊት ያለው ፊርማ የእሱ እንዳልሆነ እሱ በጣት አሻራ ካልሆነ በስተቀር ማንበብና መጻፍ ስለማይችል በጽሑፍ መፈረም እንደማይችል አስረድቷል፡፡

ጉዳዮን ካዩት ሁለት ዳኞችም ይህ የሟች ኑዛዜ የተባለው በሕግ ፊት የፀና እንዲሆን ሕጉ የሚለውን አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት በኑዛዜው ሰነድ ላይ የሟችና የአራት ምስክሮች ፊርማ መኖር አለበት፡፡ በኑዛዜው ላይ የአራት ምስክሮች ስምና ፊርማ በግልጽ ይታያል፡፡ ይሆን እንጅ በኑዛዜው ላይ ስማቸው በአራተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት አቶ ታደሰ ብርቂ ኑዛዜውን ተመልክተው በስማቸው ፊት ለፊት ያለው ፊርማ የእሣቸው አለመሆኑን በዕለቱም በኑዛዜው ላይ አለመፈረማቸውን መጻፍም ሆነ ማንበብ አለመቻላቸውን ገልፀው የምስክርነት ቃላቸውን ሰጥተዋል፡፡ ምስክሩ ፍርድ ቤት ቀርበው በዚህ መልክ እያስረዱ ፊርማው የምስክሩ ፊርማ ነው ተብሎ የሚወሰድበት ምክንያት የለም፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ባይ የሟች ኑዛዜ ነው በማለት በማስረጃነት ያቀረቡት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ፎርማቱን ጠብቆ ያልተዘጋጀ መሆኑ ስለተረጋገጠ የስር ፍርድ ቤት ኑዛዜው ፈራሽ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም በማለት የወሰኑ ሲሆን ሶስተኛው ዳኛ በበኩላቸው በውሣኔው ባስቀመጡት የሐሣብ ልዩነት፣ ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የወሐሮ ዘነበች ቦጋለ ኑዛዜ ሕጉ የሚጠይቀውን መሰፈርት ያሟላ መሆን አለመሆኑን አስመልክቶ ሲመረመር አንዱ ምስክር ያልፈረመበት መሆኑን የመሠከረ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በቦታው ተገኝቶ ኑዛዜ ሲደረግ የሰማ መሆኑን መስከሯል፡፡ የኑዛዜውን ይዘትና የተናዘዙበትን ሁኔታ አስመልክቶ ከሌሎች ምስክሮች ጋር የሚስማማ መልኩ መስክሯል፡፡ የምስክሮች ቃል ከኑዛዜው ጋር በይዘቱ የተስማማ ነው ነገር ግን የቀረበው ኑዛዜ ተናዛዥዋ ያአውራጣት ምልክታቸውን አድርገውበታል ተብሎ የቀረበ ቢሆንም ያውራጣት ምልክት ነው ተብሎ የተቀመጠው ምልክት በእስክርቢቶ የተሞጫጨረ እንጂ በእርግጥም የጣት አሻራ አለመሆኑን በአይን ስመለከተው በግልጽ ለይቸዋለሁ፡፡ ስለዚህ እንደብዙሀኑ ድምጽ ምስክረ አልፈረመበትም በሚል ብቻ ሣይሆን ተናዛዥዋ የአውራጣት ምልክታቸውን ያላደረጉበትም በመሆኑ ጭምር ኑዛዜው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881/3/ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ስላላሟላ ከብዙሀኑ ደምጽ በአካኼድ ብቻ በሐሣብ ተለይቻለሁ በማለት ወስነዋል፡፡

ከላይ ካነሣናቸው በፍርድ ቤት ታይተው ከተወሰኑ ጉዳዮች የምንረዳው አንድ ኑዛዜ በሕግ ማሟላት የሚገባውን ፎርማሊቲ በተሟላ ሁኔታ ካላሟላ ፈራሽ እንደሚሆን ነው፡፡ ምክንየቱም ሕጉ የኑዛዜ ፎርም አስመልክቶ ያስቀመጣቸው ድንጋጌዎች እጅግ ጥበቅና ተናዛዡ በሕይወት ዘመኑ የሚያደርገው ኑዛዜ ከሞተ በኋላ ውጤት እንዲኖረው ከፈለገ ሊከተላቸው የሚገቡ አስገዳጅ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ ተናዛዡ ሕጉ ካስቀመጠው ፎርም አንዷን ሣያሟላ የሚተወው ኑዛዜ ፈራሽ አንደሚሆን አውቆም ሆነ ሳያውቅ የሕጉን ፎርማሊቲ አንዷን እንኳን ሣያሟላ ኑዛዜ ጥሎ ካለፈና በዙዛዜው ተፈጻሚነት ክርክር ከተነሣ ኑዛዜው ፈራሽ ይሆንበታል፡፡ ሰለዚህ የኑዛዜ ፎርም ለኑዛዜ በሕግ ፊት ዋጋ መኖር እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይገባናል፡፡

## 5.3 ኑዛዜው ያልተሻረ ወይም ውድቅ ያልሆነ መሆኑ

አንድ ኑዛዜ በሕጉ የተደነገጉትን የሥረ ነገር ሁኔታዎች አሟልቶ መገኘቱና በሕጉ በተደነገገው ፎርም መሠረት መፈፀሙ ብቻውን ሟች በሞተ ጊዜ ኑዛዜውን ውጤት ለማስጠትና ለማስፈፀም አያስችልም፡፡ በሕጉ የተደነገጉትን የሥረ ነገር ሁኔታዎች በሚሟላት ሕጉ በሚደነግገው ፎርም መሠረት የተፈፀሙ ኑዛዜ ዋጋ የሚኖረው ሟች ኑዛዜውን ያልሻረው ወይም ኑዛዜው ውድቅ ያልሆነ እንደሆነ ነው፡፡

እዚህ ላይ መታየት ያለበት የኑዛዜ መሻር እና የኑዛዜ ውድቅ መሆን አንድና ተመሣሣይ አለመሆናቸው ነው፡፡ የኑዛዜ መሻርና revocation of will የኑዛዜ ውድቅ መሆን lapse of will/ በተለይ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ የተለያዩ ጽንሰ ሀሣቦች ናቸው፡፡

### 5.3.1 የኑዛዜ መሻር /revocation of will/

የኑዛዜ መሻር የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ብዙ የሕግ ሙሁራን በብዙ መንገድ ይተረጉሙታል፡፡ የኑዛዜ መሻር የሚለው ጸንስ ሀሣብ ተናዛዡ ኑዛዜውን ካደረገ በኑላ ያደረገው ኑዛዜ ውጤት እንዳይኖረው አስቦ የሚፈጽመውን ማናቸውንም ድርጊት አጠቃለን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው፡፡

ለግንዛቤአችን ይረዳን ዘንድ በblacks law dictionary የተሰጠውን ትርጉም ብንመለከት፣ Revocation of will is recalling, annulling or rendering inoperative of an existing will by some subsequent act of the testator which may be, by making a new will inconsistent with the terms of the first, or by destroying the old will or by disposing of the property to which it is related or otherwise.
በማለት ይተረጉመዋል፡፡

ኑዛዜ በማናቸውም ጊዜ በተናዛዡ የሚሻር ተግባር መሆኑ ይኸም የኑዛዜ አይነተኛ ባህሪ መሆኑን አይተናል፡፡ ሆኖም ኑዛዜ መሻር የራሱ የሚከተሉት ልዩ ባህሪያት አሉት፡፡
ኑዛዜ ለመሻር በመጀመሪያ በሕግ ፊት ውጤት ያለው ኑዛዜ መኖር ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ማንም ቢሆን የሌለን ኑዛዜ ለመሻርና ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው ለማድረግ አይችልም፡፡

ኑዛዜው መሻር የሚችለው ኑዛዜውን ያደረገው ሰው ብቻ ነው፡፡ ኑዛዜ የመሻር ተግባር በውክልና የሚሠራ ተግባር አይደለም፡፡ በመሆኑም ኑዛዜውን ካደረገው ሰው ፈቃድ ውጭ ኑዛዜውን ሌላ ሰው ሊሽረው

የማይችል በመሆኑ፣ ኑዛዜውን ለመሻር አንድ ሰው ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይኸ ማለት አንድ ሰው ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ችሎታ ካጣ ኑዛዜውን መሻር የማይችል መሆኑ የኑዛዜ መሻር ልዩ ባህሪ ነው፡፡

ተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣኑ ኑዛዜየን አልሽርም ብሎ በሚገባው ማናቸውም ስምምነት ወይም ውል ሊገደብ አይችልም፡፡ ማናቸውም ኑዛዜን ላለመሻር የሚደረግ ውል በሕግ ፊት ውጤት የማይኖረው መሆኑ ተናዛዡ ያደረገውን ኑዛዜ ሙሉ በሙሉ ወይም ከፈፀመው የኑዛዜ ውስጥ ግማሹን ወይም አንዷን ክፍል ብቻ በመሻር ሌላው የኑዛዜ ክፍል ለመተው የሚችል መሆኑ ናቸው፡፡

ተናዛዡ ኑዛዜው የሚሽረው በሁለት አይነት መልኩ እንደሆነ በውርስ ሕግ ዙሪያ የተጻፉ በርካታ ጽሑፎች ያሣያሉ፡፡ ይኸም፣ኑዛዜውን በግልጽ በመሻር/ Express Revocation/ እና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፈፀም የኑዛዜ መሻር implied revocation ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ከላይ ያነሣናቸውን የኑዛዜ መሻር ልዩ ባህሪያትና ኑዛዜ በግልጽና በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሻርበትን ሁኔታ አካትቶ እናገኘዋለን፡፡

ሀ. <u>በግልጽ ኑዛዜን ስለመሻር</u>

በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ተናዛዡ በሁለት አይነት መንገድ ኑዛዜውን በግልጽ ለመሻር ይችላል፡፡ የመጀመሪያው ተናዛዡ ኑዛዜዎቹ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም ዓይነት ግልጽ አድርጐ በማሣወቅ ኑዛዜውን የሻረው እንደሆነ ነው፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898/1/ በግልጽ እንደተመለከተው በዚህ አኳኋን ተናዛዡ ኑዛዜው በግልጽ ለመሻር እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ ኑዛዜዎቹ፣ ዋጋ ያላቸው እንደሆኑ በሚያስፈልገው ፎርም የሚለው አባባል መታየት አለበት፡፡ ይኸ ማለት በቃል የተደረገን ኑዛዜ በቃል ኑዛዜ በግልጽ የተደረገን ኑዛዜ በግልጽ በተደረገ ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገን ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሁፍ በተደረገ ኑዛዜ ፎርም ዓይነት ብቻ ነው መሻር የሚችለው ተብሎ መተርጐም አለበት ወይስ፣ ከዚህ ሰፋ ባለ ሁኔታ በግልጽ የተደረገን ኑዛዜ በእጅ ጽሑፍ በተደረገ ፎርም የሚለው አከራካሪ ነጥብ ነው፡፡

የኑዛዜ መሠረታዊ ባህሪ ተናዛዡ በፈለገ ሠዓት ሊሽረው የሚችለው ከመሆኑ አንጻር በተናዛዡ ኑዛዜውን የመሻር ስልጣን በሚያጣብብ መልኩ የሕጉ ድንጋጌ መተርጐም የለበትም፡፡

በዚህ አንጻር ስናየው በግልጽ ያደረገውን ኑዛዜ በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ ኑዛዜ ለማድረግ ማሟላት የሚገባቸውን ፎርማሊቲዎች አሟልቶ ቀደም ሲል ያደረገውን ኑዛዜ በግልጽ እስከሻረ ድረስ ሟች ከሞተ በኋላ እንዲፈጽም የማይፈልገውን ኑዛዜ የሕጉን ድንጋጌ አጥብቦ በመተርጐም ውጤት መስጠቱ ተገቢ

አይሆንም፡፡ በመሆኑም በቃል የተደረገን ኑዛዜ በእጅ ጽሑፍ ወይም በግልጽ በተደረገ ኑዛዜ ፎርሞ በማሟሎት ለመሻር ሌሎቹንም በዚሁ አይነት መንገድ ለመሻር ይችላል የሚል አተረጓጎም የሚከተሉ አሉ፡፡ ሁለተኛው መንገድ ተናዛዡ በግልጽ ቀደም ሲል አድርጎት የነበረውን ኑዛዜ የሚሽርበት መንገድ ከፊተኛው ኑዛዜ ጋር አብሮ ሊፈፀም የማይችል ሌላ ኑዛዜ ያደረገ እንደሆነ ነው፡፡

ብዙ ኑዛዜዎች አንድ ሰው ባደረገ ጊዜ ኑዛዜዎቹ አብረው ተፈጻሚ የማሆኑ ከሆነ አብረው ሊፈፀሙ የሚችሉበት መጠን አብረው ተፈጻሚወች አንደሚሆኑና የሁለቱ ኑዛዜዎች ቃላት ተጣጥመው ሊፈፀሙ ያልተቻለ እንደሆነ በኑላ የተደረገው ኑዛዜ ውስጥ ላለው ቃል ምርጫ እንደሚሰጥ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898 ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም በኑላ የተደረገው ኑዛዜ በፊት ከተደረገው ኑዛዜ ጋር የሚቃረን ከሆነ ተናዛዡ ኑዛዜውን በግልጽ እንደሻረ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898/2 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ የሌሎች አገር ህጐች በዚህ ዓይነት የሚደረግ የኑዛዜ መሻርን ተግባር በተዘዋዋሪ የተደረገ የኑዛዜ መሻር /implied revocation of will/ በማለት የሚሰይሙት ቢሆንም በኢትዮጵያ ውርስ ሕግ ደግሞ ግልጽ የሆነ የኑዛዜ መሻር በሚለው ርእስ እንደተካተተ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 898 ተደንግጓል፡፡

/ለ/ <u>በተዘዋዋሪ መንገድ ኑዛዜን ስለመሻር</u>

ተናዛዡ ኑዛዜውን የሚሽርበት ሌላው መንገድ ኑዛዜዋ ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርጉ ሌሎች ተግባራትን በመፈፀም በተዘዋዋሪ መንገድ በመሻር ነው፡፡ ተናዛዡ ኑዛዜውን ለመሻር ወይም ለመለወጥ ያለውን ሀሣብ በቂ አድርጐ በመግለጽ አይነት ኑዛዜውን ራሱን በማጥፋት በመቅደድ የኑዛዜውን አነጋገር በመሠረዝ ኑዛዜውን ወይም ኑዛዜው ውስጥ የተመለከተውን አንድ ቃል ለመሻር ይችላል፡፡ ተናዛዡ በሕግ የሚፀና ኑዛዜ ካደረገ በኑላ ከላይ የተጠቀሱትን ግዙፍ ተግባራት /Physical act/ ባደረገው ኑዛዜ ላይ ከፈፀመ ኑዛዜውን እንደሻረ እንደሚቆጠርና ተናዛዡ እነዚህን የሀይል ተግባራት በፈፀመ ቁጥር ኑዛዜውን የመሻር ፍላጐት አለው ተብሎ እንደሚገመት እንደዚሁም የኑዛዜው መጥፋት ወይም መሠረዝ የተናዛዡ ተግባር ነው ተብሎ እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 899/2 እና 899/3/ የሚደነግጉ ሲሆን በእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች የተቀመጠ የሕግ ግምቶች ሊስተባበሉ የሚችሉ የሕግ ግምቶች በመሆናቸው ተቃራኒ ማስረጃ በማቅረብ ለማስተባበልና ሟች ኑዛዜውን ያልሻረው መሆኑን ለማስረዳት እንደሚቻል መገንዘብ ይገባል፡፡ ሌላው ተናዛዡ ኑዛዜውን በተዘዋዋሪ የሚሽርበት መንገድ በኑዛዜ የተሰጠን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ተናዛዡ ፈቅዶ ለሌላ ሰው ያስተላለፈው እንደሆነ ነው፡፡ እዚህ ላይ ንብረቱን ለሌላ ሰው ማስተላለፍ የሚለው ተናዛዡ በስጦታ ወይም በሽያጭ ወይም በሌላ መንገድ የንብረቱን የባለቤትነት መብት ለሌላ ሰው ያስተላለፈው እንደሆነ ነው፡፡

ተናዛዡ በኑዛዜ ውስጥ በስጦታ የሰጠውን ንብረት ባለቤትነት ለሌላ ሶስተኛ ወገን ካስተላለፈ ኑዛዜው ተፈጻሚ እንዳይሆን ግልጽ ሀሣብ ያለው መሆኑን ስለሚያሣይ የንብረቱ ባለቤትነት ተመልሶ በእሱ እጅ ቢገባም ተናዛዡ በመጀመሪያ ያደረገው ኑዛዜ ውጤት እንደማይኖረው እና ኑዛዜውን በተዘዋዋሪ መንገድ እንደሻረው እንደሚቆጠር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 900 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ እንደዚሁም ኑዛዜውን የሻረው ኑዛዜ በድጋሚ መሻሩ የበፊቱን ኑዛዜ እንዲሠራ/ ዋጋ እንዲኖረው አያደርግም፡፡

5.3.2 **<u>የኑዛዜ ውድቅ መሆን/Lapse of will/</u>**

የኑዛዜ ውድቅ መሆን ወይም /Lapse of will/ የሚለውን ጽንሰ ሀሣብ ከኑዛዜ መሻር ጋር አንድ አድርጐ የመመልከት ችግር አለ፡፡

በስነ ሕግ ጥናት ውስጥ "lapse'' የሚለው ቃል The terminiation or failure of a right or a priviledge through neglect to exercise it within some limit of time or through failure of some contingence' ማለት ነው፡፡ የኑዛዜው ውድቅ መሆን ስንል አንድ ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ ሕጉ በሚያዝዘው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተናዛዡ ማድረግ የሚገባውን ባለማድረጉ ወይም ተናዛዡ ኑዛዜ ከተፈፀመ በኋላ አንድ ክስተት በመፈጠሩ፣ ኑዛዜው ሕጋዊ ውጤት እንዳይኖረው ሕጉ ክልከላ ሲያደርግበት ነው፡፡

ኑዛዜን መሻር በተናዛዡ የሚፈፀም ተግባር ሲሆን ኑዛዜ ውድቅ የሚሆነው ደግሞ በውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ግልፅ ትዕዛዝ ነው፡፡ በመሆኑም የኑዛዜ ውድቅ መሆን ምንጩና መሠረቱ የሕጉ ድንጋጌ ነው፡፡ በአጠቃላይ አንድ ኑዛዜ ውድቅ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች የሚያስቀምጠው ሕግ አውጭው ነው፡፡ በኢትዮጵያ የውርስ ሕግ ውስጥ ኑዛዜ ውድቅ ሊሆን የሚችልባቸው በርካታ ምክንያቶች ተቀምጠዋል፡፡ የመጀመሪያው ተናዛዡ በሕግ እንዲፈጽም የታዘዘውን ድርጊት ባለመፈፀሙ የሚመጣ ነው፡፡ ኑዛዜው የተደረገው በተናዛዡ የእጅ ጽሁፍ በሆነ ጊዜ ኑዛዜው በተደረገ በሰባት ዓመት ውስጥ ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም ፍርድ መዝገብ ቤት ዘንድ ያልተቀመጠ እንደሆነ ውድቅ ሊሆን እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 907 ይደነግጋል፡፡ ሌሎቹ ምክንያቶች ኑዛዜው ከተደረገ በኋላ የተከሰቱትን ክስተቶች የሚመለከቱ ናቸው፡፡ እነርሱም፣

- ተናዛዡ ኑዛዜ ካደረገ በኋላ ልጅ ከወለደ ወይም አንድ ተወላጅ ተወልዶ በተተኪነት ውርሱን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆነ፣
- ባል ለሚስቱ ወይም ሚስት ለባሏ ኑዛዜ ካደረጉ በኋላ ጋብቻው በሞት ሣይሆን በሌላ ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ፣

- ኑዛዜ የተደረገለት ሰው ከተናዛዡ በፊት የሞተ ወይም ኑዛዜውን ለመቀበል ያልቻለ ወይም ያልፈቀደ እንደሆነ፣

መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 902 እና 904 እስከ 907 የተደነገጉት ድንጋጊዎች ያስረዳሉ፡፡

እዚህ ላይ ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ሟች ኑዛዜ ካደረገ በኑላ ልጅ ቢወለድም ዳኞች ኑዛዜውን አይተው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 905 ድንጋጌዎች መሠረት ኑዛዜ በከፊል ውጤት እንዲኖረው የማድረግ ስልጣን እንዳላቸውና ከተናዛዡ በፊት የሞተው ሰው ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሲሆን የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ከሟች ቀደም ቢሞትም የእሱ ተተኪዎች በውርሱ ሊካፈሉ እንደሚችሉ፣ እንደዚሁም ኑዛዜ ተጠቃሚው ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተደርጐለት ከሆነ ሟች የስጋ ዘመድ ወራሽ በማጣቱ ንብረቱ ለመንግስት የሚገባ በሆነ ጊዜ የልዩ የኑዛዜ ስጦታ ተጠቃሚው ወራሾች እሱን ተክተው በሟች ውርስ ሊካፈሉ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 908 የተደነገገ መሆኑን ነው፡፡

## 5.4 ኑዛዜ መኖሩን ስለማስረዳት

አንድ ሰው በአንድ ሰነድ ወይም በአንድ ተግባር ውስጥ እሱን የሚመለከት መብት ሊኖረው ይችላል፡፡ በተመሣሣይ መልኩ ሟች በሕይወት ዘመኑ በአደረገው ኑዛዜ ውስጥ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሚሆንበት በርካታ አጋጣሚ አለ፡፡ ዋናውና ትልቁ ነገር ሟች በሕይወት ዘመኑ በአደረገው ኑዛዜ እሱ የኑዛዜ ተጠቃሚ መሆን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት እና ለማረጋገጥ ካልቻለ መብት እያለው በመብቱ ጠቃሚ የማይሆንበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

የኢትዮጵያ የሲቪል ሎው የሕግ ስርአት ተከታይ ከሆኑት አገሮች አንደኛዋ በመሆኗ አንድ ጉዳይ ለማስረዳት መቅረብ የሚገባውን የማስረጃ አይነትና የማስረዳት ሀላፊነት ያለበት ተከራካሪ ወገን የሚወስኑ ዝርዝር የማስረጃ ሕግ ደንቦች በተበታተነ ሁኔታ ተደንግገው ይገኛሉ፡፡

የኑዛዜውን ቃልና ይዘት አስመልክቶም ማን ማስረዳት እንዳለበትና ምን አይነት ማስረጃዎች ማቅረብ እንደሚገባው በውርስ ሕግ ውስጥ ልዩ ድንጋጌዎች ተደንግገው እናገኛለን፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 896 መሠረት አንድ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ሟች በሕይወት ዘመኑ ለእሱ ጥቅም ያደረገው ኑዛዜ መኖሩንና የኑዛዜው ቃልና ይዘት ምን እንደሆነ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ስለዚህ ምን ጊዜም የሟች የኑዛዜ ወራሽና ተጠቃሚ ነኝ የሚል ሰው

- ሟች በሕግ ፊት ውጤት ያለው ኑዛዜ የፈፀመ መሆኑን፣
- የኑዛዜውን ቃልና ይዘት፣
- እንደዚሁም እሱ በሟች ኑዛዜ ውስጥ ተጠቃሚ መሆኑን፣

የማስረዳት ሸክም /Burdon of proof/ አለበት፡፡

የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ኑዛዜ መኖሩን እና የኑዛዜውን ቃል የማስረዳት ሸክም ያለበት ማን እንደሆነ በመደንገግ ብቻ አላቆሙም፡፡ የሕጉ ድንጋጌዎች ለምን አይነት ኑዛዜ ምን አይነት ማስረጃ መቅረብ እንዳለበት ጥብቅ የሆነ መስፈርት አስቀምጠዋል፡፡

በመሆኑም በግለጽ የተደረገ ኑዛዜ ወይም በተናዛዡ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ መኖሩን ለማረጋገጥ የኑዛዜው ጽሑፍ ዋናው ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ መዝገብ ሹም ትክክለኛ ሆኖ የተመሰከረ አንድ ግልባጭ መቅረብ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/1/ ይደነግጋል፡፡ ከሕጉ ድንጋጌ የምንረዳው በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ ወይም በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜ ለማስረዳት በመጀመሪያ መቅረብ የሚገባው የኑዛዜው ዋና ሰነድ ወይም original/primary document/ መሆኑን ነው፡፡

የሕጉ ድንጋጌ ዋናው ሰነድ primary document በሌላ ጊዜ የዋናው ሰነደ ትክክለኛ ግልባጭ ወይም ኮፒ መሆኑ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም የተረጋገጠ ' Certified copy of the origional document' በማስረጃነት ሊቀርብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

ከእነዚህ ከሁለቱ የማስረጃ አይነቶች ውጭ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜን ወይም በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜን ለማስረዳት አይቻልም፡፡ ይኸም ማለት ትክክለኛነቱ ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ሰው ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ያልተረጋገጠ ፎቶ ኮፒ ወይም ግልባጭ በማቅረብ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜን ወይም በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገ ኑዛዜን ለማስረዳት አይቻልም፡፡ ይህንንም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/2/ እጅግ ጥብቅና ጠንካራ በሆነ አገላለጽ ኑዛዜዎችን ለማስፈፀም በማናቸውም ሌላ መንገድ ማስረዳት አይቻልም በማለት ደንግጐታል፡፡

ሌላው መነሣት ያለበት ጥያቄ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/3/ ምን ለማድረግ እንደገባ እና ሕግ አውጭ ይህንን ድንጋጌ በማስገባት ምን ግብ ሊመታ እንዳሰበ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/3/ አንድ የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆነ ሰው ለመብቱ ማስረጃና ማረጋገጫ የሆነውን የኑዛዜ ሰነድ አንድ ሰው ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት ቢያጠፋበት፣ ቢቀድበት ወይም ቢያቃጥልበት የኑዛዜ ሰነዱን ባያጠፉት ኖሮ፣ ከሟች ውርስ ኑዛዜውን በማስረጃነት አቅርቦ ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም ያስቀረቡትና ኑዛዜውን ያጠፉበት

ሰው በኑዛዜው ከሟች ውርስ ሊያገኝ የነበረውን ጥቅም ያህል ካሣ እንዲከፍለው ክስ ሲያቀርብ ኑዛዜውን በማስረጃነት እንዳይቀርብ አድርጐ ባጠፋበት ሰው ላይ ይህንን ጥፋቱን ሊያስረዱ የሚችል ማናቸውንም አይነት ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችል የሚደነግግ የሕግ ድንጋጌ ነው፡፡

ለምሣሌ አቶ ከበደ ተሰማ ለጓደኛቸው አበበ ዓለሙ 500000 ብር የሚያወጣ ማርቸዲስ የቤት መኪና በእጁ ጽሑፍ ባደረጉ ኑዛዜ ቢያወርሱና አቶ ከበደ ከሞቱ በኀላ ታላቅ ልጃቸው ወንድወሰን ከበደ ይህንን የሟች ኑዛዜ አቶ አበበ እንዳያገኙትና በማስረጃነት እንዳይጠቀሙበት በማሰብ በእሣት ቢያቃጥለው፣ አቶ አበበ ዓለሙ የኑዛዜው ዋና ሰነድ ወይም አግባብ ባለው ባለስልጣን የተረጋገጠ ኮፒ ስለሌላቸው በሟች ከበደ ተሰማ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ወራሽ ሆነው ለመቅረብ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/1/ እና 897/2/ መሠረት ኑዛዜውን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚቻል ማስረጃ የላቸውም፡፡ ሆኖም አቶ አበበ ዓለሙ የብር 500000 ካሣ አቶ ወንድወሰን እንዲከፍላቸው ክስ ማቅረብና ይህንንም ለማስረዳት ወንድወሰን የኑዛዜውን ሰነድ ሲያቃጥል ያዩ ምስክሮችን፣ ሟች ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ወራሽ ያደረጋቸው መሆኑን የሚያስረዳላቸውን ማናቸውንም አይነት ማስረጃ ማቅረብ እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897ሐ3ሐ ይደነግጋል፡፡ በዚህም ሕግ አውጭው ሆነ ብለውም ሆነ በቸልተኝነት የሟችን ኑዛዜ የሚያጠፉ ሰዎች ይህንኑ ጥፋታቸውን ሊያስረዳ የሚችል ማናቸውም አይነት ማስረጃ እንደሚቀርብባቸውና በጥፋታቸውም ተጠያቂ እንዲሆኑ በመደንገግ ከወዲሁ የሟችን ኑዛዜ በጥንቃቄ መያዝ እንዳለባቸው የማስጠንቀቅና ይህንንም ሲተላለፍ ተጠያቂ የማድረግ ሀሣብና ፍላጐት እንዳለው ያሣያል፡፡ የቃል ኑዛዜንም አስመልክቶ ሕጉ በዝምታ ያለፈው ቢሆንም ተናዛዡ የቃል ኑዛዜ ሲያደርግ የነበሩና የሰሙ ሰዎችን በማቅረብ ማስረዳት እንደሚቻል ግልጽ ነው፡፡

በአጠቃላይ ኑዛዜ ያለ መሆኑንና የኑዛዜውን ቃልና ይዘት የማስረዳት ሸክም ያለበት የኑዛዜ ተጠቃሚው መሆኑ፣ በግልጽ የተደረገ ኑዛዜ እና በተናዛዡ እጅ ጽሑፍ የተደረገን ኑዛዜ ለማስረዳት የሚችለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 897/1/ የተመለከቱትን ማስረጃዎች ብቻ በማቅረብ መሆኑ ግንዛቤ ሊያዝበትና በአፈጻጸምም ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ፡ በጽሑፍ ማስረጃን ይዘት በቃል ምስክር ማስረዳት ከመሠረታዊ የማስረጃ ሕግ መርህ አንጻር ተገቢ ነው ወይ? የሚለው ሲሆን በተለይም ደግሞ ሟች ከሞተ በኂላ ውጤት በሚኖረው ኑዛዜ በቃል ለማስረዳት እንዴት ሊፈቀድ ይችላል፡፡ የኑዛዜው ይዘቱ ብቻ ሣይሆን ፎርሙን ያሟላ መሆኑንስ ሰነዱ በሌለበት ሁኔታ እንዴት በሰው ምስክር ማስረዳት ይቻላል? የሚሉት ነጥቦች አከራካሪዎች ናቸው፡፡

በመሆኑም እንኳን ሰነዱ በሌለበት ሁኔታ ሰነዱ ቀርቦ ኑዛዜው በሕጉ የተቀመጠውን ፎርም ካላሟላ ውጤት የማይኖረው በመሆኑና ሰፊ ክርክር የሚያስነሣ በመሆኑ ኑዛዜን አስመልክቶ የሚነሱ መጠነ ሰፊ ክርክሮች እና ሊሰጥ የሚችለውን ብይን የበለጠ ለመገንዘብ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ፍርድ እንመልከት፡፡

የክርክሩ መነሻ አቶ አየለ ታምራት በህይወት በነበሩበት ዘመን የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም በጽሁፍ አድርገዋል የተባለውን ኑዛዜ ነው፡፡ ኑዛዜው በታይኘ ተጽፎ የቀረበ ነው፡፡ አቶ አየለ ታምራት ኑዛዜውን አደረጉ የተባለው የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም ይሁን እንጂ የሞቱት የካቲት 3 ቀን 1985 ዓ.ም ተናዘዙ በተባለ በአምሥተኛው ዓመት ላይ ነው፡፡ የኑዛዜው ተጠቃሚ ነኝ በማለት በኑዛዜው ጽሁፍ ላይ የተዘረዘሩትን ንብረቶች ባለመብት ለመሆን እንዲያስችላት ኑዛዜው ፀድቆ የኑዛዜ ወራሽነቷን የሚያረጋግጥ ምሥክር ወረቀት እንዲሰጣት፣ በኑዛዜው ላይ በተገለፀው መልኩ የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ሚስት ስለመሆኗ በፍርድ ቤት ተረጋግጦ እንዲታወቅላት፣ ከሟች አቶ አየለ ታምራት ጋር በባልና ሚስትነት አብረን ስንኖር ተወልዷል የምትለው ህፃን ክንፈሚካኤል የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ልጅና ወራሽ ነው ተብሎ እንዲወሰንላት፣ በኑዛዜውም ወራሽ ነው እንዲባል አቤቱታ ጽፋ ለወረዳ 13 ፍርድ ቤት በማመልከት ፋይል ያስከፈተችው የአሁኗ መልስ ሰጪ ወ/ሮ አልማዝ ሃይለመስቀል ናት፡፡

በሌላም በኩል የአሁን ይግባኝ ባዩች በበኩላቸው የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት የመጀመሪያ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች መሆናቸውን በፍርድ ቤት ውሣኔ ተረጋግጦ እንዲታወቅላቸው ለወረዳው ፍ/ቤት አመልክተው ፋይል እንዲከፈትላቸው አድርገዋል፡፡

የሟች ሚስት ነኝ ለምትለው ለወ/ሮ አልማዝ ሃይለመስቀልና ከእርሷ ለተወለደው ልጅ አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ እንዲፀድቅ የእርሷም ሚስትነት እንዲረጋገጥ እና ክንፈሚካኤል የተባለው ልጅም የሟች ልጅ ስለመሆኑ እንዲወሰን የሚል አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረቧን ይግባኝ ባዩች እንደሰሙ ባስከፈተችው መዝገብ ላይ ተቃዋሚ በመሆን ቀርበው ተፈቅዶላቸው በርካታ የሕግ ክርክሮችን በማቅረብ ኑዛዜው ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ስለመሆኑ፣ መልስ ሰጪም ከሟች አባታቸው ጋር አብራ የነበረችው በቤት ሠራተኛነት እንጂ ተጋብተው በባልና ሚስትነት ያለመሆኑን፣ ከሟች ወልጃለሁ የምትለው ልጅ የልጅነት ጉዳይም በወረዳ ፍርድ ቤት ደረጃ ታይቶ የማይወሰን መሆኑን በመዘርዘር ያቀረበችውን ጥያቄዎች በመቃወም ተከራክረዋል፡፡

ወረዳ ፍ/ቤትም ሁለቱን መዝገቦች በማጣመር ሲያይ ከቆየ በኁላ መጋቢት 8 ቀን 1986 ዓ.ም በዋለው ችሎት መርምሮ በሰጠው ውሣኔ ሟች አድርገዋል የተባለውን ኑዛዜ በብዙ መልኩ ተቀባይነት የማይሰጠው ስለመሆኑ ተችቶ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሲያደርገው፣ የሟች ሚስት መሆኔ ይታወቅ ብላ ወ/ሮ አልማዝ

ሃይለመስቀል ያቀረበችውን ጥያቄ በተመለከተም ከሟች ጋር አብረሽ የነበርሽው በቤት ሠራተኛነት እንጂ ጋብቻ በመፈፀም በባልና ሚስትነት ስላልሆነ ሚስት አይደለሽም ብሎ ሲውሰነ፣ ክንፈሚካኤል የተባለው ሟች አባቱ ስለመሆናቸው ይወሰን የተባለውን በሚመለከትም የተወለደው ከጋብቻ ውጭ ስለሆነ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ነው ቀርቦ መታየት ያለበት በማለት በአጠቃላይ የአሁኗ መልስ ሰጪ ያቀረበቻቸውን ጥያቄ ሣይቀበላቸው የቀረ ሲሆን ይግባኝ ባዩች የሟች የአቶ አየለ ታምራት ህጋዊ ወራሾች ስለመሆናቸው ተረጋግጦ እንዲወሰን ያቀረቡትን ጥያቄ ግን በመቀበል ወራሽ ናቸው ሲል ወስኗል፡፡

የአሁኗ መልስ ሰጪ ይህንኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመቃወም ግንቦት 1 ቀን 1986 ዓ.ም በተፃፈ የይግባኝ ማመልከቻ በወቅቱ ለነበረው ለክልል 14 መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት የይግባኝ ክርክሯን በማቅረብ ተከራክራለች፡፡ ዞን ፍ/ቤትም ለይግባኙ በተከፈተው ቁጥሩ 928/86 በሆነው መዝገብ ላይ የአሁኑ ይግባኝ ባዩች ለቀረበው የይግባኝ ቅሬታ መልስ እንዲሰጡበት በማድረግ አከራክሯል፡፡ የአሁኗ መልስ ሰጪ በሥር ባቀረበችው ክርክር ይግባኝ ባዩች የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ህጋዊ ወራሽ መሆን አይችሉም የሚል ክርክር አልነበራትም፡፡ የመልስ ሰጪ ዋና ጥያቄና ክርክር ሟች የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም በጽሁፍ አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ እንዳለ መጽደቅ አለበት፡፡ የክንፈሚካኤል ሞግዚት መሆኔ ተረጋግጦ መወሰን አለበት የሚል ነው፡፡ ባቀረበችው የይግባኝ ማመልከቻ ላይ ስለሚስትነቷ ጉዳይ ብዙም ትኩረት አላደረገችም፡፡ ክንፈሚካኤል የተባለው ልጅ አባት አቶ አየለ ታምራት ናቸው ተብሎ መወሰን አለበት ስትል ለወረዳው ፍ/ቤት ያመለከተችውንም በይግባኙ እምብዛም ስታነሳው አልታየም፡፡

ዞን ፍ/ቤትም በመጨረሻ መርምሮ በሰጠው ውሣኔ በህጋዊ ጋብቻ የተወለዱት የሟች አራቱ ልጆች፣ ሚስት ነኝ ስትል የነበረችው ወ/ሮ አልማዝ ሃይለመስቀል እንዲሁም ከእርሷ የተወለደው ክንፈሚካኤል የተባለው ልጅ በጠቅላላው ስድስቱም ሰዎች በእኩል ሁኔታ የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ወራሾች ይሆናሉ በሚል ድምዳሜ ላይ ይድረስ እንጂ ኑዛዜ በተባለው ነገር ሙሉ በሙሉ አላመነበትም፡፡ ኑዛዜ የተባለው ነገር በሕጉ ምንያህል ተቀባይነት እንዳለውና በሕጉ እይታ በትክክል ኑዛዜ ሊሰኝ ስለመቻሉ ብዙም ያለው ነገር ሣይኖር አልፎ ኑዛዜው የሟች ልጆችን ከውርስ የማግለል ይዘት ስላለው እንዳለ ለመቀበል አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ኑዛዜው ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሊደረግ ስለማይችል ሁሉንም በአንድ የወራሽነት ዘንግ በማሰለፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይሻላል ብሎ ኑዛዜውን በከፊል በመቀበል ሁሉንም ሰዎች የሟች የመጀመሪያ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች አድርጓቸዋል፡፡

ይግባኙ ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ ይግባኝ ባዩች ሟች የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ ፍጹም ሀሰት እና ከሕጉ ውጭ ተቀነባብሮ ተዘጋጅቶ የቀረበ ስለሆነ በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ አይደለም፡፡ መልስ ሰጪም ሆነች ከእርሷ የተወለደው ልጅ ከእኛ እኩል

የአባታችን የሟች አቶ አየለ ታምራት ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ዞን ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም ማስረጃ እና ሕጉን ያላገናዘበ ስለሆነ መሻር አለበት ባዩች ናቸው፡፡

መልስ ሰጪ ሐምሌ 13 ቀን 1992 ዓ.ም ጽፋ ባቀረበችው መልስ ሟች አቶ አየለ ታምራት የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም በጽሁፍ ያደረጉት ኑዛዜ የሚሻርበት አንዳችም የሕግ ምክንያት ያለመኖሩን፣ ይግባኝ ባዩችም ኑዛዜውን መሰረዝ አለበት ብለው ከመከራከር ውጭ መሠረዝ ይገባዋል የሚሉበትን ምክንያት በተጨባጭ ለማስረዳት ያለመቻላቸውን፣ ዞን ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔም ምንም አይነት ጉድለት የሌለበት መሆኑን በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ ይግባኝ ባዩች በበኩላቸው ጥቅምት 22 ቀን 1993 ዓ.ም የመልስ መልሱን ጽፈው በማቅረብ ይግባኙን በሚያጠናክር መንገድ ተከራክረዋል በማለት የክርክሩን ሂደት ከተነተነ በኋላ ፍርድ ቤቱ በሰጠው ትችት በእኛም በኩል የግራቀኙን ክርክር በመመርመር እንደተገነዘብነው በዚህ መዝገብ ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባው አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጭብጥ ሟቹ አቶ አየለ ታምራት የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም በጽሁፍ አድርገዋል የተባለውን ኑዛዜ በሕጉ አግባብ የተፈፀመና ተቀባይነት የሚሰጠው ነው ወይንስ ከሕጉ ውጭ ነው ተብሎ ፈራሽ የሚሆን ነው የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

አቶ አየለ ታምራት የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም በጽሁፍ ተናዘዋል ከተባለ በኍላ ለአምስት አመታት ያህል በህይወት ሲኖሩ ቆይተው የሞቱት የካቲት 3 ቀን 1985 ዓ.ም መሆኑ ተነግሯል፡፡ ኑዛዜ ነው ተብሎ በቀረበው ጽሁፍ ላይ በአብዛኛው ያላቸውን ሃብትና ንብረት ለወ/ሮ አልማዝ ሃይለመስቀልና ከእርሷ ለተወለደው ክንፈማካኤል ለተባለው ልጅ እንዲወርሱ የተናዘዙላቸው ሆኖ ይታያል፡፡

ይግባኝ ባዩች የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ልጆች ስለሆኑ በሕጉ የመጀመሪያ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች ናቸው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ህጋዊ ወራሾች ደግሞ ያለ ኑዛዜ ወራሾች ናቸው፡፡ አቶ አየለ ታምራት እነዚህን አራት ልጆች ያላቸው መሆኑን እየታወቀ መልስ ሰጪ ኑዛዜ ነው ብላ ባቀረበችው ጽሁፍ ላይ አንደኛዋ ይግባኝ ባይ ለወ/ሮ ጽጌረዳ አየለ ለመታሰቢያ ያህል የጣቱን ወርቅ እንዲሁም ለ4ኛው ይግባኝ ባይ ለአቶ መልኬ አየለ የሚኖርበት አንድ ክፍል ቤትና አቶ አበበ መሸሻ የሚተኛበትን ክፍል ቤት ሰጥቻለሁ ብለዋል ተብሎ ከመፃፉ ውጭ ቀሪዎቹ ሁለት ልጆች ማለትም 2ኛ እና 3ኛ ይግባኝ ባይ ይጡ ወይም ያግኙ የተባለ ነገር የለም፡፡ ለ1ኛዋ ይግባኝ ባይ ተናዘዋል የተባለውም ቢሆን ለመታሰቢያ ያህል የጣት ወርቅ እንደሰጧት ተደርጎ የተፃፈ እንጂ ከዋናው የሟች ሀብት የተሰጣት ምንም ነገር የለም፡፡ አለ የተባለውን ንብረት አወረሱ የተባለው ለአሁኗ መልስ ሰጪ እና ከእርሷ ለተወለደው ክንፈሚካኤል ለተባለው ልጅ ነው፡፡ 2ኛ እና 3ኛ ይግባኝ ባይ የሟች ልጆች መሆናቸው እየታወቀና ከውርሱም የተገለሉበት ምክንያት ሣይነገር በዝምታ ከውርሱ ተነቅለዋል፡፡

ከዚሁ ስንነሣ መልስ ሰጪ ሟች አድርገዋል ብላ ያቀረበችው ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 939/2/ መሠረት የሟቹን ልጆች ከወራሽነት መንቀልን አያስከትልም።በሌላም በኩል በኑዛዜው ፎርምና አሰራር በኩል ያለውን ስንመረምር መልስ ሰጪ ሟች የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም አድርገዋል ብላ ያቀረበችው የጽሁፍ ኑዛዜ ነው። በጽሁፉ ላይ እንደተገለፀው ሟች እንደተናገሩ ተረቆ ከተፃፈ በኋላ እንደገና ወደሌላ ቦታ ተወስዶ በታይፕ ተዘጋጅቶ ቀርቦ ተመልክተውት ትክክለኛ ቃል ነው ብለው በፊርማቸው አረጋግጠዋል። በመጀመሪያ የኑዛዜ ቃሌን ተቀብለው አናዘዙኝ የሚሉት የንስሃ አባታቸው አባ ደስታ ካሣዬን ነው። በማናዘዝ ቃሌን ተቀበሉኝ ያሉትም አራት ምሥክሮች ባሉበት ሲሆን ምሥክሮቹም ሟች ሲናዘዙ አይተን ሰምተን ፈርመናል ብለዋል። በጽሁፉ መግቢያ ላይ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 880/ሀ/ እና 881 /2/ መሠረት መሆኑ ተጠቅሷል።

ሟች አድርገዋል ተብሎ የቀረበው ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 ላይ የተገለፀው በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ፣፣ አይነት መሆኑ ነው። በግልጽ የሚደረግ ኑዛዜ ደግሞ ተናዛዡ እየተናገረ ማናቸውም ሌላ ሰው ወይም ተናዛዡ ራሱ የሚጽፈው ነው። ሕጉ ኑዛዜው በተናዛዡና በአራቱ ምሥክሮች ፊት ካልተነበበና ይኸው ሥርዓት /ፎርማሊቲ/ መፈፀሙንና የተፃፈበትንም ቀን የሚያመለክት ካልሆነ በቀር ፈራሽ እንደሚሆን፣ ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት እንደሚፈርስ ያስረዳል። ኑዛዜ ተብሎ የቀረበውን ጽሁፍ ደግሞ ስንመለከተው ከአፈፃፀም ሲጀምር ሟች በቀጥታ በራሣቸው አንደበት ምሥክሮች ቁጭ ብለው እየሰሟቸው ራሣቸው እየተናገሩ የፃፉት ወይም ሌላ ሰው አጠገባቸው ሆኖ አራቱ ምስክሮች ባሉበት እየተናገሩ ቃል በቃል የፃፈው ስለመሆኑ አያስረዳም። እኔ እየተናገርኩ ጽሁፉ ተረቆ ከዚያ በኋላ በታይፕ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ተደርጐ ፣፣ የሚለው በቀጥታ አራቱ ምሥክሮች እየሰሙና እያዩ ሟች በራሣቸው አንደበት እየተናገሩ ቃል በቃል ያልተፃፈ መሆኑን ያሣያል። ኑዛዜው ደግሞ የተቀነባበረ የማርቀቅ ሥራ የሚያስፈልገው ሣይሆን የተናዛዡ የግል ተግባር ነው። ኑዛዜ በምክክርና በመወያየት የሚፈጸም አይደለም። ኑዛዜ ሌላ ሰው በድርሰት መልክ ጽፎ አቅርቦት ተናዛዡ በቃሉና በአፃፃፉ እስማማበታለሁ ብሎ የሚፈርመው ነገር አይደለም።

ሟች አደረጉ ተብሎ የቀረበው ኑዛዜ በመኪና የተፃፈ ነው። በመኪና የተፃፈው ረቂቁ በሌላ ጽሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ከተደረገ በኋላ ነው። በመኪና/በታይፕ / የተፃፈው ደግሞ ሌላ ቦታ ተወስዶ አራቱ ምስክሮች በሌሉበት ለመሆኑ መረዳት ይቻላል። ሕጉ ግን ተናዛዡ አራቱ ምሥክሮች በግንባር ባሉበት በቀጥታ በራሱ አንደበት እየተናገሩ ቃል በቃል ኑዛዜው ተጽፎ ወዲያውኑ ተነቦ ተናዛዡ ምሥክሮች ሣይነጣጠሉ እዚያው በዚያው መፈረም ያለባቸው መሆኑን ነው የሚያስገነዝበው። በዚህ ጉዳይ እንደሚታየው ደግሞ ሟች አድርገዋል ተብሎ የቀረበው ኑዛዜ ሕጉ በሚያዘው መንገድ የተፈጸመ አይደለም። ጽሁፉም ተናዛዡና አራቱ

ምሥክሮች በአንድነት በተገኙበት ተነቦላቸው ወዲያውኑ የፈረሙበት መሆኑን አይገልጽም፡፡ ኑዛዜ ተብሎ በቀረበው ጽሁፍ ላይ አንደኛ ምሥክር ተብለው የተፃፉት አቶ ሃብተስላሴ አብተው ወረዳው ፍ/ቤት ቀርበው ስለኑዛዜው አደራረግ ሲጠየቁ የፃፈውን አላውቅም ብለዋል፡፡ ኑዛዜው ስለመነበብ አለመነበቡም የማውቀው ነገር የለም ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ሁለተኛው የሟች ንሰሃ አባት ነኝ የሚሉት አባ ደስታ ካሣዬም ራሴ አንብቤ ፈረምኩ ከሚሉ በቀር ለሁሉም ምስክሮች ኑዛዜው መነበቡን አላስረዱም፡፡ 3ኛው ምሥክር ሟች በታይኘ አስመትተው አምጥተው ፈረምንበት አሉኝ በእርሱ ፊት ሟች እየተናዘዙ ኑዛዜው ስለማፃፉ አላስረዱም፡፡ ኑዛዜውን ሁሉም ምሥክሮች እና ተናዛዡ ባሉበት ተነቦልናል አላሉም፡፡ በአጠቃላይ ከምስክሮቹ አመሰካከር ለማረጋገጥ የተቻለው ሟች የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም አድርገዋል ተብሎ የቀረበው ኑዛዜ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 881 መሠረት ያልተፈፀመና በሕጉ ላይ የተገለፀውን ኑዛዜ መንፈስም ሆነ ይዘት የሌለው መሆኑን ነው፡፡

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 857/1/ ላይ እንደተደነገገው ኑዛዜ የሟቹ ጥብቅ የሆነ ራሱ የሚፈጽመው ሥራ ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛ፣ዜ ነው ተብሎ በቀረበው ጽሁፍ ላይ የሕግ አንቀጾች ተጠቅሶ መገኘቱና በምሥክሮች ፊት ሣይሆን ሌላ ቦታ በታይኘ ተጽፎ መቅረቡ ሲታይ ሕጉ በሚያዘው መሠረት የተፈፀመ ትክክለኛ ኑዛዜ ነው ብሎ ለመናገር አይችልም፡፡ በእነዚህ ምክኒያቶች ሟች አድርገዋል የተባለው በሕጉ ብቃት ያለው ኑዛዜ ነው የማይሰኝ ከመሆኑም ሌላ ሕጉ በሚያዘው መንገድ የተፈፀመ ባለመሆኑ በሕጉ ፈራሽ ከሚሆን በቀር የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት የለም፡፡ መልስ ሰጪም ሆነች ከእርሷ የተወለደው ክንፈሚካኤል የተባለው ልጅ በኑዛዜው በሕጉ አግባብ ባለመፈፀሙ ኑዛዜ የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ወራሾች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ የክልል 14 መስተዳደር ዞን ፍ/ቤት መልስ ሰጪ ከልጁ  የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት የኑዛዜ ወራሾች ይሆናሉ የሚለው የሰጠው ውሣኔም ሙሉ በሙሉ የተሳሳተ ስለሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽረን ወራሽ መሆን የሌለባቸው ሰዎች ናቸው ብለናል፡፡ ይግባኝ ባዩች የሟቹ ሕጋዊ ወራሾች መሆናቸው ስላላከራከረ ወረዳው ፍ/ቤት በወሰነው መሠረት የሟቹ የአቶ አየለ ታምራት ህገዊ ወራሾች መሆናቸውን እንዳለ በማረጋገጥ ወስነን መልሰናል፡፡ መልስ ሰጪ ከሟቹ ተወልዷል ስለምትለው ክንፈሚካኤል ስለተባለው ልጅ ወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ላይ ባመለከተው መንገድ ሟች ወላጅ አባቱ ስለመሆናቸው እንዲረጋገጥላት ሥልጣኑ ለሆነው ፍ/ቤት በማመልከት ከመጠየቅ የሚያግዳት ነገር አይኖርም፡፡ ሚስትነቷን በተመለከተም ወረዳው ፍ/ቤት ሣይቀበላት ቀርቷል፡፡ ለዞን ፍ/ቤት ባቀረበችው ይግባኝም ኑዛዜው መጽደቅ አለበት የሚል ክርክር አቀረበች እንጂ ሚስት ነኝ በሚለው ክርክር አልገፋችበትም፡፡ በዚህም መዝገብ ከሟቹ ጋር ባልና ሚስት ነኝ የሚል ክርክር አላነሣችም፡፡ በዚህ ላይ የቀረበችው ይግባኝ እስከሌለ ድረስ የሟች ሚስት ነበረች አልነበረችም የሚል ጭብጥ ይዞ መወሰን አያስፈልግም፡፡በመጨረሻም ስናጠቃልለው ከፍ ሲል በተጠቀሱት የሕግ ምክንያቶች ሟች አቶ አየለ ታምራት

የካቲት 15 ቀን 1980 ዓ.ም አድርገዋል የተባለው ኑዛዜ ውድቅ ሆኖ የክልል 14 መስተዳድር ዞን ፍ/ቤት ኑዛዜውን በሚመለከት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ በማለት ወሣኔ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ ውሣኔ የምንረዳው በሕግ ውጤት ያለው ኑዛዜ መኖሩን ለማስረዳት የኑዛዜው ሰነድ መቅረቡ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ነው፡፡

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የኑዛዜን ፎርም በተመለከተ በመዝገብ ቁጥሮች 25048፣ 16839፣11625፣10237ና 17429 ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ውሳኔዎቹ ተገቢ ነውን ይላሉን? ለምን?

# ምዕራፍ ስድስት

# ውርስን ማጣራት እና ውርስን ማስተዳደር

የዚህ ምእራፍ ዋና ዓላማ

- ውርስን ለማጣራት መከናወን ስላለባቸው ተግባራትና ስለ ውርስ አጣሪ አሿሿም ግንዛቤ ማስያዝ፣
- ከሟች የውርስ ንብረት መብት አለኝ የሚሉ ሰዎች ጥያቄ ስለሚወሰንበት ሁኔታ ማሣየት፣
- የሟች ወራሾች ውርሱን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል ስላላቸው ምርጫ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- ስለ ውርስ እዳ አከፋፈል እና ስለ ወራሽነት የምስክር ወረቀት አንዳንድ ነጥቦችን ማብራራት፣
- ስለ ውርስ መዘጋትና የውርስ መዘጋት ስለሚያስከትለው ውጤት ግንዛቤ፣

ማስጨበጥ ነው፡፡

## 6.1 ወራሽነትን ስለማጣራትና ስለ ውርስ አጣሪ

በምእራፍ ሁለት በግልጽ እንደተመለከተው ሟች በሞተበት ጊዜና ቦታ የሟች ውርስ እንደሚከፈት ገልፀናል፡፡ የሟች ውርስ ሟች በሞተበት ጊዜና ቦታ የሚከፈት ቢሆንም የሟች ውርስ እስከሚጣራ ድረስ የሟች ንብረት "አንድ የተለየ ንብረት፣፣ እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ይኸም ማለት የሟች ንብረት ከሌሎች ሰዎች ንብረት ወይም ከወራሾቹ ንብረት ጋር ሣይቀላቀል የባለቤትነት መብቱ ለወራሾች ሣይተላለፍ እንደ አንድ ልዩ ንብረት፣ Distinct estate፣ሆኖ መያዝ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 942 ይደነግጋል፡፡ ይኸም የሚሆነው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ የሟች ውርስ ሣይጣራ ንብረቱ ከሌሎች ሰዎች ንብረት ጋር ቢቀላቀል ውርሱን ለማስተዳደርም ሆነ ለማከፋፈል የሚያጋጥመው ችግር ከባድ በመሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ውርስን የማጣራቱ ሥራ በሟች የውርስ ስርዓት አፈጻጸም ውስጥ በቀላሉ የማይታይና እጅግ በጣም

አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ የውርስ ማጣራት ሥራ በሟች የውርስ ስርዓት ለማስፈፀም አስፈላጊ ተግባር ነው ካልን የውርስ ማጣራቱን ተግባር ሀላፊነት ወስዶ የሚያስፈጽም አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች መኖር አለባቸው፡፡ እነዚህ ውርሱን የማጣራት ተግባር የሚፈጽሙትን ሰዎች የውርስ አጣሪ በመባል ይታወቃሉ፡፡

6.1.1 <u>**ወራሽነትን ስለማጣራት**</u>

ውርስ ማጣራት ማለት፣

- የሟች ወራሾች እነማን እንደሆኑ አጣርቶ መወሰን፣
- የውርሱ ሀብት መጠን አይነትና ግምት እንደዚሁም የሚገኝበትን ቦታ አጣርቶ መወሰን፣
- ሌሎች ሰዎች ከሟች የተበደሩትን ገንዘብ መሰብሰብና በሟች ውርስ ላይ ሊከፍላቸው የሚገቡ አስገዳጅ የሆኑ እዳዎችን አጣርቶ መክፈል፣
- እንደዚሁም ሟች ልዩ የኑዛዜ ስጦታ ያደረጉላቸውን ሰዎች የተሰጣቸውን ልዩ የኑዛዜ ስጦታ መክፈል፣

ማለት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 944 ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ የውርስ ማጣራት ተግባራት በብቃት እስኪከናወኑ፣ የውርሱ ንብረት እንደ ናአንድ የተለየ ንብረትን እንደሚቆጠርና ከውርሱ ሀብት ላይ ገንዘብ ለመጠየቅ መብት ያላቸው ሰዎች ማለትም የሟች አበዳሪዎች እና የፍርድ ባለመብቶች ለገንዘባቸው ዋስትናና መያዥያ የሚሆናቸው ይኸው በመጣራት ላይ ያለው የውርሱ ንብረት ነው፡፡ ይኸም በመሆኑ ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ ከሟች ወራሾች ገንዘብ ጠያቂ የሆኑ ሰዎች በውርሱ ንብረት ላይ አንዳችም የይገባኛል ጥያቄ ማቅረብ እንደማይችሉና ምንም አይነት መብት እንደሌላቸው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943/1/ እና 943/3/ ድንጋጌዎች ያመለክታሉ፡፡

እነዚህ ድንጋጌዎች የራሣቸው ጠቀሜታና ግብ አላቸው፡፡ ምክንያቱም የሟች ውርስ በሚጣራበት ጊዜ የሟች ወራሾች አበዳሪዎችና ገንዘብ ጠያቂዎች የውርሱን ንብረት በመያዥያነት እንዳይዙ የሚያደርገው የሟች ወራሾች ከውርሱ ንብረት ድርሻ ሊያገኙ የሚችሉት ከሟች እዳ የተረፈ ንብረት ሲኖር ብቻ በመሆኑ ነው፡፡
ሀኑ የሟች ወራሾች አበዳሪዎች ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ በውርሱ ንብረት ላይ የይገባኛል ጥያቄ እንዳያቀርቡ በሟች ወራሾች እዳ ምክንያት የውርሱ ንብረት በመያዣነት እንዳይያዝ የሚከለክል ነው፡፡

እንደዚሁም ውርሱ በመጣራት ላይ እያለ ከሟች ውርስ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከሟች ወራሾች የግል ሀብት ላይ አንዳችም መብት እንደሌላቸው እና የሟችን የውርስ ንብረት ብቻ መከታተል እንዳለባቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 943 ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡
እዚህ ላይ ውርስን ማጣራት አስፈላጊነት በመጀመሪያ ከሟች ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ውርሱ ከመከፋፈሉ በፊት ገንዘባቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ፣ በማስከተልም ከውርሱ በእዳነት የሚጠየቁ ለምሣሌ ለሟች የቀብር ስነ ስርዓት የወጣው ወጭ፣ ከውርሱ መከፈል ያለበት የቀለብ እዳ እና ሟች በልዩ ኑዛዜ የሰጣቸው ስጦታዎች በቅደም ተከተል ተከፍለው ሲያበቁ ነውና ከዚህ የተረፈ ንብረት ካለ ነው የሟች የሕግ ወራሾችና ጠቅላላ የኑዛዜ ተጠቃሚዎች ከሟች ውርስ ንብረት ድርሻቸውን ያገኛሉ፡፡

በመጨረሻም የውርስ ሕጋችን ወራሾችና የኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸው ሰወች ውርሱን ስለማጣራት ወይም ስለመካፈል በመካከላቸው በሚደረገው ክርክር ሁሉ አንድ ወይም ብዙ የዘመድ አስታራቂ ዳኞች እንዳያዩት ለመስማማት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 945 ይደነግጋል፡፡

### 6.1.2 <u>የውርስ አጣሪ</u>

ከላይ እንደተገለፀው ውርስን ማጣራት በሟች የውርስ ስርዓት አፈጻጸም ወቅት እጅግ በጣም አስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ ይህንን ውርሱን የሚያጣራው ሰው ወይም ሰዎች የውርስ አጣሪ ተብለው ይጠራሉ፡፡ የውርስ አጣሪ ከሶስቱ በአንደኛው መንገድ ሊሾም እንደሚችል የውርስ ሕጋችን ይደነግጋል፡፡ የውርስ አጣሪ፣

- በሟች ኑዛዜ መሠረት፣
- በሕግ ሊመረጥ ወይም ሥልጣኑን ከሕግ ሊያገኝ፣
- በዳኞች ሊሾም ይችላል፡፡

የመጀመሪያውን በተመለከተ ሟች አንድ ኑዛዜ የተወ እንደሆነና ሟቹ በዚሁ ኑዛዜ ውስጥ የኑዛዜው አስፈጻሚ የሾመ እንደሆነ ሟች የመረጠው ሰው የውርሱ አጣሪ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ የሾመ እንደሆነ ሟች በግልጽ በኑዛዜው ካላመለከተ በስተቀር በሟች ኑዛዜ ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውርሱን የማጣራት መብት ይኖረዋል፡፡ ሟች የውርስ አጣሪውን በኑዛዜ የሾመ እንደሆነ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ አድርጐ እንደሆነ ጠቅላላ ኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ውርሱን የማጣራት መብት በቅደም ተከተል ይኖራቸዋል፡፡ ሟች የውርስ አጣሪውን በኑዛዜ የሾመ እንደሆነ ወይም ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገለት ሰው የተገኘ እንደሆነ የሟችን

ያሉ ኑዛዜ ወራሾች የውርስ አጣሪነት ስልጣን የሚያስቀረው እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 948 ተደንግጓል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ ያልሾሙ እንደሆነ ወይም ሟች ጠቅላላ የኑዛዜ ስጦታ ያደረገለት ሰው የሌለ እንደሆነ የሟች ያለ ኑዛዜ ወራሽ የሆኑ ሰዎች ሰውየው ከሞተበት ቀን አንስቶ ያለ አንዳች ፎርማሊቲ የውርስ አጣሪነት መብት እንደሚኖራቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 947 የሚደነግግ ሲሆን ብዙ ሰዎች የውርስ አጣሪ በሆኑ ጊዜ የአጣሪነቱን ተግባር በመተባበር መስራት እንዳለባቸው ወይም አንዱን በመወከል ለማሠራት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 958 ይደነግጋል፡፡

ሶስተኛው የውርስ አጣሪ የሚሰየምበት ስርዓት በፍርድ ቤት ውሣኔ የውርሱ አጣሪ የሚሰይምበት ሁኔታ ነው፡፡ የውርስ አጣሪ በፍርድ ቤት የሚሰየመው፣

- የሟች ወራሾች የማይታወቁ እንደሆነ፣
- ያለ ኑዛዜ ወራሾች ውርሱን ለማጣራት የማይፈቅዱ መሆናቸውን ገልፀው ያሣወቁ እንደሆነ፣
- ሟች የኑዛዜም ሆነ ያለ ኑዛዜ ወራሽ ያልተወና የሟችን ሀብት መንግስት የሚወርሰው በሆነ ጊዜ፣

የአስተዳደር ሕጐችን ወይም ደንቦችን መሠረት በማድረግ ዳኞች የውርሱን አጣሪ እንደሚሰይሙ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 949 ድንጋጌዎች ያስረዳሉ፡፡

እንደዚሁም ዳኞች በሟች ኑዛዜ፣ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተሰየመውን የውርስ አጣሪ በሌላ የውርስ አጣሪ የመተካት ስልጣን እንዳላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 951 ይደነግጋል፡፡ የውርስ አጣሪን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 949 መሠረት መሰየምንና በሕግ ወይም በሟች ኑዛዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ራሱ የሰየመውን የውርስ አጣሪ መተካት /replacement / እና substitution/ ሁለት የተለያዩ ጽንሰ ሀሣቦች ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ በሕግ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤቱ የተሰየመን አንድ የውርስ አጣሪ ስልጣንና ሀላፊነት በማንሣት ሌላሐሌሎችሐ የውርስ አጣሪ የሚሰይመው፣

- ውርስ አጣሪው የተሾመበት ኑዛዜ ዋጋ ያለው ኑዛዜ መሆኑ አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ ወይም፣
- በሌላ ምክንያት ውርስ አጣሪውን በመለየት ላይ የሚያጠራጥር ነገር ሲኖር ወይም፣
- ብዙ ውርስ አጣሪዎች ለምሣሌ ስልጣናቸው 947 የሚመነጭ ብዙ ያለ ኑዛዜ ወራሾች ኖረው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 958 በሚደነገገው መሠረት ውርሱን በመተባበር በመግባባት ለማስተዳደርና ለማጣራት ያልተስማሙ እንደሆነ ወይም፣
- ከወራሾቹ መካከል አንዱ አካለ መጠን የላደረሰ ልጅ ወይም የተከለከለ ሰው ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ለምሣሌ በአገር ባለመኖሩ፣ እብደቱ በግልጽ ያልታወቀ ሰው በመሆኑና በሌሎች ምክንያቶች ጥቅሙን ለማስከበር የማይችል በሆነ ጊዜ ወይም፣

- የውርሱ አስተዳዳር ወይም የማጣራቱ ስራ ልዩ ችግር ያስነሣና ልዩ ሙያ ያላቸውን ሰወች ወይም ሌላ ችግሩን ለመቅረፍ የሚችል የውርስ አጣሪ መሰየም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወይም፣
- በሕግ ሟች ኑዛዜ ወይም በዳኞች የተሰየመው አጣሪ ቸልተኛና ትጉህ ያልሆነ እንደሆነ ወይም የማጭበርበር ባህሪ የሚታይበትና ሀቀኝነት የጉደለው የሆነ እንደሆነ ወይም አጣሪው የማጣራት ስራውን በሚገባ ለመፈፀም ችሎታ የሌለው መሆኑ የታወቀ እንደሆነ፣

ዳኞች ከማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ከሚል ባለጉዳይ ጥያቄ አቅራቢነት በሕግ፣ በኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሣኔ ተሰይሞ የነበረውን የውርስ አጣሪ በመሻር በአካባቢው ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠውን ሰው ወይም ማናቸውንም ለስራው ብቁ ነው ብለው የሚመርጡትን ሌላ ሰው በውርስ አጣሪነት ለመሰየምና ለመተካት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 951 ተመልክቶ እናገኘዋለን።

በውርስ ህጋችን በግልጽ እንደተመለከተው በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተመረጠ ወይም የተተካ የውርስ አጣሪ የሚከተሉት ግዴታዎችና ሀላፊነቶች ይኖሩበታል።

- ሟች በህይወት ዘመኑ ያደረገው ኑዛዜ ካለ ኑዛዜውን መፈለግና የሟችን የኑዛዜ ወይም ያለኑዛዜ ወራሾች እነማን እንደሆኑ ማረጋገጥ፣
- የውርስ ንብረት ከብልሽትና ከብክነት ለመታደግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ በመውሰድና ሌሎችንም አስፈላጊ ተግባራት በመፈጸም የውርሱን ሀብት ማስተዳደር፣
- በግልጽ የታወቁ፣ ክርክርን የማያስነሱ መከፈል ያለባቸውን የውርስ እዳዎች በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 1014 በተቀመጠው ቅደም ተከተል መሰረት መክፈል፣
- ሟቹ በልዩ ኑዛዜ ያደረጋቸውን ስጦታዎች መክፈልና የሟችን የኑዛዜ ቃል ለመፈጸምና ውጤት ለመስጠት ማንኛውንም አስፈላጊ ጥንቃቄ ማድረግ፣
- ጥያቄው ያገባኛል በሚል ማናቸውም ባለጉዳይ ሲቀርብና ዳኞችን የሚያሳምን ሆኖ ሲገኝ ስለስራው መልካም አፈጻጸም አንድ ዋስ ወይም ሌላ የመልካም ስራ አፈጻጸም ማረጋገጫ ሊሆን የሚችል መያዣ ማቅረብ፣
- ስራውን ለመተው ሲፈልግ አዲስ አጣሪ እስከሚሰየምና ተተክቶ ስራውን እስከሚጀምር ድረስ የአጣሪነት ስራውን የማከናወን፣
- ሟች በአደረገው ኑዛዜ ስለአጣሪነቱ የስልጣን ወሰንና ስለስራው አፈጻጸም የሰጠውን መመሪያና ትእዛዝ ተከትሎ የመስራትና ዳኞችም ስለስልጣኑ ወሰንና ስለስራው አፈጻጸም የሚሰጡትን ትእዛዞች በማክበር የአጣሪነት ስራውን ማከናወን፣
- ውርሱን አጣርቶ ከጨረሰ በኂላ ለወራሾቹ ስለማጣራቱ የስራ ክንውን ሪፖርት ማቅረብ፣

- ውርስ አጣሪው ማናቸውንም የህጉን ድንጋጌዎች በሟች ኑዛዜ የተሰጡትን መመሪያዎች ወይም በዳኞች የተሰጡትን ትእዛዞች በሚቃረን በጥፋቱ ወይም በቸልተኝነቱ መንገድ ለሚያደርጋቸው ጉዳዮችና በዚያ መሰረት ለሚደርስ ጉዳት በሀላፊነት የመጠየቅ ግዴታ እንዳለበት፣

ከፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 952፣ 954-957 እንደዚሁም የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 960 እና 961 በማየት መረዳት ይቻላል።

በሌላ በኩል ህጉ በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በውርስ አጣሪነት ለሚሰየሙ ሰዎች ያስቀመጠላቸው መብት አለ። ከመብቶቹ መካከል እጅግ በጣም አስፈላጊው የውርስ አጣሪነት ስራ ማንም ሰው በፈቃዱ ብቻ ሊያከናውነው የሚገባና ማንም ሰው ያለፈቃዱ የአጣሪነት ስራዎችን ለመቀበል የማይገደድ መሆኑ ነው። አንድን ተግባር አንድ ሰው ተገድዶ እንዲያከናውን ማድረግ የተከለከለና መሰረታዊ የሆነውን የሰው ልጅ ነጻነት መብት የሚነካ በመሆኑ የውርስ አጣሪነትን ተግባር አንድ ሰው ሳይፈልግ እንዲቀበልና እንዲሰራ ማድረግ እንደማይቻል የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 953 በግልጽ ይደነግጋል። ሁለተኛው መብቱ ደግሞ ውርስ አጣሪው ስራውን እፍጻሜ ለማድረስ ወይም ለተወሰነ ጊዜ ለመስራት በግልጽ ግዴታ የገባ ካልሆነ በቀር በማናቸውም ጊዜ ስራውን መተው የሚችል መሆኑ ነው። እዚህ ላይ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ‹በግልጽ ግዴታ የገባ ካልሆነ በቀር› የሚለው ሀረግ ነው። በዝምታ በህግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በዳኞች የውርስ አጣሪ ሆኖ እንዲሰራ መመረጡን ተቀብሎ ስራ መጀመሩ ብቻውን የማጣራት ስራውን በማናቸውም ጊዜ የመተው መብቱን አያስቀርበትም። ስራውን የመተው መብቱ ቀሪ የሚሆነው በግልጽ እራሱን ግዴታ ያስገባ እንደሆነ ብቻ ነው።

ሌላው እዚህ ላይ መታየት ያለበት ውርስ አጣሪው ይህንን የማጣራቱን ስራ የመተው መብቱን እንደፈለገው ሊጠቀምበት አይችልም። የሟች ውርስ ንብረት የግድ መጠበቅና በጥንቃቄ መያዝ ስለሚገባው ሌላ ተተኪ አጣሪ እስኪመረጥና ስራውን እስኪረከብ ድረስ ስራውን እየሰራ መቆየት ያለበት መሆኑ የፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 954 ድንጋጌዎችን በማየት ለመረዳት ይቻላል።

በሶስተኛ ደረጃ ለውርስ አጣሪ የተቀመጠለት መብት አጣሪው ውርሱን ለማጣራት ለሰራው ስራ የአገልግሎት ዋጋ የማግኘት መብት ያለው መሆኑ ነው። የውርሱ አጣሪ የአገልግሎት ክፍያውን የሚያገኘው ሟች በኑዛዜው ውስጥ በሰጠው መመሪያ ወይም ወራሾቹ በሚያደርጉት ስምምነት ወይም ዳኞች በሚሰጡት ውሳኔ መሰረት ሊሆን እንደሚችል የፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 959 ይደነግጋል። በመሆኑም አጣሪው ውርሱን በማጣራት ለሰራው ስራና ግልጋሎት ከውርሱ ንብረት ላይ ከላይ ባስቀመጥናቸው ሁኔታዎች ሲወሰንለት የአገልግሎት ዋጋ የማግኘት መብት እንዳለው መታወቅ ይኖርበታል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የውርስ ህግ መሰረት ‹ውርሱን ስለማጣራት› የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ምንነትና ይዘት እንደዚሁም ጠቀሜታ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የመጀመሪያው በምእራፍ ሁለትም ለመጠቆም እንደተሞከረው ‹የሟች ውርስ መከፈት› እና ‹የሟችን ውርስ ማጣራት› የሚሉት ጽንሰሀሳቦች እጅግ በጣም የተለያዩ ናቸው፡፡ የሟች ውርስ መከፈት የምንለው ሟች ህይወቱ ካለፈበት ቅጽበት ጀምሮ ምንም አይነት የሲቪል መብት ግዴታ ሊኖረው ስለማይችል ህጉ የሟች ህይወት ካለፈችበት ሰኮንድ ጀምሮ የሟች መብትና ግዴታ ለሟች ወራሾች ለማስተላለፍ የሚያደርጋቸውን ጥንቃቄ የሚመለከት ነው፡፡

የሟች ውርስ የሚከፈተውም ሟች መኖሪያ ስፍራና ሟች በሞተበት ጊዜ እንደሆነ በፍትሀ ብሄር ህግ ቁጥር 826 ተመልክቷል፡፡ የሟችን ውርስ ማጣራት የምንለው ደግሞ የሟችን ያለኑዛዜና በኑዛዜ ወራሾች የሚለዩበት፣ የሟች እዳ የሚከፈልበት፣ የሟች አበዳሪዎች እና ተበዳሪዎች የሚለዩበት፣ ንብረቱ በሟች ወራሾች እስኪተላለፍና ውርሱ እስከሚዘጋበት ቀን ድረስ የንብረት ማስተዳደር ስራዎች የሚከናወንበት ውስብስብ ተግባር ነው፡፡

አሁን በስራ ላይ ያለው የውርስ ህግ አጣሪ ስለሚሆኑ ሰዎች ሲደነግግ ቀዳሚውና የመጀመሪያው የውርስ አጣሪ የሚሆነው ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ አድርጎ የሾመው ሰው እንደሆነ ከገለጸ በኋላ ሟች በኑዛዜ የውርስ አጣሪ አድርጎ የሾመው ሰው ከሌለና በኑዛዜው የውርስ አጣሪ እንደሚሆንና ጠቅላላ ኑዛዜ የተደረገለት ሰው መገኘት የሟችን ያለኑዛዜ ወራሾች የአጣሪነት ስራ እንደሚያስቀረው በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 948 ንኡስ ቁጥር 2 እና 3 የሚደነግግ ሲሆን የሟች ውርስ መዘጋት ማለት ደግሞ የሟችን ንብረት ለወራሾች በአግባቡ የማከፋፈል ስራን አይጨምርም፡፡

የውርስ አጣሪው ሀላፊነት ከላይ ያነሳናቸውን ተግባር በመፈጸምና የሟችን ወራሾችና የሟች ከእዳ ተከፍሎ የሚቀረውን ንብረት በማጣራት፣ ዝርዝርና የመጨረሻ ሪፖርት ለወራሾቹ ማቅረብ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ በኋላ የውርሱን ንብረት ማስተዳደርም ሆነ የሟችን ንብረት መከፋፈል የወራሾች መብትና ሀላፊነት እንጂ የውርሱ አጣሪ አይደለም፡፡

በመሆኑም ውርስ አጣሪ በዋነኛነት ሊፈጽማቸው የሚችላቸው ተግባራት፣

- ከሟች ውርስ መብት አለን የሚሉትን ሰዎች ሁኔታ መወሰን፣
- የሟችን የውርስ ንብረት ማስተዳደር፣
- የሟችን የውርስ እዳ መክፈል፣

ናቸው፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች

የሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 32095፣ 25869፣23329፣28764 የሰጣቸውን ውሳኔዎች በመተንተን አብራሩ። ውሳኔዎቹ ትክልል ናቸው ብለው ያምናሉን?

# ምእራፍ ሰባት

# ስለውርስ የተደነገጉ የይርጋ ጊዜ ገደቦች

የዚህ ምእራፍ ዋና አላማ

- በውርስ ይርጋ ላይ በአተረጓገም ረገድ ያሉ ችግሮችን ማሳየት
- የተሻለ ትርጉም ተግባራዊ ማድረግ

## መግቢያ

በማናቸውም ጉዳይ አንድ ሰው በሕግ ከውል ወይም በፍርድ ቤት ውሣኔ መብት ያገኘ እንደሆነ፣ መብቱን የሚጠይቅበትና በሥራ ላይ የሚያውልበት የተወሰነ የጊዜ ገደብ ይሰጠዋል። ባለመብቱ በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ መብቱን ለመጠየቅ ተገቢውን ትጋት ማድረግና፣ የመብት ጥያቄውን ማቅረብ ያለበት ሲሆን፣ መብቱን በሕጉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልተጠቀመ ግን፣ ክርክሩ በይርጋ የጊዜ ገደብ የተገደበ መሆኑን በመገለፅ ሌላኛው ተከራካሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በማንሣት ክርክሩ እንዳይታይ ለማድግ እንደሚችል በፍተሐብሔር ሕጉ፣ በንግድ ሕጉና በሌሎች አዋጆችና ደንቦች እንደዚሁም ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጐች ለመረዳት ይቻላል።በፍትሐብሔር ጉዳይ ተከራክረው በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካላነሣው በቀር ዳኞች በራሣቸው አነሳሽነት አንድን ክርክር የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል ብለው ለመዝጋት እንደማይችሉ በመሠረታዊ መርህነት የተቀመጠ ሲሆን፣ በወንጀል ጉዳይ ግን ዐቃቤያነ ሕግም ሆኑ ዳኞች ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ፣ የወንጀል ክስ ማቅረቢያው የይርጋ ጊዜ ያለፈ መሆኑን በመጥቀስ ክሱን መዝጋት እንደሚችሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ተቀምጧል።

በአጠቃላይ የይርጋ ጊዜ ገደብ ማስቀመጥ ያስፈለገበት ምክንያት እና ስለ ይርጋ ጊዜ ገደብ በክርክር ወቅት እንዴት ማንሣት እንደሚቻልና ማን ሊያነሳው እንደሚችል በሕጉ ከተቀመጡት መሠታዊ መርሆች በመነሳት ለመግቢያ ያህል ይህንን ካልን፣ በውርስ ሕጋችን  ውስጥ የተቀመጡ የይርጋ የጊዜ ገደቦች ምንድን ናቸው? የይርጋ የጊዜ ገደቦች ማን ሊጠቀምባቸው ይችላል?  ይዘታቸው እና አተረጓጐማቸው ምን መምሰል አለበት? የሚሉትን ነጥቦች መዳሰሱ አስፈላጊ ነው። ከዚህ ምዕራፍ ውስጥ፣ ትኩረት የሚሰጠው በተለይ የሟች ውርስ

ከተከፈተ በኋላ፣ ሊቀርቡ የሚችሉ ክርክሮችን አስመልክቶ በሕጉ የተቀመጡ የይርጋ ጊዜዎች፣ እና በአፈጻጸምና በአተረጓጎም ላይ ያለው ችግር ላይ ነው፡፡

## 7.1 ኑዛዜን ስለመቃወም የተቀመጠ የጊዜ ገደብ፣

በመጀመሪያ የውርሱ አጣሪ፣ የሟችን ኑዛዜ የማፈላለግ ግዴታ እንዳለበት እና የሟችን ኑዛዜ ባገኘ ጊዜ፣ ሟች በሞተ በአርባ ቀን ውስጥ የሟች ያለኑዛዜ ወራሾች አንደሚናገርና ኑዛዜው የሟች ያለኑዛዘ ወራሾች ባሉበት እንደሚነበብ፣ እንደዚሁም የኑዛዜው ፎርምና ኑዛዜው ዋጋ ያለው መሆኑ እንደሚመረመር በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 964፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 968 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 969 ይደነግጋሉ፡፡ እንደዚሁም ሟች ኑዛዜ ያልተወ እንደሆነ የውርሱን አደራረግ እና የአከፋፈል ዓይነት እንዴት ሊፈፅም እንዳቀደ ውርስ አጣሪ ለሟች ያለ ኑዛዜ ወራሾች ሟች ከሞተ ከአርባ ቀን በኋላ ማሳወቅ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 972 ይደነግጋል፡፡ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም በአግባቡ የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው በጠቅላላ አይፀናም ወይም በኑዛዜው ከተነገረው ቃል ውስጥ አንዱ አይፀናም በማለት ክስ ለማቅረብ ያላቸውን የኃሣብ መግለጫ ወይም ስለክፍያው በሒሣብ አጣሪው ያቀረበውን ድልድል አመዳደብ ኃሣብ ለመቃወም ኑዛዜው ከተነበበለት ቀን አንስቶ የአሥራ አምሥት ቀን ጊዜ እንዳላቸው ይህ መግለጫ በፅሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ካልደረሰ በርቀት እንደማይፀና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 973/1/ እና 973/2/ ይደነግጋሉ፡፡በእነዚህ የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ኑዛዜው ሲፈስ/ ሲነበብ/ ወራሹ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ የነበረ ሰው የሟች ኑዛዜ ነው ብሎ ውርስ አጣሪው በያዘው ኑዛዜ ላይ መቃወሚያና ክርክር ማቅረብ ከፈለገ፣ ይህንኑ ኃሣቡን በፅሑፍ ለውርስ አጣሪው፣ ለዳኞች ወይም የወራሹን ጉዳይ ለማየት የተሰየሙ የሽማግሌ ዳኞች ካሉ፣ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ የጽሑፍ መግለጫ መስጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ሕጉ የሚለው መቃወሚያውን ኃሣብ ያለው መሆኑን ማሳወቅ አለበት፡፡ ወራሹ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ፣ የፅሑፍ መግለጫውን ባያቀርብ ምን ይሆናል የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ለመቃወም ያለውን የኃሣብ መግለጫ ካላቀረበ፣ በኑዛዜው ወይም የውርሱ አጣሪ ያቀረበውን የድልድል ኃሣብ እንደተቀበለ እንደሚቆጠር ከሕጉ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ ስለክፍያው በሒሣብ አጣሪው " የቀረበውን ድልድልን አመዳደብ ኃሳብ በመቃወም " የሚለው ሐረግ፣ የውርሱ ኃብት በወራሾች መካከል የሚደረገውን አከፋፈል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ይገባል፡፡ ውርስ አጣሪው ውርሱ ከመዘጋቱ በፊት የሟች የመክፈያ ጊዜ የደረሰ ዕዳ እና የመክፈያ ጊዜ ያልደረሰ ዕዳ፣ የሟችን ልዩ የኑዛዜ ስጦታ እና የውርሱን ዕዳ እንዴት ሊከፍል እንዳለበት የሚያቀርበውን የክፍያና የድልድል ኃሣብ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ መግለጫቸውን ማቅረብ አለባቸው በማለት ታስቦ የተደነገገ ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ውርሱ ከተዘጋ በኋላ ወራሾች ውርሱን የሚከፋፈሉት በመካከላቸው የሚያደርጉት ሥምምነት በሟች ኑዛዜ ውስጥ በተቀመጠ የክፍያ ደንብ ወይም ዳኞች

በሚሰጡት ትዕዛዝ መሠረት መሆኑን በምዕራፍ ስድስት በሰፊው ያየነው በመሆኑ ነው፡፡ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም በሕጋዊ ወኪላቸው የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በውርስ አጣሪው የቀረበው የክፍያና የድልድል ኃሣብ ተገቢ ዓይደለም የሚለውን መቃዎሚያ በፅሑፍ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ካሣወቁ በኋላ፣ መግለጫውን ካቀረቡበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ወር ድረስ ክሱን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት፣ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 945 መሠረት ለተሰየመው የሽምግልና ዳኞች ክስ ካላቀረበ በስተቀር፣ በሌላ ጊዜ መቃወሚያውን ማቅረብ እንደማይችል እና ጥያቄው በይርጋ እንደሚታገድ የፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 973/3/ ይደነግጋል፡፡ኑዛዜው ሲነበብና ሲፈፀም ያልነበሩ ወይም ሕጋዊ ወኪል ያልነበራቸው ሰዎች የውርሱ አጣሪ፣ ስለኑዛዜው እና ክፍያና ድልድል አመዳደብ ኑዛዜው ሲነበብ ላልነበረው ሰው ከነገረው በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ፣ የመቃወሚያውን የፅሑፍ መግለጫ ማቅረብ ያለበት መሆኑንና መግለጫ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ እስከ ሶስት ወር ድረስ ክሱን ለዳኞች ማቅረብ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974/1/ ይደነግጋል፡፡ኑዛዜው ሲነብና ሲፈርስ ራሣቸው ወይም ወኪላቸው ያልነበሩ ሰዎችና ከዚያም በኋላ ውርስ አጣሪው አግኝቶ ስለኑዛዜው ያልነገራቸው ሰዎች ኑዛዜው ከፈሰሰበት ጊዜ ከአምሥት ዓመት በኋላ ወይም ኑዛዜ የሌለ ከሆነ ሟች ከሞተ ከአምሥት ዓመት በኋላ በኑዛዜው መፅናት፣ ስለክፍያው አመዳደብ አጣሪው ያቀረበውን ኃሣብ በማናቸውም አስተያዬት ቢሆን መቃወሚያ ሊያቀርብበት እንደማይችል እና ጥያቄው በይርጋ እንደሚታገድ፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974/2/ ይደነግጋል፡፡

ከላይ ያነሳናቸው የሕግ ድንጋጌዎች በውርስ አጣሪው አፈላልጐ ባቀረበው ኑዛዜና ባቀረበው የክፍያና የድልድል ኃሣብ ላይ ያለ ኑዛዜ ወራሾች በስንት ጊዜ ውስጥና እንዴት መቃወሚያቸውን ማቅረብ እንደሚችሉ የሚደነግጉ ናቸው፡፡ እነዚህን የሕግ ድንጋጌዎች በሌላ ክፍል ስለ ውርስ ይርጋ ከተደነገጉት ጋር በማገናዘብ ማየት ይገባል፡፡

## 7.2. <u>የወራሽነት ጥያቄ ለማቅረብ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ፣</u>

ወራሽ የሆነ ሰው ለሟቹ ወራሽ መሆኑና ከውርሱ ላይ ያገኘውን ድርሻ የሚያመለክት የወራሽነት የምሥክር ወረቀት እንዳጡት ዳኞችን ለመጠየቅ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 996/1/ ይደነግጋል፡፡ ይኸ ድንጋጌ፣ ከፍርድ ቤት የወራሽነት የምሥክርነት ወረቀት መያዝ፣ በወራሹ ሲፈልግ የሚጠይቀው እንጅ ሕጉ ሟችን ለመውረስ የግድ ከፍርድ ቤት የወራሽነት ማስረጃ ማውጣት እንዳለበት እንደሚያስገድደው ውርሱን አስመልክቶ ለመወሰን ከተሰየሙ የሽምግልና ዳኞች በውርሱ አጣሪ እና ወራሾች በመካከላቸው በሚያደርጉት ሥምምነት ወራሽነቱ እና ከውርሱ ስለደረሰው ድርሻ ማስረጃ ሊሰጠው እንደሚችል ይታያል፡፡ ያም ሆነ ስመንብረት ለማዛወር እና ከሌሎች የሟች መብቶች ለመጠቀምና ለመሥራት የፍርድ ቤት የወራሽነት የምሥክር ወረቀት መጠየቁ የተለመደ ስለሆነ የወራሽነት የምሥክር ወረቀት መጠየቅ ይችላል፡፡እንደዚሁም ወራሽ አለመሆኑን በግልፅ የሚያሣይ ማስረጃና መቃወሚያ በቀረበ ጊዜ የተሰጠው የወራሽነት ማስረጃ

እንደሚሰረዝና ዳኞች የወራሽነት ማስረጃ በሚሰጡበት ጊዜ አስፈላጊ መስሎ ከታያቸው ማናቸውንም የማረጋገጫ ዋስትና እንዲሰጥ ሊያስገድዱት እንደሚችሉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 998 እና 996/2/ ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በመነሳት አንድ ሰው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው ውርሱን ወይም ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ አንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ እንዲታወቅለትና የተወሰደው የውርስ ንብረቶች እንዲመለስለት መጠየቅ እንደሚችል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 የሚደነግግ ሲሆን፣ ጥያቄውን ማቅረብ ያለበትን ጊዜ አስመልክቶ ከሟሽ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሣሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦሥት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለወራሽነት ጥያቄ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት ማግኘት እንደማይችል የፍትሐብሔር ሕጋችን 1001/1/ ይደነግጋል፡፡እዚህ ላይ መታየት ያለበት አንድ ሰው የሟች ኑዛዜ ተጠቃሚ መሆን የሚችል ኑዛዜ በእጁ እንደሚገኝ ለውርስ አጣሪው አቅርቦ ውርስ አጣሪወ ኑዛዘውን በሚያነብበት ሰዓት ራሱ ወይም ወኪሉ ካንልነበረ ወራሽ ኑዛዜው ከፈሰሰበት ቀን አንስቶ በአምሥት ዓመት ውስጥ መቃወሚያ ካልቀረበ ከዚያ በኋላ ሊቀርብ እንደማይችል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974/2/ የተደነገገው ድንጋጌ ከፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ ድንጋጌ ጋር እንዴት ነው ተጣጥመው ተግባራዊ የሚሆኑት የሚለው ሲሆን፣ በሌላ በኩል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ አተረጓጐምና አፈጻጸም እንዴት መሆን አለበት የሚለው ጥያቄም መነሳት ያለበት ነው፡፡

ምክንያቱም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ሟች ከሞተበት ወይም ከሣሹ በመብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አሥራ አምሥት ዓመት ካለፈ በኋላ በዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በስተቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አይኖረውም በማለት የሚደነግግ በመሆኑ ነው፡፡ይህንን አስመልክቶ፣ በውርስ ሕግ ዙሪያ የተደነገጉ የይርጋ ጊዜ ገደቦች አተረጓጐምና አፈጻጸም በፍርድ ቤቶች የተለያዩ ትርጉሞችና ውሣኔዎች መስጠት ምክንያት እንዲሆኑና እስካሁን ድረስ ችግሩ እንዳልተቃለለ፣ አሁንም ይኸ ነው ትክክለኛው አተረጓጐም እና አፈጻጸም ብሎ ለመናገርም ሆነ ለመጻፍ አስቸጋሪ መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ ሆኖም እስካሁን የሰጡ አንድ አንድ አተረጓጐሞችን በማሳየት ተማሪዎች የበለጠ እንዲከራከሩና እንዲወያዩ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ አንድ አንድ ነጥቦችን ለማንሣት እሞክራለሁ፡፡

የመጀመሪያው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 974/2/ ተፈጻሚ የሚሆነው የሟችን ውርስ የሚያጣራ፣ በሕግ፣ በሟች ኑዛዜ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ የውርስ አጣሪ፣ ሟች አድርጐታል የተባለው ኑዛዜ አግኝቶ የኑዛዜውን ፎርምና የኑዛዘውን ዋጋ መኖር፣ የሟች ያለኑዛዜ ወራሾች ወይም አራት አካለመጠን ያደረሱ ሰዎች ባሉበት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 968 በተመረመረበት ሁኔታ ነው፡፡ ሆኖም ኑዛዜ ያለ መሆኑን

ለውርስ አጣሪው ሣያሳውቅ ቀጥታ የኑዛዜ ወራሽ መሆኑ እንዲታወቅለት ለፍርድ ቤት አመልክቶ የወራሽነት የምሥክርነት ወረቀት በመውሰድ የሟችን ንብረት በእጁ ካስገባ ሰው ወይም በሐሰት የሟች ያለኑዛዜ ወራሽ ነኝ ብሎ የሟችን ንብረት ከወሰደ ሰው፣ ለማስመለስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 968 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ሣይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ የተመለከተው ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ እና 1000/2/ አስመልክቶ የሚታየው አተረጓጐም ልዩነት ሲሆን በአንድ በኩል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ የማይነቀሣቀስ የሟችን ንብረት፣ ለማስመለስ ሊቀርብ የሚችለው ክስ በምን ያህል ጊዜ መቅረብ እንደሚገባው የሚወሰን ሲሆን፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ግን የማይንቀሣቀስ ንብረትን ለማስመለስ የሚቀርብን ክስ የይርጋ ጊዜ የሚመለከት ነው በማለት በመተርጐም ፍርድ የሰጡ ዳኞች ያሉ ሲሆን፣በሌላ በኩል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ከዘር የወረደ ርስት ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት በማስመለስ ከአሥራ አምሥት ዓመት በኂላም ክስ ለማቅረብ እንደሚፈቀድ፣ "ሟች ከሞተበት ወይም ከሣሹ በመብቱ ሊሰራበት ከቻለበት ቀን አንስቶ አሥራ አምሥት ዓመት ካለፈ በኂላ ከዘር የወረደ እርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸወም አስተያዬት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም " የሚለው ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ ንብረቱ የሚንቀሣቀስ እና የማይንቀሣቀስ ሲሆን በማለት ለመለየት መሞከሩ የሕጉን ይዘት መንፈስና መልዕክት የሚያንፀባርቅ አይደለም የሚል ትችት ሲሰጡ ይስተዋላሉ፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ ምን ጊዜም ተፈጻሚነቱ የሚንቀሣቀሱ ንብረቶችን ለማስመለስ ቢሆንም፣ ንብረቶቹን የያዛቸው ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርሱን ንብረት በያዘው ሰው ላይ ክስ የማቅረቢያ ጊዜን የሚወስን ነው፡፡

የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ደግሞ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ኖሮት ነገር ግን የውርሱ ኃብት ለእሱ ብቻ የማይገባ በሆነ ጊዜ፣ ሌላኛው ወራሽ ከውርሱ ድርሻውን እንዲያካፍለው ሊጠይቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ምክንያቱም በወራሾች መካከል የመተማመን ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል በሶስት ዓመት ውስጥ ወንድሙ ከአባታቸው ያገኘውን የውርስ ኃብት እንዲያካፍለው ካልጠየቀ፣ ጥያቄውን በይርጋ ለመገደብ አስቦ አይደለም ሕግ አውጭው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ የደነገገው፡፡በመሆኑም ሕጉ ወራሾች ወራሽ ያልሆነ ባዕድ ሰው የውርሱን ንብረት መያዙን ባወቁ በአጭር ጊዜ ውስጥ መብታቸውን እንዲያስከብሩ የሚገፋፋ ሲሆን፣ የሟች ወራሽ የሆነ ሰው የውርሱን ንብረት ጠቅልሎ በያዘበት ሁኔታ ግን የወራሽነታቸውን መብት ካረጋገጡ ወይም ሟች ከሞተ እስከ አሥራ አምሥት ዓመት ባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ድርሻቸውን እንዲያካፍላቸው መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ መተርጐም ያለበት በዚህ መልኩ ነው በማለት ትርጉም የሚሰጡ አሉ፡፡

ከዘር የወረደ ርስትን አስመልክቶ የፍትሐብሔር ሕጉ በወጣበት ጊዜ የነበረው የመሬት ሥሪት ዘር እየተቆጠረ ከአንዱ ወደ ሌላው እንዲተላለፍ ይፈቀድ የነበረ በመሆኑ ሕግ አውጭው የሚች ርስት ለኔ ይገባኛል የሚለውን ጥያቄ የጊዜ ገደብ ሊያደርግበት አልፈለገም፡፡ ሆኖም "ርስት " ማለት ከመሬት ውጭ ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን ለምሣሌ ቤትን ይጨምራል ወይስ አይጨምርም የሚለው ነጥብ በትኩረት መታየት አለበት የሚል አስተያየትና ትችት የሚሰጡ አሉ፡፡ከላይ እንዳነሳነው የውርስ ሕግ የይርጋ ጊዜ ድንጋጌዎች እጅግ በጣም አከራካሪና ውስብስብ ናቸው፡፡ በመሆኑም የዕርቀት ትምህርት ተማሪዎች እነዚህን እና ሌሎች የይርጋ ጊዜ ድንጋጌዎች ዙሪያ የሚነሱትን ጥያቄዎች በቱቶሪያል ክፍል በሚገናኙበት ጊዜ አንስተው መወያየትና መከራከር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በፍርድ ቤቶች የሚሰጠውን ትርጉም ለመረዳት በፍርድ ቤቶች እየተሰጡ ያለ የተለያዩ አተረጓጐሞችንና ተከራካሪዎች የሚያቀርቧቸውን ሙግቶች ማየት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡በውርስ ጉዳይ የይርጋ ክርክር አስቸጋሪነትና የይርጋ ሕግ ድንጋጌዎችን አተረጓጐም ላይ የሚታየውን ልዩነት ለመረዳት ከዚህ በታች በተሰጠቀሱት ሶስት ጉዳዮች የቀረበውን ክርክርክና የተሰጠውን ትርጉም ዋና ዋና ነጥቦች መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

የመጀመሪያው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 992/88 ሚያዝያ 29 ቀን 1993ዓ.ም. በይግባኝ ባዮች በእነ ወ/ሮ እየሩሣሌም ታደሰ /ሶስት ሰዎች/ እና በመልስ ሰጭዎች በሆኑትና የወ/ሮ እሸቴ የሱፍ ወራሾች በሆኑት እነ ወ/ሮ አበባየ ወ/ሚካኤል /ስድስት ሰዎች/ መካከል በሰጠው ውሣኔ ላይ የቀረበውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች አተረጓጐም ላይ የቀረበውን የመከራከሪያ ሀሣብ ነው፡፡የጉዳዩ መነሻ ግምቱ ብር 10000/ አስር ሺ ብር/ የሆነ በቀድሞው አሠራር ጉለሌ አወራጃ እየተባለ ይጠራ በነበረው በቀበሌ 10 ውስጥ የሚገኘው ቁጥር 132 የሆነው ቤት ነው፡፡ የዚህ ክርክር መነሻ የሆነው ቤትም የጥንት ባለቤት ወ/ሮ ሰናይት ኃይለየሱስ የተባሉት ሴት ሲሆኑ ወ/ሮ ሰናይት ጥር 23 ቀን 1949ዓ.ም. ቤቱን ቦታና መሬቱን ለሚመለከት የጽሑፍ ኑዛዜ አድርገው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡ወ/ሮ ሰናይት የተናዘዙት በወቅቱ በህይወት ለነበሩት ልጃቸው ለወ/ሮ ማርትሬዛያ ወ/ሚካኤል ሲሆን ኑዛዜው ለፍርድ ቤት ከቀረበ በኂላ ተቃውሞ ስለገጠመው በፍርድ ቤት የፀና መሆኑን ከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 12 ቀን 1956 የሰጠው ፍርድ ቤት በማስረጃነት ቀርቦ ተያይዟል፡፡ የወ/ሮ ሰናይት ወራሽ የሆነችው ወ/ሮ ማርትሪዘያ ወ/ሚካኤል መጋቢት 11 ቀን 1958ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ሲሆን ይግባኝ ባዮች የሚች ወ/ሮ ማርትሪዘያ ወራሽ መሆናቸውን ለፍርድ ቤት አቅርበው ያረጋገጡት ከሃያ ሁለት ዓመት በኂላ ጥቅምት 1 ቀን 1981ዓ.ም. ነው፡፡

ይግባኝ ባዮች መጋቢት 6 ቀን 1983ዓ.ም. ለአዲስ አበባ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ከላይ የተጠቀሰውን ቤትና ቦታ እናታቸው ወ/ሮ ማርትሪዘያ ከእናቷ ከወ/ሮ ሰናይት የወረሰችውና

በ1958ዓ.ም. እናታቸው ቢሞቱም እስከ 1967ዓ.ም. የአብዮት ለውጥ ድረት በቤትና በቦታው ይኖሩ እንደነበር ገልፀው ከዚያ በኋላ እኛ በማናውቀው መንገድ ወ/ሮ እሸቴ የሱፍ የቤትና የቦታውን የባለቤትነት ስም በስሟ አዛውራና ወ/ሮ እሸቴ የሱፍ በ1982ዓ.ም. ስትሞት የወ/ሮ እሸቴ የሱፍ ወራሾች የሆኑት ከአንደኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር ድረስ ስማቸው ለተጠቀሰው መልስ ሰጭዎች ተላልፎ የወ/ሮ እሸቴ ወራሾች ቤቱንና ቦታውን ለአምስተኛ እና ለስድስተኛ መልስ ሰጭዎች ሸጠውላቸው ስመ ንብረቱ በአምስተኛና በስድስተኛ መልስ ሰጭዎች ስም ተዛውሯል፡፡ በመሆኑም ቤቱና ቦታው ከአያታችን በውርስ የወረደልን ርዕስት ስለሆነ ያለምንም ሕጋዊ መብት ቤቱንና ቦታውን የሸጡት የሟች ወ/ሮ እሸቴ ወራሾችና አምስተኛና ስድስተኛ መልስ ሰጭዎች የውርሱን ንብረት ሊያስረክቡን ይገባል በማለት ይግባኝ ባዮች ክስ አቅርበዋል፡፡መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው የቤቱ ግምት ብር 10000/ አስር ሺ ብር/ ስለሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አከራክሮ የመወሰን ስልጣን የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ክሱ የቀረበው የይግባኝ ባይ አውራሽ ወ/ሮ ማርትሪዚያ ከሞቱ ከሃያ ዓመት በኋላ በመሆኑ ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ባዮች በበኩላቸው ቤቱ ከእናታቸውና ከአያታቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የውርስ ንብረት ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ላይ የተጠቀሰው የሶስት ዓመትም ሆነ የአስራ አምስት ዓመት ይርጋ ሕግ ቀሪ አይሆንም፡፡ እንደዚህ አይነቱ የውርስ ንብረት በሚመለከት የሚቀርብ ክስ በይርጋ ቀሪ ሊሆን አይችልም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ፍርድ ቤቱን ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ስልጣን የለውም በሚለው የመልስ ሰጭዎች/የሥር ተከሣሾች/ መቃወሚያ ላይ ብይን ሣይሰጥ የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ካለቀ በኋላ ተከሣሾች /መልስ ሰጭዎች/ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ጠቅሰው ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ የይርጋ መቃወሚያ ክርክር መሠረት በማድረግ ከሣሾች /ይግባኝ ባዮች/ በውርስ ከእናታችን ሊተላለፍልን የሚገባ ነው የሚሉት ቤት ጉዳይ እናታቸው ከሞቱበት 1958ዓ.ም. ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት ወር 1983ዓ.ም. ድረስ ሃያ አምስት ዓመት በላይ ስለሆነው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ላይ በተመለከተው የአስራ አምስት ዓመት ይርጋ ሕግ ቀሪ ይሆናል በማለት የካቲት 30 ቀን 1086ዓ.ም. ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ባዮች ይህንን የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የይርጋ ሕግ ድንጋጌ በተለይም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ አተረጓጐም በመቃወም ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲያቀርቡ የሕጉ ድንጋጌ " ሟች ከሞተበት ወይም ተከሣሹ በመብቱ ለመስራት ከቻለበት ቀን አንስቶ አስራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርዕስት ካልሆነ በቀር የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም " በማለት ይደነግጋል አሁን ክስ ያቀረብንበት ቤት ከአያታችን ጀምሮ በዘር የወረደልን ርዕስት በመሆኑ የዚህ አይነት ጥያቄ በይርጋ የጊዜ ገደብ ቀሪ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ

ቤት የፈፀመውን የሕግ አተረጓጐም ስህተት በማረም ውሣኔውን እንዲሽረው በማለት ያመለከቱ ሲሆን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ይግባኙን ያስቀርባል ብሎ መልስ ሰጭዎች ክርክራቸውን እንዲያቀርቡ ካደረገ በኋላ አወዛጋቢ ስለሆነው የይርጋ ክርክር ምንም አይነት የወራሽነት ክርክር ወራሾች በሶስተኛ ወገኖች ላይ ሊያቀርቡ እንደማይችሉና ከአስራ አምስት ዓመት በኋላ ክስ ቢያቀርቡ ተከሣሾች የይርጋ ጥያቄ ካነሱ ክሱ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የሰጠው መደምደሚያ ነው፡፡

ሁለተኛው ይግባኝ ባይዮች የዚህ አይነት አተረጓጐም ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ድንጋጌ መንፈስ ውጭ መሆኑን በመጥቀስ ንብረቱ ከዘር የወረደ ርዕስት ከሆነ ወራሾች ምንም አይነት የይርጋ የጊዜ ገደብ ሣይኖርባቸው ከሃምሣ ዓመት ከሰማንያ ዓመት ከዚያም በላይ ቆይተው ክስ ማቅረብ የሚከለከሉበት የሕግ ድንጋጌ የለም በማለት ከዘር የወረደ ርዕስትን ለማስመለስ የሚቀርብ ክስ ምንም አይነት የጊዜ ገደብ አልተጣለበትም የሚለውን ጽንፍ የሚያሣየው ይግባኝ ባዮች ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ የሰጡት ትርጓሜና ያቀረቡት የመከራከሪያ ሀሣብ ነው፡፡በመሆኑም የሚከተሉትን ነጥቦች በትኩረት ማየት ያስፈልጋል፡፡

- ርዕስት የሚለው ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የካቲት 1993ዓ.ም. ባሣተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት የተሰጠው ትርጉም ርዕስት ማለት ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት ማለት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ ይህንን የመዝገበ ቃላት ትርጉም እንዳለ ከወሰድነው ሕጉ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ከመሬት ውጭ ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን ለማስመለስ የሚቀርብ ክስ የይርጋ የጊዜ ገደብ እንዳይኖረው ታስቦ የተቀረፀ ነው ወይ; ብለን ስንጠይቅ በእንግሊዝኛው ቅጅ " action relate famimly immovable" በሚለውና በአማርኛው ርዕስት በሚለው ቃል መካከል ልዩነት እንዳለ እናያለን፡፡
- ይግባኝ ባዮች እንዳቀረቡት በውርስ ከዘር የሚተላለፍ የማይንቀሣቀስ ንብረት አስመልክቶ የሚቀርበው ጥያቄ የጊዜ ገደብ የማይኖረው ከሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለ እጅ /ባለይዞታ/ የሆነ ሰው የዚህኑ ንብረት ግብር ሣያቋርጥ በስሙ ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል በማለት ስለሚደነግግ ይግባኝ ባዮች ያቀረቡት አተረጓጐም እንዴት ከዚህ የሕግ ድንጋጌ ጋር የሚጣጣም ይሆናል የሚለውን ነጥብ መመልከት ያስፈልጋል፡፡
- ሌላው በትኩረት መታየት ያለበት ነጥብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ንዑስ ቁጥር 1 ውስጥ በሁለተኛው ሀረግ ላይ በልዩ ሁኔታ የተቀመጠው መሠረተ ሀሣብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ከዘር የወረደ ርዕስት ካልሆነ በስተቀር የሚለውን ለመረዳትና ለማገናዘብ ብንጠቀምበት፣ መዝገቡን ለመፍታት የሚረዳ አይሆንም ወይ? የሚለውን ሀሣብ በጥልቀት ማየት ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ

የነበረው ሕግ አውጭ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለ እጅ /ይዞታ/ የሆነ ሰው የዚህኑ ንብረት ግብር ሣያቋርጥ ለአስራ አምስት ዓመት ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት እንደሚሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1165 የመጀመሪያው ሀረግ ላይ በግልጽ ካስቀመጠ በኋላ ይኸ ጠቅላላ ሕግ የማይሠራበትን ልዩ ሁኔታ በሁለተኛው ሀረግ ላይ አስቀመጧል፡፡ በልዩ ሁኔታ የተቀመጠው "የማይንቀሣቀሰው ንብረት መሬት ሲሆንና በአገሩ ሥርዐት መሠረት የመሬቱ ርዕስትነት የግል የአንድ ሰው ሣይሆን ተወላጆች የሚካፈሉት በሆነበት ስፍራ ተወላጅ የሆነው ሰው የትውልድ ሀረጉን መዝዞ ርዕስቱ እንዲሰጠው ለመጠየቅ ይህ ይርጋ አያግደውም" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ከዚህ መሠረታዊ ጉዳይ ተነስተን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ውስጥ በዘር የወረደ ርዕስት ካልሆነ በስተቀር የሚለውን አባባል ሕጉ ሲወጣ በነበረው የመሬት ስርዓት ምክንያት ዘር መዝዞ ርዕስት /መሬት/ መካፈል በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ ርዕስት የሚለው ከመሬት ውጭ ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን አያካትትም በሚል አኳኋን ካልተተረጐመ በውርስ በተገኙ የማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ አይሠራም ማለት አይሆንም ወይ? በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168/1/ በሁለተኛው ሀረግ ላይ የተቀመጠውስ ልዩ ሁኔታ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ በዘር የወረደ ርዕስት ከሚለው ቃል ጋር እንዴት ነው ማጣጣም የሚቻለው የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦችን በጥልቀትና በትኩረት መመርመርና ማየት አስፈላጊ ሲሆን አሁን ካለው ሕገ መንግስታዊ ስርዓት አንጻር መሬት የመንግስትና የሕዝብ ንብረት በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ "ከዘር የወረደ ርዕስት ካልሆነ በስተቀር" የሚለው ልዩ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ቀሪ አይሆንም ወይ? የሚለውንም ነጥብ መመርመር ይጠይቃል፡፡

ሁለተኛው የወራሽነት ጥያቄ የይርጋ ክርክር አስመልክቶ ፍርድ ቤት ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 2104/88 ማያዝያ 1 ቀን 1993ዓ.ም. በይግባኝ ባይ የሕጻን አዲስ አለም ሞግዚት አስር አለቃ ደረሰ ሲሣይ እና በመልስ ሰጭዎች እነ ዶ/ር ሰለሞን ተፈራ /ሁለት ሰዎች/ መካከል የነበረውን ክርክር አይቶ በሰጠው ውሣኔ ነው፡፡የክርክሩ መነሻ የአሁን መልስ ሰጭ የሆኑት የሥር ከሣሾች እነ ዶ/ር ሰለሞን ተፈራ የሟች አባታችን ንብረት የሆነው በወረዳ 20 ቀበሌ 51 ክልል የሚገኘው ቁጥር 145 የሆነው ቤት በወታደር ተፈራ አሰገደው ቤት ይግባኝ ባዮች/ የሥር ተከሣሽ/ እንዲያስረክብ የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በመስጠቱ ነው፡፡

የአሁን ይግባኝ ባይ የሕጻን አዲስአለም ሞግዚት በስር ፍርድ ቤት በተከሣሽነት ቀርቦ የከሣሾች/ መልስ ሰጭዎች / ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2000/1/ መሠረት ቀሪ ይሆናል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሌሎች የመከላከያ ሀሣቦችን አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የይግባኝ ባይን/ ተከሣሽን/ የይርጋ ጊዜ ገደብ መቃወሚያና መከላከያ መልስ ውድቅ በማድረግ ይግባኝ ባይ ንብረቱን ለመልስ ሰጭዎች

/ለሥር ከሣሾች/ እንዲያስረክብ ፍርድ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ባይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያነሣሁትን የይርጋ ክርክር እና ሌሎች ነጥቦች በአግባቡ ሣያይ ስለወሰነብኝ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይሻርልኝ ሲል ያመለከቱ ሲሆን መልስ ሰጭዎች በበኩላቸው የይግባኝ ቅሬታውን በመንቀፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን የያዘው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመልስ ሰጭዎች ክስ በይርጋ ይታገዳል ወይስ አይታገድም የሚለውን ጭብጥ አስመልክቶ በሰጠው ውሣኔ " ይግባኝ ባዩ ጉዳዩ በይርጋ ይታገዳል ያለውን በተመለከተ መልስ ሰጭዎች በስር ባቀረቡት ክስ ይገባናል የሚሉት ንብረት የአውራሻቸው ወታደር ተፈራ አሰግደው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ንብረቱ አዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 20 ቀበሌ 51 ክልል ውስጥ የሚገኘው ቁጥሩ 145 የሆነው ቤት ነው፡፡ ይኸ ቤት የአባታችን የግል ሀብት ስለሆነ በውርስ የሚገባን ነው ባዮች ናቸው፡፡ የመልስ ሰጭዎች አባት ወታደር ተፈራ አሰግደው የሞተው ነሐሴ 5 ቀን 1969ዓ.ም. መሆኑን መልስ ሰጭዎች በክርክራቸው ገልፀዋል፡፡ አንደኛው መልስ ሰጭ ወራሽነቱን ያረጋገጠው ጥቅምት 1983ዓ.ም. መሆኑን ተያይዞ የቀረበው የፍርድ ቤት ውሣኔ ያመለክታል፡፡ ሁለተኛው መልስ ሰጭ የሟች ወራሽ መሆኑ ባይካድም መቼ ወራሽነቱን እንዳስወሰነ የፍርድ ቤት ማስረጃ አላቀረበም፡፡የመልስ ሰጭዎች አባት ሚስት የነበረችው ወ/ሮ ሽታዬ ተሾመ ደግሞ የሞተችው በታህሣሥ ወር 1978ዓ.ም. ላይ ነው፡፡ ይግባኝ ባይ ወ/ሮ ሽታየ ተሾመ ከሞተች በኋላ መቼ ቤቱን እንደያዘው የተረጋገጠበት መንገድ ባይኖርም እስከ ታህሣሥ ወር 1978ዓ.ም. ድረስ በሟች በወ/ሮ ሽታየ ይዞታ ስር የቆየ መሆኑን ነው መረዳት የሚቻለው፡፡ ይግባኝ ባይ የሚታወቀው ወ/ሮ ሽታየ ተሾመ የወለደቻቸ ሕጻን አዲስዓለም ደረሰ ሞግዚት ነኝ ብሎ በመቅረቡ እንጅ በሞግዚትነቱም ሆነ በሌላ መንገድ ቤቱን መቼ እንደያዘው አልታወቀም፡፡

መልስ ሰጭዎች ይግባኝ ባይ ቤቱን መያዙን አወቅን የሚሉት በ1981 ወይም 1982ዓ.ም. ላይ ነው፡፡ ይግባኝ ባይም ከዚህ ቀደም ብለው ቤቱ በእኔ መያዙን ያውቃሉ አላለም፡፡ ይኸ ከሆነ ወ/ሮ ሽያዬ ከሞተችበት ጊዜ አንስቶ መልስ ሰጭዎች ክሱን እስካቀረብኩበት ጥቅምት ወር 1984 ድረስ ያለው ሲታሰብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ላይ ተወስኖ የተገኘው የይርጋ ዘመን አላለፈም፡፡ ይግባኝ ባይ ይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት የመልስ ሰጭዎች ከነሐሴ ወር 1969ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚለው ተቀባይነት የሚሰጠው አይደለም፡፡ ምክንያቱም ይግባኝ ባይ ቤቱን የያዘው የመልስ ሰጭዎች አባት ከሞተበት 1969ዓ.ም. ጀምሮ ባለመሆኑና እስከ ታህሣሥ ወር 1978ዓ.ም. ድረስ በሟቿ ወ/ሮ ሽታየ ተሾመ ተይዞ የቆየ ስለሆነ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ የውርስ ንብረትን በተመለከተ የሚያገለግለው የይርጋ ዘመን ይግባኝ ባይ እንደሚለው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ ላይ የተመለከተው የሶስት ዓመት ይርጋ ዘመን ሣይሆን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ የተጠቀሰው የአስራ አምስት ዓመት የይርጋ ዘመን ነው፡፡ ከዚህ የይርጋ ዘመን አንጻር ሲታይ መልስ ሰጭዎች በአሁኑ ይግባኝ ባይ ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የሚታገድ ሊሆን አይችልም፡፡ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይ ያቀረበውን የይርጋ ክርክር ወድቅ ያደረገው በአግባቡ

ነው" በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡በዚህ ጉዳይ እና ፍርድ ቤቱ በሰጠው የሕግ ትርጉም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ ላይ የተጠቀሰው የይርጋ የጊዜ ገደብ ለሚንቀሣቀሱ ንብረቶች ብቻ የሚሠራ መሆኑ የፍትሐብሔር ቁጥር 1000/2/ የተቀመጠው የአስራ አምስት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ለማይንቀሣቀስ ንብረት የሚሠራ መሆኑን ለያይቶ ለመግለጽና የሁለቱን ድንጋጌዎች አጠቃቀም ለማሣየት ተሞክሯል፡፡

ሆኖም በዚህ ውሣኔ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ነጥቦችን በውል ሣያብራራ እንደውም በሚያደናግር መልኩ አድበስብሷቸው ያለፈ ይመስለኛል፡፡ የመጀመሪያው በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ከሣሹ በመብቱ መስራት ከቻለበት የሚለውን ሀረግ የተረጎመበት አግባብ ነው፡፡ አንድ ሰው የወራሽነት ማስረጃውን ሣያወጣ አስር ዓመት በራሱ ቸልተኝነት ቢቆይ በመብቱ መስራት የሚቻለው የወራሽነት ማስረጃ ካገኘበት ጊዜ ጀምሮ ነው የሚለው አተረጓጉም ተገቢነት አለውን? ከሣሹ በራሱ ጥፋትና ቸልተኝነት ያባከነው ጊዜ በመብቱ መስራት ከቻለበት ቀን አንስቶ በሚለው ሀረግ ውስጥ የሚሸፈን ነው ወይስ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የሟችን መሞት የውርሱን መከፈት የሚያውቅ ወራሽን ለመጥቀም ነው በመብቱ ለመስራት ከቻለበት ቀን አንስቶ የሚለው ሀረግ የሚለው በአግባቡ መታየት አለበት፡፡ ሌላው በዚህ ጉዳይ መልስ ሰጭዎች ሟች መሞቱንና ቤቱ በሟች ወ/ሮ ሽታየ ተሾመ መያዙን ካወቁበት ቀን ጀምሮ መሆን አልነበረበትም ወይ የይርጋ የጊዜ ገደቡ መቆጠር ያለበት፡፡ የወ/ሮ ሽታየ ልጅ ሕጻን አዲስአለም አወራሷ ወ/ሮ ሽታየ ተሾመ በመከላከያነት ልታነሣው የምትችለውን ነጥብ ሁሉ በሞግዚቷ አማካኝነት የማቅረብና የመከራከር መብት የላትምን?

መልስ ሰጭዎች ሟች መሞቱን ካወቁበት ጊዜ ጀምሮ በአስራ አምስት ዓመት ውስጥ ከቤቱ ውስጥ በማናቸውም መንገድ ያሉ ሰዎች በውርስ ያኙትን ቤት እንዲያስረክቧቸው በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 36/3/ መሠረት መጠየቅ የሚችሉ ሆኖ እያለ ፍርድ ቤቱ እስከ 1978 ቤቱ በወ/ሮ ሽታየ በመያዙ 1978ዓ.ም. በኂላ በወ/ሮ ሽታየ ተሾመ ወራሽ ሕጻን አዲስ አለም መያዙን ከፋፍሎ ይርጋውን ለማሰብ የተጠቀመበት ምክንያት ምንድን ነው የሚሉት ነጥቦች በጥልቀት መታየት ይገባቸዋል፡፡

ሌላው በወራሽነት ጥያቄ የይርጋ ክርክርን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች መካከል ያለውን ልዩነት የማያሣየው የምዕራብ ጉጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 1936 ሐምሌ 13 ቀን 1996ዓ.ም. የሰጠወን ወሣኔ መነሻ በማድረግ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 4606 የካቲት 15 ቀን 1997ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ነው፡፡የክርክሩ መነሻ እነ ሁሴን አብዲ አባታቸው አቶ አብዲ ታከለ ከሟች እናታቸው ጋር በጋብቻ ያፈራውን ንብረት ግማሹን ለእኛ ለወራሾቹ እንዲያካፍለን በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ አቶ አብዲ ታከለ በበኩላቸው የከሣሾች እናት ከሞተች

ሃያ ሰባት ዓመት እንደሆናት በመግለጽ የከሣሾች ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ መሠረት በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበዋል። የከሣሾች ጠበቃ በበኩላቸው ምንም እንኳን እነ ሁሴን አብዲ ወላጅ እናታቸው በሞት ከተለዩ በኋላ ከእናታቸው በውርስ ሊያገኙ የሚገባቸውን ሀብት ሣይጠይቁ ሃያ ሰባት ዓመት የቆዩ ቢሆንም ከሣሾች አባታቸውን ያልከሰሱት የእናታችንን ድርሻ ከፍለህ ስጠን ብሎ ለማለት አባታቸውን የማክበር ፍርሀት ስላለባቸው ነው። በመሆኑም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች በቴዘመዳሞች መካከል ተፈጻሚ የሚሆን የሕግ ድንጋጌ አይደለም። ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ማየት ያለበት ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ጋር በማዛድ ነው። ከሣሾች ወላጂ አባታቸውን አክብረውና ፈርተው የውርሱ ንብረት /የእናታቸውን/ ድርሻ እንዲያካፍላቸው አልጠየቁም ነበር። አሁን ግን ተከሣሽ ሌላ ሚስት ያገባ በመሆኑ ድርሻቸወን መጠየቅ ግድ ሆኖባቸዋል በማለት ተከራክረዋል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የምዕራብ ጉጃም ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋጌዎች በወርስ ጉዳይ ተጠቃሽ ሊሆን እንደማይገባወና ተፈጻሚነትም እንደሌለው ካስቀመጠ በኋላ የከሣሾች ክስ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ መሠረት በይርጋ ይታገዳል በለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎችን አሰናብቷል።

በስር ፍርድ ቤት ከሣሽ የነበሩት እነ ሁሴን አብዱ በጠበቃቸው አማካኝነት መስከረም 6 ቀን 1997ዓ.ም. በስር ያሱትንና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 የይርጋ ድንጋገዎች በቤተዘመድ መካከል የሚሠራ አይደለም። ፍርድ ቤቱ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ድንጋገዎች ከግምት ወስጥ ማስገባት ነበረበት በለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበወ በስር ፍርድ ቤት ተከሣሽ የነበሩት መልስ ሰጭ መልሣቸወን ካቀረቡ በኋላ የካቲት 15 ቀን 1997ዓ.ም. በድምጽ ብልጫ ውሣኔ ሰጥቷል።በውሣኔው አብላጫ ድምጽ የሰጡት ዳኞች፣

"ግራ ቀኙ የሚከራከሩት በውርስ ሀብት ሲሆን በክርክሩ የተነሣው ጭብጥ የይርጋ ጥያቄ ሲሆን መልስ ሰጭ ይግባኝ ባዮች የውርስ ሀብቱን ሊጠይቁ ከሚገባቸው ጊዜ አሣልፈው ያቀረቡት በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል ሲሉ ይግባኝ ባዮች ደግሞ መልስ ሰጭ አባታችን በመሆኑ ምክንያት አክብረን ውርሱን ሣንጠይቅ የቆየን በመሆኑ በይርጋ ሊታገድብን አይገባም ብለዋል የስር ፍርድ ቤት ይህን አስመልክቶ የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/2/ መሠረት በማናቸውም አስተያየት የውርስ ይርጋ ጥያቄ የሚቋረጥበት ምክንያት ቢቀርብም ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ስለሚገልጽ ክርክሩ በይርጋ ይታገዳል በማለት በፋ/መ/ቁጥር 01936 በ13/11/96 በዋለው ችሎት የሰጠውን ብይን የሚነቀፍ ባለመሆኑ በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ አጽንተነዋል "በማለት የወሰኑ ሲሆን፣ልዩነታቸውን ያሰፈሩት ዳኛ ደግሞ፣

"ይህ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በአብላጫ ድምጽ የስር ፍርድ ቤት ድምጽ የስር ፍርድ ቤት ብይን የሚያፀድቅ የራሱን ውሣኔ ሰጥቷል።የስር ፍ/ቤት ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ለሰጠው ብይን በዋቢነት የጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/2/ እና የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 245/2/ ነው። ከመዝገቡ ላይ እንደተረዳሁት ከሆነ ክርክሩ ውርስን የሚመለከት ሲሆን የሚከራከሩትም ወላጅ አባትና ልጆች ናቸው በከሣሽነት የቀረቡት ልጆች ሲሆኑ የሚከራከሩበትም ንብረት መኖሪያ ቤትና ቦታን የሚመለከት ነው። ይግባኝ ባዮች/ልጆች/ ከእናታቸው ሞት በኋላ አከራካሪውን ንብረት በመልስ ሰጭ የተያዘ መሆኑን ያውቃሉ የተያዘውን ክስ ያቀረቡትም እናታቸው ከሞቱ ከ25 አመት በኋላ ነው። ክሱ ከዚህ ጊዜ በኋላ የቀረበ ቢሆንም የእናታቸው ሞትና ንብረቱም በመልስ ሰጭ የተያዘ መሆኑን የሚየውቁ እንደመሆኑ መጠን የይርጋው ጊዜ መታየት ያለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1000/1/ መሠረት እንጅ በንዑስ ቁጥር ሁለት ላይ በተመለከተው አይደለም። እንደተረዳሁት ከሆነ ንዑስ ቁጥር ሁለት የተደነገገው ራሱን የቻለ የይርጋ ጊዜ ለማስቀመጥ ተብሎ ሣይሆን በንዑስ ቁጥር አንድ ላይ የተመለከተውን ከፍተኛ የይርጋ ጊዜ ለመገደብ በሚል ምክንያት ነው። በተጨማሪም እነዚህ ድንጋጌዎች የይርጋ የገደብ ጊዜ ከማስቀመጥ ውጭ ይርጋ ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚመለከቱ አይደለም ይህንና የውርስ ሕጉ በሌሎች ጉዳዮች ላይ አልፎ አልፎ ስለይርጋ የደነገገውን ስንመለከተው ይርጋ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ የሚገልጹት ነገር የለም። ይህም ይህን በተመለከተ የውርስ ሕጉ ክፍተት ያለው መሆኑን የሚያመለክት ነው። እንዲህ ባለ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ ደግሞ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ጉዳይ በፍ/ሕ/ቁጥር 1677/1/ እና 1853 ሊታይ የሚገባው ሆኖ ይሰማኛል። ከሣሾች ልጆች እንደመሆናቸው መጠን በአካባቢያችን ባህልና ሞራላዊ አመለካከት አንጻር ከሣሾች በጊዜው አባታቸውን ያልከሰሱት አባታቸውን በመፍራትና በማክበር እንደሆነ መገመት የሚያዳግት አይደለም። ስለሆነም የይርጋ ጊዜው በተጠቀሰው ሕጋዊ ምክያት መቋረጥ የሚገበው ሆኖ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ በዋናው ጉዳይ ላይ ክርክራቸው እንደገና ሊታይ ይገባል በማለት የተለየ ሃሣቤን አቅርቤአለሁ" በማለት ገልፀዋል።

በከፍተኛው ፍርድ ቤት እና በክልለ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቀረበወ ክርክርና የተሰጠወ ውሣኔ አሁንም በይርጋ ዙሪያ የወርስ ሕጉ ድንጋገዎች ተፈጻሚነትና አተረጓጐም ችግር ያለባቸወ መሆኑን የበለጠ ግልጽ የማያደርግ ነው።ይህንን ጉዳይ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1002 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች አቀራረጽ በማየት ጭምር የውርስ ሕግ የይርጋ ድንጋጌዎች በቤተዘመዳሞች በመካከል ወይም ወራሾች እርስ በርሣቸው በሚያደርጉት ክርክር ተፈጻሚነት ይኖረዋል ወይ? የሚለውን ነጥብ ማንሣት ይቻላል። የወራሽነት የይርጋ ጊዜ ገደብን አስመልክቶ ያሉትን ድንጋጌዎች ስንመለከት የመጀመሪያው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 ሲሆን መሠረቱ ቁጥር 1 ብሎ የሚጀምር ነው። ይኸ ድንጋጌ ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ የሌለው ሰው ከውርሱ አንዱን ክፍል በእጁ ያደረገ እንደሆነ እውነተኛው ወራሽ ወራሽነቱ

እንዲታወቅለትና የተወሰዱት ንብረቶች እንዳመለሱለት ክስ ማቅረብ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ከዚህ በማስከተል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ቁጥር 2 ሲሆን ጥያቄውን ለማቅረብ የተወሰነ ጊዜ በማለት ያስቀምጣል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1001 ቁጥር 3 ስለ ውጤቶች ይደነግጋል የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1002 ቁጥር 4 ሆኖ ልዩ የኑዛዜ ስጦታ የተደረገላቸው ሰዎች ያስቀምጣል፡፡

እነዚህ ከአንድ እስከ አራት ተከታታይ ቁጥር የተሰጣቸው ድንጋጌዎች ተያይዘው መተርጐምና ተግባር ላይ መዋል እንዳለባቸው ድንጋጌዎቹን በቁጥር ማያያዝ የተፈለገበት ምክንያት ይኸው እንደሆነ የሚያከራክር አይደለም፡፡ ይኸ ከሆነ የፍትሐበሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች መነበብና መተርጐም ያለባቸው በመርህ ደረጃ ከተቀመጠው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 ጋር መሆን ይገባዋል ከተባለ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 999 እውነተኛ ወራሽ የሆነ ሰው የሟች ወራሽ ካልሆነ ሰው የውርሱን ንብረት ማስመለስ የሚችል መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ በሁለት እውነተኛ ወራሾች መካከል የሚነሣ ድርሻየ ይገባኛል ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 የይርጋ የጊዜ ገደብ አይቋረጥም በማለት ክርክር ማንሣት ይቻላል፡፡ ሆኖም እዚህ ላይ መነሣት ያለበት ጥያቄ፣

- ወራሾች የውርሱን ድርሻ ሌላኛው ወራሽ እንዲሰጣቸው ክስ በማናቸውም ጊዜ ማቅረብ ይችላሉ ቢባል ሌሎች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1168 ያሉት ድንጋጌዎች እንዴት ተፈጻሚነት ለማግኘት ይችላሉ?
- አንድ ክስ የሚቀርብበትን ጊዜ በይርጋ መገደብ ያስፈለገበት ዋናውን ዓላማስ የሚያዛንፍ አይሆንም ወይ?
- የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 በውርስ ጉዳይ በቤተዘመድ መካከል ያለን የውርስ ንብረት ለመካፈል ተፈጻሚ ማድረግ ተገቢነት አለው የሚሉትንና ሌሎች ነጥቦች በትኩረት ማየት አለባቸው፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ካየናቸው ሶስት በፍርድ ቤት ታይተው የተወሰኑ ጉዳዮች እንደሚታየው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች አተረጓጐምና ተፈጻሚነት ላይ ሰፊ ልዩነትና ክፍተት ያለ መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 ድንጋጌዎች በወራሾች መካከል ባለ ክርክር የሚያገለግል የይርጋ የጊዜ ገደብ ነው፡፡ ወራሽ በሆነና ወራሽ ባልሆነ ሰዎች መካከል ያለውን ክርክር የሚገደብ የይርጋ ህግ ድንጋጌ ስለሌለ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1677(1) 1845 ተፈፃሚ ይሆናል በማለት በልዩ ውሣኔ ስጥቷል ይኸ የመጨረሻውና አምስተኛው አተረጓጐም ነው፡፡

# <u>የመወያያ ጥያቄዎች</u>

1. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ እና 968/2/ መካከል የመልዕክት አለመጣጣምና ግጭት አለ ብለው ያስባለ?
2. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/1/ እና 9000/2/ እንዴት መተርጐምና መፈፀም አለባቸው ብለው ያሰባሉ?
3. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ "ርስት" የሚለው ቃል ከመሬት ሥሪት ውጭ ሌሎች የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን በሚጨምር መንገድ መተርጐም አለበት ብለው ያስባሉ? ለምን?
4. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2000/2/ በአማርኛው <u>ቅጅ ከዘር የወረደ ርዕስት</u> ካልሆነ በስተቀር የሚለው ሀረግና በእንግሊዝኛው ቅጅ " unless the action relates to family immovable" የሚለው ሀረግ ተመሣሣይ መልዕክት ያስተላለፋሉ ብለው ያስባለ፡፡ ልዩነት ካላቸው የትኛውን ቅጅ ነወ ቅድሚያ መስጠት ያለብን?
5. የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1852 በውርስ ጉዳይ በቤተዘመዳሞች መካከል የሚነሣ የይርጋ ክርክርን አስመልክቶ ተፈጻሚነት ሊኖረው ይገባል የሚለው ክርክር ተገቢ ነውን? ለምን?
6. " በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1000/2/ ወራሹ መብቱን ለመስራት ከቻለበት ቀን ጀምሮ " የሚለው አባባል እንዴት ነው መተርጐም ያለበት፡፡ አንድ ወራሽ መብቱን ሊሠራበት አይችልም ነበር የሚባለው በምን ሁኔታ ነው?
7. ከዚህ ጽሑፍ ጋር በተያያዘው እነ ጌታቸው አሰፋው እና እነ ጌታቸው ጅማ ጉዳይ አይተው

   ሀ. ፍርድ ቤቱ ስለ ይርጋ አተረጓጐም የሰጠው ትችት ተገቢነት

   ለ. መልስ ሰጭ ውትድርና መቆየቱ መብቱን ሊሠራበት አልቻለም በማለት ያሣለፈው ብይን ምክንያታዊና የሕጉን መንፈስና አላማ ያገናዘበ መሆኑን ያብራሩ
8. የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1000 እና 1080 ንዑስ አንቀፅ 3 ድንጋጌዎች ዓላማና ግብ እንደዚሁም የተፈፃሚነት ወሰን ያብራሩ
9. የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥሮች 32815፣28102፣28508፣25507 የሰጣቸውን ውሳኔዎች በማንበብ ይተቹ፡፡

## ዋቢ መፅሐፍት

- Blacks Law Dictionary

  Seventhe Edition, ST PAUL MINN, 1999
- Parry H.D The Law of Testate and Intestate Seccession ,Sweet and Maxweu limited , 1966
- Atkinson, Tomas, Hand book of the law of wills it paul minn, wese publishing cor. 1953
- Coluson, N.S, Succession in the musuin Family, Cambridge, at university press, 1971.